# የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርት

## የተማሪ መማሪያ



## 5ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

©የመጽሐፉ ህጋዊ ቅጂ ባለቤት 2014 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው፡፡

# ምስጋና

ይህን የትምህርት መፅሐፍ ዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣ በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ **አቶ ዘላለም ሙላቱ** የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለሥራችን መሳካት ሁል ጊዜ አብረውን በመሆን፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ **አቶ አድማሱ ደቻሳ**፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ **አቶ ዳኛው ገብሩ** የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ **አቶ ሳምሶን መለሰ**፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ **ወ/ሮ አበበች ነጋሽ**፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ **አቶ ሲሳይ እንዳለ**፣ የቴክኒክ አማካሪ **አቶ ደስታ መርሻ** ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስከሚ ጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

# የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርት

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

# 5ኛ ክፍል


### አዘጋጆች

ጥበቡ ወልደዩሐንስ
ይርጋ ቁምላቸው
ዩሐንስ ሰብስቤ

### ገምጋሚዎች

እየሩሳሌም በዳኔ
ማርቆስ ወልደሃና
ሰሎሞን ኃይለማርያም

### አስተባባሪ

ጌታቸው ታለማ

### ሌይአውት ዲዛይን

በእንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምዕራፍ አንድ፡ጥበባዊ ግንዛቤ ........ 1
የምዕራፍ አንድ መግቢያ ........ 1
1.1. የሙዚቃ አላባዊያን ........ 2
1.1.1 ስልተ-ምት (Rhythm) ፡-ስልተ ምት ምንድነው? ........ 3
1.1.2 ኃይለ ድምፅ (Dynamics) ........ 3
1.1.3 ቴምፖ (tempo)፡ ........ 5
1.1.4 የክረት መጠን (Pitch ቃና) ........ 6
1.1.5 ዜማ (Melody) ........ 6
1.1.6 ህብረ- ሙዚቃ (harmony) ........ 7
1.1.7 የድምፅ ቀለም (Timber) ........ 8
1.1.8 የጊዜ ቆይታ (Duration) ........ 9
1.2. የውዝዋዜ አላባዊያን ........ 13
1.2.1 የሰውነት ቅርፅን መሰረት ያደረገ አቋቋም ........ 13
1.2.2. የቦታ አያያዝና አጠቃቀም እንቅስቃሴ ........ 14
1.2.3. ከአጣማሪ ጋር እንቅስቃሴ ማቀናጀት ........ 14
1.3. መሰረታዊ የትያትር አላባዊያን ........ 15
1.3.1. ከዋኞች (ተዋንያን) ........ 15
1.3.2 ተደራሲያን (ታዳሚዎች) ........ 16
1.3.3 አዘጋጅ ........ 16
1.3.4 የመከወኛ ቦታ ........ 16
1.3.5 ጥበባዊ ግብዓቶች ........ 17
1.3.6 ጽሑፈ- ተውኔት ........ 17
1.3.7. ቀላል የቪዲዮ አቀራረጽ ዘዴ ........ 18
1.3.8 የቅርብ እይታ ቀረጻ ........ 18
1.3.9 የመካከለኛ እየታ ቀረጻ ........ 18
1.3.10. የሩቅ እይታ ቀረጻ ........ 19
1.3.11. የአጠቃላይ እይታ ቀረጻ ........ 21
1.4. የዕይታ ጥበባት አላባዊያን ........ 21
1.4.1. የዕይታ ጥበባት ........ 21

1.4.2. መስመር ........................................................ 22
1.4.3. መሰረታዊ መስመሮች ........................................................ 23
1.4.4. የመስመር አይነቶች ........................................................ 24
1.4.5. ምስለ ቅርፆች ባለሁለት አውታረ መጠን (2ዲ) ........................................................ 24
1.4.6. ምስለ ቅርጽ ባለ ሦስት አውታረ መጠን / 3ዲ/........................................................ 25
1.4.7. አካባባዊ ቦታ........................................................ 26
1.4.8. ሕብረ ቀለም ........................................................ 26
1.4.9. ሻካልሴ / ሻካራና / ልስላሴ ........................................................ 29
1.4.10. የንጣትና ጥቁረት ሂደት / value / ........................................................ 30
1.4.11 መጠን / proportion /........................................................ 31
1.1.12 ሐረግ ........................................................ 33

## ምዕራፍ ሁለት ፡-ፈጠራን መግለፅ ........................................................ 38

የምዕራፍ ሁለት መግቢያ ........................................................38
2.1 የሙዚቃ ኖታዎችን መፃፍና ስያሜያቸውን መጥራት ........................................................ 39
2.2 ስብስብ (Staff) ........................................................ 42
2.2.1. የሙዚቃ መስመርና ባዶ ቦታ መሰየሚያዎች (clefs) ........................................................ 44
2.2.2. የድንገተኛ ምልክቶች (Accidentals sign)፡-........................................................ 48
2.2.3. የጊዜ አመልካች (Time signature)........................................................ 50
2.3 በውዝዋዜ እንቅስቃሴ የሙዚቃ ድምፆችን መግለጽ........................................................ 51
2.4. አልባሳትንና የመዋቢያ ግባአቶችን ተጠቅሞ ቲያትር መስራት ........................................................ 52
2.5 የገፅ ቅብና መዋቢያ ግብዓቶች ........................................................ 55
2.6 የወረቀት ሞዛይክ እና ዝግ ህትመት/በድንች/ማተም/........................................................ 71
2.6.1. የማጠበቂያ አሠራር........................................................ 73

## ምዕራፍ ሦስት፡- ታሪካዊና ባህላዊ አውዶች........................................................ 78

የምዕራፍ ሦስት መግቢያ........................................................78
3.1. ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸው ሃገረሰባዊ መዝሙሮች ........................................................ 78
3.2 ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸው ሀገረሰብ የውዝዋዜ አይነቶች........................................................ 85
3.3. የሃገረሰብ ተረትና ታሪኮች መንገር........................................................ 86
3.4 የዕይታ ጥበባት ታሪክ / የዋሻ ውስጥ ጥበብና ቀለም ቀብ ........................................................ 94

ምዕራፍ አራት፡- ሥነውበታዊ ዕሴት (ዋጋ) ............................................. 100

የምዕራፍ አራት መግቢያ..............................................................................100

4.1 የሙዚቃ ጥበብ ሃሳብን ከውዝዋዜና ከቲያትር ጥበባት ሐሳብ ጋርያለውን ልዩነትና አንድነት መወያየት..................................................................................................100

4.1.1. የውዝዋዜ ሃሳብን ከሙዚቃና ከቲያትር ጥበባት ሐሳብ ጋር ያለውን ልዩነትና አንድነት መወያየት ልማዳዊ የሃገረሰብ ውዝዋዜ..................................................101

4.1.2. የቲያትር ሃሳብን ከሙዚቃና ከውዝዋዜ ጥበባት ሐሳብ ጋር ያለውን ልዩነትና አንድነት መወያየት ........................................................................................................102

4.2. የዕይታና እደጥበባት አስፈሊጊነት በማህበረሰቡ ውስጥ ........................................105

4.2.1 አካላዊ ጥቅሞች ........................................................................................107

4.2.2 የእይታ ጥበባት ትምህርት የማስታወስ ችሎታ ያሻሽላል......................................107

ምዕራፍ አምስት፡- ጥምርታ፣ ዝምድናና፣ ትግበራ.................................... 112

5.ጥመርታ ..................................................................................................112

5.1. የትራፉክ፣ የኤችአይቪ፣ የአደንዛዥዕፅ፣ ወዘተ...የሚገልፁ/ድንበር ተሻጋሪ ዘርፈብዙ ጉዳዮችን/፣መዝሙራትን ......................................................................................113

5.1.1 የትራፊክ፣ የኤችአይቪኤድስ፣ የአደንዛዥዕፅ፣ ወዘተ... የሚገልፁ/ድንበር ተሻጋሪ ዘርፍብዘ ጉዲዮችን/ ውዝዋዜማጣመር ማጣመርና ምከወን 118

5.1.2 የትራፉክ፣ የኤችአይቪ፣ የአደንዛዥዕፅ፣ ወዘተ... የሚገልፁ/ድንበር ተሻጋሪ ዘርፍ ብዘ ጉዲዮችን/ተውኔት ማጣመር ...........................................................................119

5.1.3 አካባባቢው አቅጣጫ ማሳያ ምልክቶች /አርማ እና እና የተስቅሉ ............................124

5.2 የንግድና ተዛማች ዘርፍ ያላቸው ዳርጅቶችና አርማዎቻቸው.....................................127

5.2.2 የትራፊክና የመንገድ ዳር አቅጣጫ ጠቀዋሚ ምልክቶች..........................................128

5.2.3 ፖስተር ................................................................................................ 130

ዋቢ መጽሃፍት............................................................................................133

## የመጽሐፉ መግቢያ

ይህ ትበዋናነት በአራት የጥበብ ዘርፎች ላይት ኩረት ያደረገ ሲሆን እነሱም፡- ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣ ትያትር፣ ወይም ፊልም እናየዕደ-ጥ+ብ (ሥዕል፣ ቅርፅበ ጋራ አካቶና አጣምሮ በመያዝ/ እንዲይዝ ተደርጎ የተዘጋጀ ሲሆን በክ.ዕ.ጥ. በሃገራችን ብሎም በዓለም ደረጃ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ፋይዳው የጎላ ከመሆኑም ባሻገር ለፈጠራ ለቴክኖሎጂ ብሎም የአንድ አገር እድገት የሚለካው በእነዚህ የተዘረዘሩ አራት የጥበብ ዘርፎች ላይ የሚወሰን መሆኑየሚያከራክር አይደለም፡፡

የክ.ዕ.ጥ.እድገት አሁን ካለውና ወደ ፊት ከሚመጣው የቴክኖሎጂ ሁኔታ ጋር ማመጣጠን አስፈላጊ ስለሆነ እና ክ.ዕ.ጥ. ለተማሪዎች ሁለንተናዊ እውቀት ከፍተኛ አስተዋጽዖ የሚያበረክት መሆኑ ታምኖበት በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ከሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ በዚህ የክ.ዕ.ጥ. ትምህርት ውስጥ አምስት ምዕራፎች የተካተቱ ሲሆን እነሱም፡- ምዕራፍ አንድ ጥበባዊ ግንዛቤ፣ ምዕራፍ ሁለት ፈጠራ ንመግለፅ፣ ምዕራፍ ሦስት ታሪካዊና ባህላዊ አውዶች፣ ምዕራፍ አራት ሥነ-ውበታዊ እሴት፣ ምዕራፍ አምስት ጥመርታ፣ ዝምድናና ትግበራ የሚሉ ይዘቶች ተካተውበታል፡፡ በእነዚህ ይዘቶች ውስጥ የተለያዩ ዋና ዋና ርዕሶች እና ንዑሳን ርዕሶች በዝርዝር የቀረቡበት ትምህርት ነው፡፡

## የመፅሐፍ አጠቃላይ አላማ

ከእዚህ የክፍል ደረጃ በኂላ ተማሪዎች የሚከተለትን ትችላላችሁ፡-

- ቀላል የዕይታ ጥበብን አላባዊያንን (በመስመር፣ በቅርፅ፣ በፎርም፣ በቀለም፣ በይዘት፣ ሻካራነትና ልስላሴ፣በመጠን፣በሐረግ) ትለያላችሁ፡፡
- የቲያትር፣የቪዱዮ ቀረፃ ዘዴ፣ትለያላችሁ፡፡
- ቀላል የውዝዋዜ አላባዊያንን ዘዴ፣ትለያላችሁ፡፡
- ቀላል የሙዚቃ አላባዊያንን ሪትምን፣ዲይናሚክስን/ሃይለ ድምፅን/ቴምፖ /የፍጥነት ልክ/፣ ፒች/ የክረት መጠን/ ወዘተ..ታውቃላችሁ፡፡
- ቀላል የሙዚቃ ኖታዎችን ታነባላችሁ፡፡
- የወረቀት ሞዛይክ፣ብሎክ ህትመት/ፎቶ ህትመት/ትሰራላችሁ፡፡
- አልባሳትና የመዋቢያ ግብአቶችን በመጠቀም ቀላል ቲያትር ታቀርባላችሁ፡፡
- የተለያዩ የክዋኔ ጥበባትን በመጠቀም ተመሳሳይነትና ሌዩነት ያላቸውን ሃሳቦች ትገልፃላችሁ፡፡
- የእይታ ጥበብንና ዕደ ጥበባትን በህብረተሰብ ውስጥ ያለውን ጥቅም ትገልፃላችሁ፡፡
- የትራፊክ ፣የኤች አይ ቪ ኤድስ፣የአደንዛዥ ዕፅ፣ወዘተ… /ድንበር ተሻጋሪ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን/መዝሙር ትዘምራላችሁ፡፡
- የትራፊክ ፣የኤች አይ ቪ ኤድስ፣የአደንዛዥ ዕፅ፣ወዘተ… /ድንበር ተሻጋሪ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን/በውዝዋዜ ትገልፃላችሁ፡፡
- የትራፉክ ፣የኤች አይ ቪ ኤድስ ፣የአደንዛዥ ዕፅ፣ወዘተ… /ድንበር ተሻጋሪ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን/በትያትር ታቀርባላችሁ፡፡

- በህብረተሰቡ አካባቢ እየተዘዋወሩ የተሰቀሉትን አመልካቾች፣ ምልክቶች፣አርማዎች፣የተለጠፈ ማስታወቂያዎችን ጥናት ማድረግ የማህበረሰቡን የተለያዩ ዓይነት ሀገርኛ መዝሙሮችን ትለያላችሁ፡፡
- የማህበረሰቡን የተለያዩ ዓይነት ሀገርኛ ውዝዋዜዎችን ትለያላችሁ፡፡
- በታሪክ ያሉትን የተለያዩ የዕይታ ጥበብ/የዋሻ ጥበብና ቀለም ቅብ/ ትገልፃላችሁ፡፡
- የሃገር ውስጥ የጥበብ እንቅስቃሴን በመዝሙራት፣በውዝዋዜዎች፣በትያትር፣በድምፅ አልባ እንቅስቃሴ ትከውናላችሁ፡፡
- የታወቁ ሃገርኛ መዝሙሮችን ትመድባላችሁ፡፡
- የታወቁ ሃገርኛ ውዜዋዛዎችን ትመድባላችሁ፡፡
- የጎበኛችኃቸውን ቦታዎች ሪፖርት በቃል ታቀርባላችሁ፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## ጥበባዊ ግንዛቤ

### የምዕራፍ አንድ መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የተካተቱት ዋናዋና ይዘቶች እና በቅድሚያ ማወቅ ስላለብን ይዘቶች ሲሆን የሚያነሱ ናቸው፡፡ እነዚህ ይዘቶችም የሙዚቃ አላባዊያን፣የውዝዋዜ አላባዊያን፣መሰረታዊ የቲያትር አላባዊያን የዕይታ ጥበባት አላባዊያን ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

የሙዚቃ አላባዊያን ስንል ለሚዚቃ መፈጠር /ለመፍጠር /መሰረትና/ አስፈላጊ የሆኑ ሲሆን እነሱም ፡- ስልተ ምት፣ ኃይለ ድምፅ፣ ቴምፖ፣ የክረት መጠን፣ዜማ፣ ህብረ ድምፅ፣ የድምፅ ቀለም፣ የጊዜ ቆይታ ሲሆኑ ስለእነዚህ በዝርዝር የሚገለፅበት ይሆናል፡፡

የውዝዋዜ አላባዊያን ስንልም እንደውዝዋዜ ውዝዋዜ እንዲባል የሚያሰኙት ሲሆኑ እነሱም፡- የሰውነት ቅርፅን መሰረት ያደረገ አቋቋም ፣የቦታ አያያዝና አጠቃቀምና ከአጣማሪ ጋር እንቅስቃሴ ማቀናጀት ሲሆን ስለ እነዚህ አላባዊያን በዝርዝር የምናያቸው ይሆናል፡፡

መሰረታዊ የትያትር አላባዊያን ውስጥ የምናያቸው/የተካተቱት/ደግሞ ከዋኞች/ተዋኒያን/፣ ተደራሲያን/ታዳሚያን/፣ አዘጋጅ፣ የመከወኛ ቦታ /መድረክ/፣ ጥበባዊ ግብአቶች፣ ጽሁፈ ተውኔት፣ እና ስለ ቀላል የቪዲዮ አቀራረፅ ዘዴ የሚሉትን በተግባር የተደገፈ እንቅስቃሴ ማድረግ በዝርዝር ይገለፅበታል፡፡

የዕይታ ጥበባት አላባዊያን የምንላቸው እና የዕይታ ጥበብን የዕይታ ጥበብ እንዲሆን የሚያስችሉ ሲሆኑ እነሱም፡- መስመር፣ ቅርጽ፣አካባቢያዊ ቦታ፣ ህብረ ቀለም፣ ሻካራና ልስላሴ፣ ንጣትና ጥቁረት፣ መጠንና ሐረግ፣ የሚያካትት እና ስለእነዚህ የዕይታ ጥበብ አላባዊያን የሚዳሰሱበት ምዕራፍ ነው፡፡

የዕይታ ጥበባት አላባዊያን የምንላቸው እና የዕይታ ጥበብን የዕይታ ጥበብ እንዲሆን የሚያስችሉ ሲሆኑ እነሱም፡- መስመር፣ ቅርጽ፣አካባቢያዊ ቦታ፣ ህብረ ቀለም፣ ሻካራና ልስላሴ፣ ንጣትና ጥቁረት፣ መጠንና ሐረግ፣ የሚያካትት እና ስለእነዚህ የዕይታ ጥበብ አላባዊያን የሚዳሰሱበት ምዕራፍ ነው፡፡

## 1.1.የሙዚቃ አላባዊያን

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- መሰረታዊ የሆኑትን የሙዚቃ አላባውያን ታገልፃላችሁ፡፡
- ቃላቶችን ትረዳላችሁ፡፡
- የተለያዩ ምልክቶችን ትለያላችሁ፡፡

### 1.1.1 ስልተ-ምት(Rhythm) ፡- ስልተ ምት ምንድን ነው

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የስልተ ምትን ትርጉምና ጥቅም ትናገራላችሁ፡፡
- የጊዜ አጠቃቀምን ትገልፃላችሁ፡፡

ስልተ ምት ሙዚቃን በእኩል የጊዜ ፍሰት በትክክል እንድንጫወት የሚያደርግ የአጨዋወት መሰረት ነው፡፡ እንድ ሙሉ የምት ጊዜ የምንለው በእግራችን እረግጠን ስናነሳ ይሆናል ስልተ ምት በሙዚቃ ብቻ ሳይሆን በአረማመድ፣አመጋገብ የመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች ሁሉ የምት አመልካቾች ናቸው፡፡

### 1.1.2 ኃይለ ድምፅ (Dynamics)

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የዳይናሚክ ጠቀሜታ ትረዳላችሁ፡፡
- መግለጫዎችን አጠቃቀም በተግባር ትሰራላችሁ፡፡
- ጥአመ ዜማ የሚለውን በምሳሌነት ትገልፃላችሁ፡፡

የሙዚቃ ልስላሴና (ጮክ) ማለት ነው:: ኃይለድምፅ የጩሁትመጠን ማለት ነው:: ሙያው ላይ ላሉት ሙዚቀኞች መሳሪያ ተጫዋቾችም ሆነ ድምፃውያን ለሚሰሩዋቸው ሙዚቃዎች ወይም ለሚያቀናብሩዋቸው ስራዎች መሰረታዊ ከሆኑት ዋናው ነው:: በአጠቃላይ ከመጠን በላይ አጉሉቶ መጫወትም ሆነ መስራት ከጤና ችግር አልፎ ለአካባቢ የድምፅ ብክለትን ያስከትላል::

ሰንጠረዥ:- 1 የኃይለ ድምፅ ምልክቶች

| በምኅፃረ ቃል | የጣሊያንኛው ቃል | በእንግሊዝኛው ቃል ትርጉም | በአማርኛ ቃላት |
|---|---|---|---|
| ppp | pianississim | Extreemy soft | እጅግ በጣም የለሰለሰ |
| pp | pianissimo | very soft | በጣምለስላሳ |
| mp | mezzo-piano | moderately soft | በመካከለኛለስላሳ |
| p | piano | soft | ለስላሳ |
| f | forte | loud | ጮክ ያለ ድምፅ |
| mf | mezzo-forte | moderately loud | በመካከለኛጩኸት ድምፅ |
| ff | fortissimo | very loud | በጣም ጮክ ያለ ድምፅ |
| fff | Fortississimo | Extreemly loud | እጅግ በጣም ጮክ ያለ ድምፅ |

## 1.1 ቴምፖ(tempo)

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርትተምራችሁካጠናቀቃችሁበኋላ፡-

- የሙዚቃ የፍጥነት ልኬትን ታውቃላችሁ
- የፍጥነት ልኬት ምልክቶችን ትለያላችሁ
- የጊዜ ውስንነትን ትረዳላችሁ

አንድ የመዝሙር ወይም የዘፈን ዜማ ስናዳምጥ ዜማው የተስተካከለና ጣዕም እንዲኖረው የተስተካከለ ፍጥነት ጊዜ ውስንነት ፍጥነቱን ጠብቆ እንዲዜም የሚያደርጉ ከብዙ በጥቂቱ መምሪያም ምልክቶች ሲኖሩት ብቻ ነው:: መምሪያዎቹ በደቂቃ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን የምት ፍጥነት አመልካቾች ናቸው:: (metronome) ምልክት የምትፍጥነት በደቂቃ (beats per minute) (bpm) አመልካች ነው::

ምሳሌ፡- ♩ =60

| በጣሊያንኛው | በእንግልዝኛው | በአማርኛው | የምቶቹ ፍጥንት በደቂቃ (bpm) |
|---|---|---|---|
| Largo | Very very slow | እጅግ ብጣም ዝግታ | 40 - 60 |
| Larghetto | Very slow | ብጣም ዝግታ | 60 - 66 |
| Adagio | slow | ዝግታ | 66 - 76 |
| Andante | Moving a long | መካከለኛ ዝግታ | 76 - 108 |
| Moderato | Moderatly | መካከለኛ ፍጥነት | 108 - 120 |
| Allegro | Fast and quick | ፍጣን | 120 - 169 |
| Presto | very Fast | በጣም ፍጣን | 169 - 200 |
| prestissimo | very very Fast | እጅግ በጣም ፍጣን | 200 |

### 1.1.4 የክረት መጠን Pitch(ቃና)

ከተማሪዎች የሚጠበቀው  የመማር ውጤት

ይህን ትምህርትተምራችሁካጠናቀቃችሁበኋላ፡-

- የድምፅ ቅጥነትንና ውፍረትን ልዩነት ታውቃላችሁ
- የድምፅን ልኬት ኸርዝ መሆኑን ታውቃላችሁ

ድምፆች በአየር ርግብግቦሽ አማካኝነት የሚፈጠሩና  ዝቅታና ከፍታን መጠን ልኬት (ኸርዝ) መጠን መለኪያ ነው፡፡




Pitch

### 1.1.5 ዜማ (Melody)

ከተማሪዎች የሚጠበቀው  የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ስለዜማ ምንነት ትረዳላችሁ፡፡
- ዜማ የተሟላ ድርሰት ሀሳብ እናዳለው ታስረዳላችሁ፡፡

ዜማ የተለያዩ ድምፃች ከስልተ ምት ጋር በአንድ ተዋህደው (ተደርሰው) የምናዳምጠውሙዚቃ ነው፡፡ ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በጋራ የምዘምራቸው የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር እንደዚሁም ትምህርታዊ መዝሙሮች በጨዋታ ጊዜ የምናዜማቸው ሙዚቃዎች ዜማ እንላቸዋለን፡፡

### 1.1.6 ህብረ-ሙዚቃ (harmony)

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ስለ ህብረ ድምፅ ክፍሎች ታውቃላችሁ፡፡
- የድምፆች በኅብር መቀናጀትን ትለያላችሁ፡፡

የተለያዩ ድምፆች በኅብር ሁለትና ከእዚያ በላይ ተቀናጅተው የምናደምጣቸው ሙዚቃዎች ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ድምጽ በአራት የድምፅ ምድቦች ይመደባል፡፡ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፦

1.ሶፕራኖ፡- እጅግ በጣም ቀጭን የሆኑ ድምፆች የህፃናት ታዳጊዎች እና ሴቶች ድምጽ ነው፡፡(ቀጭን የሴት ድምጽ ነው፡፡)

2. አልቶ፡- መካከለኛ ቀጭን ድምፅ በአብዛኛው ከመካከለኛው ወፍራም ድምፅና ከቀጭን ድምጽ በአማካኝ የምናደምጠው ድምፅ ነው፡፡(ወፍራም የሴት ድምጽ ነው፡፡)

3.ቴኖር፡- መካከለኛ ወፍራም ድምፅ ነው፡፡ ይህድምፅ በታዳጊ ጎረምሶች የምንሰማው ነው፡፡(ቀጭን የወንድ ድምጽ ነው፡፡)

4.ቤዝ፡- በተለምዶ ጎርናና ድምፅ የምንለው በጎረምሶች በትልልቅ ሰዎች ላይ ምናደምጠው ድምፅ ነው ፡፡(ወፍራም የወንድ ድምጽ ነው፡፡)

### 1.1.7 የድምፅ ቀለም (Timber)

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርትተምራችሁካጠናቀቃችሁበኋላ፡-

- ስለ ድምጽ ጥራት በሚገባ ትለያላችሁ

በሠው ተፈጥሮ ድምፅ ወይም በሙዚቃ መሳሪያዎች የድምፅ ውስንነት ጥራት ነው፡፡ የሃገራችንን የባህል ሙዚቃ መሳሪያ ከሆኑት ከበሮ እና የዘመናዊውን ድራም ያላቸው የድምፅ ቀለም ልዩነት የተለያየ ነው፡፡ አንድን ሰው ከሌላ ሰው የምንለይበት ነገሮች አንዱ የድምፅ ቀለም ነው፡፡

መልመጃ አንድ

I. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊድል ምረጥ /ጭ/፡፡

1. በሙዚቃ ድምፅ ፍጥነት ልኬት ረጋ ያለ የምት ፍጥነት አመልካች የሆነ ይቱ ነው?

ሀ. 120 ለ.90 ሐ.180 መ. 60

2. ለማድመጥ ተስማሚ የሆነና በቀላሉ የግጥም ፅሁፍን ሃሳብ መረዳት የሚያስችል

ሀ. ቴምፖ ለ.ሜሎዲ ሐ. ዳይናሚክስ መ. ቆይታ

3. የድምፅ ኖታና የእረፍት ኖታ ምልክቶች በእኩል ዋጋ ፍሰቱን እንድን ጠብቅ የሚያስችለን

ሀ.እረፍት ለ.ጥራት ሐ. የጊዜ ቆይታ መ.ቴምፖ

4. ኳስን ወደ መሬት አንጥረን ስንይዝ ምንን ያመለክታል?

ሀ.ዜማ ለ.ምት ሐ.ጥለዛን መ ቆይታን

II. ከእዚህ በታች ለተሰጡትን ጥያቄዎች መልሱን ፃፉ::

1. በሰው ልጅ የድምፅ ደረጃ ወፍራም የሴት ድምፅ_________ ይባላል
2. አንድን ዜማ በማድመጥ እያለን ዝምታ ቢኖች_________ መሆኑን ይገልፃል::
3. ሙዚቃን በእኩል ጊዜ እንድንጫወትና እንድናዳምጥ የሚያደርግ የድምፅ አደራደር _________ነው::
4. የሙዚቃ ድምፅ ዜማ የምት መጠን _________የባላል::

III.ከእዚህ በታች በ "ሀ" ስር የተዘረዘሩትን ከ "ለ" ስር ብተዘረዘሩት ጥያቄዎች አዛምድ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የድምፅ ጥራት | ሀ. ዜማ |
| 2. የድምፅ ጩኸት ልስላሴ | ለ. ፎርቲሲሲሞ |
| 3. ከልክ ይለፈ የድምፅ ከፍታ | ሐ. ዳይናሚክ |
| 4. ክረቶችን በስራዖት የመደርደር ጥበብ | መ. ቲምበር |

### 1.1.8 የጊዜ ቆይታ (Duration)

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ስለ ጊዜ አጠባበቅ ታውቃላችሁ::
- መሰረታዊ ምልክቶችን ትረዳላችሁ::
- የኖታና የረፍት ምልክቶች የስም ስያሜና የምት ጊዜ ዋጋቸውን ታውቃላችሁ::

የድምፅ ኖታዎችና የዕረፍት ኖታዎች ምልክቶች ድምፆችንና ዕረፍቶችንና በአጭርና በረጅም የጊዜ አቆጣጠር እንድንጫወት የሚያስችሉ ናቸው።

የድምፅ ኖታዎችና የዕረፍት ኖታዎች መፃፊያ ምልክት የስም አጠራርና ዋጋ ያላቸው ናቸው። የድምፅ ያነባበብ ስልቱም በአለም አቀፍ የኖታ ንባብ (ታ) ወይም (ላ) በማለት ነው።

| የድምፅ ኖታ ምልክቶች | የእረፍት ኖታ ምልክቶች | በአማርኛ | በእንግሊዝኛ | የጊዜ ቆይታ |
|---|---|---|---|---|
|  |  | ሙሉ | Whole | 4ምት |
|  |  | ግማሽ | half | 2ምት |
|  |  | ሩብ | quarter | 1ምት |
|  |  | አንድ ስምንተኛ 1/8 | Eighth | 1/2 ምት |
|  |  | አንድ አስራ ስድስተኛ 1/16 | sixteenth | 1/4ምት |

## የድምፅ ኖታዎች ተዋረድ



## የእረፍት ኖታዎች ተዋረድ



### መልመጃ ሁለት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎቸ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ

1. 𝅗𝅥 _ ♩ = ♩

2. 𝅗𝅥 x 𝅗𝅥 = 𝅝

ከዚህ በታች ለተጠቀሱት ትክክለኛውን መልስ ስጡ

1. ♩ + ♩ + 𝅗𝅥 = ________

2.  = ______

3.  = ______

4.  = ______

1. ድምፅ የኖታውንና የዕረፍት ኖታውን ምልክቶችን ስም ግለፅ

ጥያቄ 
1 2 3 4 5 6 7 8 9 10 11 12 13 14 15 16

2. የኖታው አቻ የቆይታ መጠን ያለውን የረፍት ምልክቶችን ፃፍ

ሀ  = ______

ለ  = ______

ሐ  = ______

መ  = ______

## 1.2.የውዝዋዜ አላባዊያን

ውዝዋዜ ወይም ዳንስ አካላዊ እንቅሰቃሴ ሆኖ የስሜት መግለጫ ከመሆን ባሻገር ሐሳብ ገላጭ ነው፡፡

የሚጠበቁ ውጤቶች

ከተማሪዎች የሚጠበቀው  የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- መሰረታዊ የሆኑትን የውዝዋዜ ክፍሎች ታውቃላችሁ፡፡
- የውዝዋዜ እንቅስቃሴ ከስልተ ምት ጋር ጥምርታ መኖሩን ታውቃላችሁ፡፡

### 1.2.1 የሰውነት ቅርፅን መሰረት ያደረገ አቋቋም

የእዚህ ውዝዋዜ ስልተ ምት እንቅስቃሴ ወገብን ይዞ መቆም፤ እግርን ከፊት ማድረግ፤ መንበርከክ፤መተኛት፤ወደፊት ደረትን ገፋ አድርጎ በመቆም በፊት ለፊት እይታ ሙሉ ገፅጻን ማሳየት፤በጎናዊ የትከሻ ትይዩ አቋቋሞችን በውዝዋዜዎቻችን ውስጥ ማየት የተለመደ ነው፡፡

ሰውነት እንቅስቃሴ የዚህ ውዝዋዜ ስልተምት እንቅስቃሴ ትከሻን ወደላይና  ወደታች እያደረጉ እያንቀጠቀጡ እግር እያነሱና እያስቀመጡ ወገብን እያናጡ (ጎንበስ ቀና)እያሉአንገትን ወደ ኋላና ወደ ፊት ወደ ጎን ማሽከርከርን፣ እጅ ማወናጨፍን፣ እግር ማጋጨትን፣ ወዘተ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን ያካትታል፡፡

### 1.2.2.የቦታ አያያዝና አጠቃቀም እንቅስቃሴ

ስልተምት እንቅስቃሴ ክብ ሰርቶ መሽከርከርን ወደፊትና ወደኃላ መንቀሳቀስን ከወዲያ ወዲህ መዝለልን በጆርባ ተኝቶ መንቀሳቀስን ሁሉ ያካትታል።

### 1.2.3.ከአጣማሪ ጋር እንቅስቃሴ ማቀናጀት

ስልተምት እንቅስቃሴ ተመሳስሎትን (የእንቅስቃሴ መመሳሰል) በአይን መተያየትን ወገብንና ትከሻን ተቃቅፎ መጨፈርን አካላዊ ምላሽ መስጠትን ፈገግታን የቁሳቁስ ጥመርታዊ አጠቃቀምን በሙሉ ይጨምራል።

#### መልመጃ አንድ

I ከእዚህ በታች ለተሰጡት ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ ስጡ።

1. ውዝዋዜ ስሜታዊና ስፖርታዊ ክዋኔ ነው።
2. እግርና መቀመጫን በማንቀሳቀስ ባህላዊ ጭፈራ ማሳየት አይቻልም።
3. በየጊዜው የሚለዋወጥ ውዝዋዜ ባህላዊ ውዝዋዜ ይባላል።
4. በውዝዋዜ እውቀት ማስተላለፍ ይቻላል።

## 1.3.መሰረታዊ የቲያትር አላባዊያን

ከተማሪዎች የሚጠበቀው  የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃች ሁበኋላ፡-

- -ስለትያትር አላባዊያን፡ ታውቃላችሁ፡፡
- -ከወኖችን ታውቃላችሁ፡፡
- -ተደራሲያንን ታውቃላችሁ፡፡
- -ስለትያትር አዘጋጅ ስለ መከወኛ ቦታ ታውቃላችሁ፡፡
- -ጥበባዊ አላባዊያንን ፅሁፈ- ተውኔት እንዲሁም ቀላል የቪዲዮ አቀራረፅን በመማር ትለማመዱታላችሁ፡፡

አላባውያን የሚባሉት ለነገሮች መፈጠር ምክንያት የሆኑ ማለትም የተፈጠረውን ነገር ቅርጽ እና ይዘት የሚወስኑ እንዲሁም ምንነቱን የሚገልጹ ሁነው በውስጡ የሚካተቱ መሰረታዊ ነገሮች ናቸው፡፡ ስለሆነም የትያትር አላባውያን የምንላቸው ትያትር በውስጡ የያዛቸው ከሃሳብ ጀምሮ መድረክ ላይ እስኪከወን ድረስ የሚያለፍባቸውን ሙያዊ ጥበባት ሁሉ የሚያጠቃልል ሲሆን በተለያዩ ዘመናት እንደ ጥበባዊ ይዘቱ እና የአቅርቦት ቅርጹ የተለያዩ ነገሮችን እየጨመረና እየቀነሰ ዘልቋል፡፡ አሁን ባለንበት ጊዜ ላይ የምንጠቀምባቸው የዘመናዊ ትያትር አለባውያን የሚከተሉት ናቸው፡-

### 1.3.1.ከዋኞች (ተዋንያን)

ከዋኞች ወይም ተዋንያን የሚባሉት በጽሁፍ የቀረቡ የድርሰቱ አለም ፍጡራንን (ገጸ ባህርያትን) በመወከል አሳማኝ በሆነ መንገድ ታሪካቸውን በመድረክ ላይ የሚያቀርቡ ሰዎች ናቸው፡፡

### 1.3.2 ተደራሲያን (ታዳሚዎች)

ተደራሲያን ትያትር ተዘጋጅቶ በሚቀርብበት ጊዜ በማቅረቢያ ቦታው በመገኘት ትያትር የሚታደሙ ሰዎች ሲሆኑ ከተዋንያን ጋር ባላቸው ጥበባዊ ግንኙነት (መስተጋብር) በሚያስለቅሰው እያለቀሱ በሚያስቀው እየሳቁ ቀጥተኛ ግብረ-መልስ (አስተያየት)በመስጠት ለትያትር መቀጠል እና ጥበባዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

### 1.3.3 አዘጋጅ

በጽሁፍ የሰፈረውን ሃሳብ ሊታይ ወደሚችል ጥበባዊ ስራ በመቀየር ህይወት የሚዘራበት እውቀት እና ክህሎቱ ከፍያለ ሰው ነው፡፡ በድርሰቱ (ጽሁፊ- ተውኔቱ) ላይ በመነሳት መታየት፣ መነገር እና መከወን ያለበትን ነገር ሁሉ የሚፈጥር ሲሆን ተዋንያንን፣ የጥበባዊ ግብዓት ባለሙያዋችን እንዲሁም ሊሆን የሚገባውን የእይታ ሁናቴ እና ድባብ መርጦ በማስተካከል (በማሰልጠን) ለአድማጭና ለተመልካች የሚመጥን ስራ (ትያትር) በበላይነት በመምራት ያዘጋጃል፡፡

**መልመጃ 1**

I የሚከተሉትን ጥያቄዋች ትክክል ከሆነ እውነት ወይም ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. አላባውያን ለነገሮች መፈጠር ምክንያት ሲሆኑ የነገሮችን ቅርፅና ይዘትም ይወስናሉ፡፡
2. ከዋንያን በፅሁፍ የቀረቡ የምናቡ ዓለም ፍጡራን ናቸው፡፡
3. ተደራሲያን ግብረ መልስ ይሰጣሉ፡፡
4. አዘጋጅ የጥበባዊ ስራዎች ሁሉ የበላይ መሪ ነው፡፡

### 1.3.4 የመከወኛ ቦታ

ለተመልካች እና ለባለሙያዎች ምቹ የሆነ፣ እይታን የማይጋርድ፤ ከዋኞች ሲያቀርቡበግልጽ የሚታዩበት፤ ለአድማጭ ተመልካቾች የሚመጥን መቀመጫ እንዲሁምሌሎች ግብዓቶችን ያካተተ ቤት ዉስጥ ከቤት ውጪ፤ ወይም በልዩ ልዩ ተንቀሳቃሽነገሮች ላይ መድረኮችን በተለያዩ ቅርጾች እና አይነቶች በመገንባት ትያትር ተዘጋጅቶየሚቀርብበት ቦታ ነው፡፡



የትያትር መድረክ

### 1.3.5 ጥበባዊ ግብዓቶች

የተለያዩ ለትትር ክዋኔ አጋዥ የሆኑ ነገሮች ሲሆኑ ስራው አምሮ እንዲታይ፤ተዋንያን (ከዋኞች) የወከሏቸውን ገጸ-ባህርያት እንዲመስሉ፤የድርሰቱን ዓለም፣ ቦታውን፣ ዘመኑን እንዲሁም ማህበረሰቡን በግልጽ በማሳየት ጥበባዊ ይዘቱ ይበልጥ እንዲዳብር ያደርጋሉ፡፡ የመዋቢያ ቁሳቁሶች፣ አልባሳት፣ የመገልገያ ቁሳቁሶች፣ ጌጣጌጦች፣ የመድረክ መጋረጃወች፣ መብራቶች፣ የድምጽ ግብዓቶች፣ ሙዚቃ፣ ልዩልዩ ስዕሎች፣ ቅርጻ ቅርጾች እና የመድረክ ላይ ግንባታዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

### 1.3.6 ጽህፈት- ተውኔት

የተውኔት ጽሁፍ በደራሲው ምናብ (አእምሮ) የሚፈጠር ሲሆን ደራሲው ስለተፈጥሮ ያለውን ግንዛቤ፤ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚዊ፣ እንዲሁም ማህበራዊ ሁኔታወችና ምልከታዎች ባገኘው እውቀት፤ የግል ስሜቱን፣ እምነቱን፣ እንዲሁም ፍልስፍናውን ተጠቅሞ ለተለያዩ የማቅረቢያ ስልቶች በታሪክ ነገራ ወይም ለመድረክ ክዋኔ በሚሆን መልኩ በዝርው ወይንም በግጥም የሚጽፈው ድርሰት ነው፡፡

መልመጃ 2

I የሚከተሉትን ጥያቄወች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. የመከወኛ ቦታ በግልፅ መታየት የለበትም፡፡
2. መድረኮች በቤት ውስጥ፤ ከቤት ውጪ፤ ወይም በተንቀሳቃሽ ነገሮች ላይ መሰራት ይችላሉ፡፡
3. የመደረክ ግንባታዎች ከጥበባዊ ግብዓቶች ውስጥ አይደሉም፡፡
4. ደራሲ የራሱን ስሜት ማንፀባረቅ ይችላል፡፡

### 1.3.7. ቀላል የቪዱዮ አቀራረጽ ዘዴ

የፊልም አዘጋጅ ለአንዳች መሰረታዊ ጉዳይ ሃሳብ ገለጻ ለተመልካች የሚያሳዩትን የገጸ- ባህርይ ድርጊት በካሜራ እይታ ውስጥ በማስግባት የሚገልጹበት ሲሆን የፊልም ጽሁፍ ጸሃፊው እንደሚተርከው ሁሉ አዘጋጆች ደግሞ በምሥል ቀረጻ አይነት በሚገባ ያዋቅሩና ይተርካሉ፡፡ እንደ ምስሉ መጠን እና ስሜት ልዩነት የሚገልጹ አላባውያን አሉት፡፡ እነሱም፡- የቅርብ እይታ ቀረጻ፣ የመካከለኛ እየታ ቀረጻ፣ የሩቅ እይታ ቀረጻ እና የአጠቃላይ እየታ ቀረጻ ናቸው፡፡

### 1.3.8 የቅርብ እይታ ቀረጻ

አዘጋጁ ካንገት በላይ ያሉ እይታዎችን በመምረጥ የተዋናዩን አትኩረታዊ እንቅስቃሴ ለማሳየት የሚጠቀምበት ነው፡፡ ያላቸውንም ጠቀሜታ ስናይ
የገጸ
ባህርይን ስሜት ይገልጻሉ፡፡
በታሪኩ ውስጥ ልብ ሰቀላን ይፈጥራሉ፡፡
እይታን በማጉላት ግልጽ እና ተተኳሪ ምስል ይፈጥራሉ፡፡

### 1.3.9 የመካከለኛ እይታ ቀረጻ

ይህ የቀረጻ አይነት የሚቀረጹ ማንኛውም አይነት ገጸ-ባህርያት እና ትዕይንታዊ ቁሳቁሶች በመካከለኛ የምስል ርቀት የሚቀረጽበት ነው፡፡ የእይታ መጠናቸውም ከፊል የሰውነት ክፍል በሰው ከወገብ በላይ እንደማለት ነው፡፡

### 1.3.10. የሩቅ እይታ ቀረጻ

በአንድ ፊልም ውስጥ የቦታን፣ የጊዜን፣ እና የገጸ-ባህርይን የጥምረት ክንውን በጥቅል ለመግለጽ የሚጠቅም የቀረጻ አይነት ነው፡፡ ፊልሙ መቼ እና የት እንደሚፈጸም በምን ያህል ሰዎች ቡድን እንደሚሰራ ያሳያል፡፡

### 1.3.11. የአጠቃላይ እይታ ቀረጻ

የፊልሙ ታሪክ የሚከናወንበትን ቦታ ከነሙሉ ድባቡ እና አካባቢው በማሳየት በተረጋጋና በተደጋጋሚ እይታ የጊዜ ለውጥ ይገለፅበታል፤ የተፈጥሮ ለውጥ ይታይበታል፤ የታሪኩ መከወኛ ቦታ ይገለጽበታል፤ እንዲሁም ድባቡ ከነሙሉ የተዋንያን እንቅስቃሴ ጋር ይታይበታል።




1 የሩቅ እይታ
2 መካከለኛ ሩቅ ዕይታ
3 መካከለኛ ቅርብ ዕይታ
4 ቅርብ ዕይታ
5 መካከለኛ ዕይታ

#### የመልመጃ አንድ ጥያቄዎች

I የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለትመልሱ።

1.የመከወኛ ቦታን ከነሙሉ አካባቢው የሚያሳይ ቀረጻ አጠቃላይ እይታ ቀረጻ ይባላል።

2. ተደራሲያን በመድረክ ላይ ገጸ- ባህርያትን ወክለው ይከውናሉ።

3. ካንገት በላይ ከዋኙን አጉልተን የምንቀርጽበት ዘዴ የሩቅ እይታ ይባላል።

## የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ እይታዊ ጥበብ ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ፊልም ለ. ትያትር ሐ. የሬዲዮ ድራማ መ. ሁሉም

2. ከሚከተሉት አንዱ የትያትር ባለሙያ አይደለም።

   ሀ. ተዋናይ ለ. አዘጋጅ ሐ. የካሜራ ባለሙያ መ. መልስ የለም

3. ከሚከተሉት አንዱ በደራሲው አማካኝት ይከወናል።

   ሀ. የመድረክ ዝግጅት ለ. የፊልም ቀረጻ ሐ. መብራት መ. ድርሰት

## የሚከተሉትን ጥያቄዎች አብራርታችሁ መልሱ።

1. በአዘጋጅ እና በደራሲ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
2. የትያትር ታዳሚዎች ለትያትር መሰራት ያላቸው አስተዋጾ ምንድን ነው?
3. በተዋንያን እና ገጸ-ባህርት መካከል ምን ልዩነት እና ግንኙነት አለ?
4. ቀላል የቪዱዮ አቀራረጽ ዘዴ የምንላቸው ምን ምን ናቸው?

## 1.4.የዕይታ ጥበባት አላባዊያን

ከተማሪዎች የሚጠበቀው  የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የዕይታ ጥባባት አላባዊያንን ትለያላቹ፡፡
- የዕይታ ጥበባት አላባዊያንን ጥቅም ትገነዘባላችሁ፡፡
- የመሰረታዊ መስመር ባህሪን ታውቃላችሁ፡፡
- የዕይታ ጥበባት አላባዊያን ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ትለያላችሁ፡፡

### 1.4.1.ዕይታ ጥበባት

ስለ ዕይታ ጥበባት ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ አንድን ንድፍ እንዴት ይዋቀራል?

የአንድ ጥሩ ንድፍ መመዘኛ ነጥቦችና እነዚህን የመሳሰሉ የዕይታ ጥበብ አላባዊያን

ይካትታሉ፡፡ ለማንኛውም ዕይታ ጥበባት ድርሰት፣ ንድፎች፣ ቀለምቅብ፣ ፎቶግራፍ ……ወዘተ የመሳሰሉትን ዘርፎች መሰረትና መዋቀር ነው፡፡

አንድ የፈጠራ ባለሙያ ሀሳቡን በተግባር ለማሳየት በስሌዳ፣ በወረቀት፣ በሸራ …….. ወዘተ አካል ላይ ሀሳቡን ዕይታ ጥበባት የሚያቀነባብርበት የተለያዩ ይዘት ያላቸው ማቀባበሪያ አላባዊያን ግብዓቶች ናቸው፡፡

### 1.4.2.መስመር፡-

የዕይታ ጥበባት ውስጥ መስመር ትልቅ ከሆኑት ግብአቶች አንዱና የመጀመሪያው ነው፡፡ መስመር በእንቅስቃሴ የሚፈጠር ምልክት በመሆኑ የትኛውም አይነት መስመር ርዝመት፣ ውፍረት፣ ቀጥነት፣ አቅጣጫ አለው፡፡

### 1.4.3.መሰረታዊ መስመሮች

**መሰረታዊ መስመሮች የምንላቸው የሚከተሉት ናቸው::**



ቋሚ መስመር



አግድም መስመር



ሰያፍ መስመር



ተጣጣፊ መስመር



ጥቅልል መስመር



ማእበላማ መስመር



ጠመዝማዛ መስመር

ሥዕል፡-መሰረታዊ መስመሮች

### 1.4.4.የመስመር አይነቶች

መሰረታዊ የመስመር አይነቶች ሰባት ናቸው:: ከላይ ተዘርዝረው ወይም ተስለው የምትመለከቷቸው መስመሮች የተገኙት እነዚህ ዋና መስመሮች ግጥምጥሞሽና የአቅጣጫ መቀያየር ነው::

ሀ -የመሰረታዊ መስመሮችን ለመሳል የሚያስፈልጉ ቍሳቁሶች

- የንድፍ እርሳስ B1፣ B2 ፣ B3.... ወዘተ
- ልሙጥ ወረቀት መሳያ፣ላጺስ፣መቅረጫ

ለ - የሚሰሩ ተግባራት

- በወረቀት ላይ በእርሳስ መለማመድ::

አሰራር ቅደም ተከተል

- የተለያዩ የምናውቃቸውን መስመሮች ያለማስመሪያ ነፃ ሆናችሁ

በማስመር መለማመድ

- የምታሰምሯቸው መስመሮች በነፃነት ስለሆነ ላጺስ መጠቀም አያስፈልግም

### መልምጃ 1

ሀ ለሚቀጥሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።

1. የአንድ ጥሩ ንድፍ መመዘኛ ነጥቦች ምንድ ናቸው?
2. የዕይታ ጥበባት አላባዊያንን ዘርዝሩ።
3. የመስመሮች ጥቅምን ዘርዝሩ።
4. መሰረታዊ መስመሮች የምንላቸው የትኞቹ ናቸው?
5. የመስመር አይነቶች ለምን ሁለት ብቻ ሆኑ?
6. ስንት አይነት መስመሮችን ተለማመዳችሁ?
7. መስመር ስትለማመዱ የትኛው መስመር አይነት ነው የከበዳችሁ?
8. የከበዳችሁን የመስመር አይነት መምራችሁ እንዲያሳዩዋችሁ ጠይቁ።

### 1.4.5.ምስለ ቅርፆች ባለሁለት አውታረ መጠን (2ዲ)

ምስለ ቅርፆች ባለ ሁለት አውታር መጠን (2ዲ) የሚባሉ የመስመሮች መዋቅር ውጤት ሲሆን ሁለት አውታር መጠን ያለው ዝርግ የሆኑ የተለያዩ ቅርፆች ናቸው።



ክብ(ሰርክል)



አራት ማዕዘን



እኩል አራት ማዕዘን



ሶስት ማዕዘን

ሥዕል፦መሰረታዊ ባለ ሁለት አውታር ቅርፅ / 2ዲ/

### 1.4.6.ምስለ ቅርጽ ባለ ሦስት አውታረ መጠን / 3ዲ/

ምስለ ቅርጽ አይነት ከላይኞቹ የሚለየው ባለሦስት አውታር መጠን /3ዲ/ በመሆኑ ነው። ይህም ማለት ፊት ለፊት፣ ከጎንና ከላይ በኩል የሚታይ አድርጎ የማሳያ ዘዴ ነው።





ሥዕል፦ምስለ ቅርጽ /ባለሦስት አውታር መጠን / 3ዲ/

### 1.4.7.አካባባያዊ ቦታ

ማንኛው የመሰረታዊ አካባቢዊ ቦታ / Space / ለየት የሚያረጉት ሁለት ባህሪያት አሉት፡፡ እንርሱም አውንታዊ አሉታዊ ናቸው (Negative or positive) ዉስጣዊና ውጫዊ ብታ ናቸው፡፡
አካባቢያዊ ቦታ የክወናና ዕይታ ጥበባት ፈጠራ የሆነውን ጥድፍ ወይም ቅብ በቀላሉማየት መረዳት እንድንችል ይረዳናል፡፡





ሥዕል :- አካባባዊ ቦታ

### 1.4.8. - ሕብረ ቀለም

እንደሚታወቀው አለማችን ስትፈጠር በብዙ ቢሊዮን ልዩ ልዩ ቀለማት ያሸበረቀችና የተዋበች ናት፡፡ በአካባቢያችን የምናያቸው ነገሮች ሁሉ ማለትም ተራራው ፣ወንዙ፣ ሽንተረሩ፣ ደኑ፣ ቤቱ፣ እንስሳቱ፣ አዋፍቱ፣ አራዊቱ፣ በየብስም ሆነ በባህር ያሉ ነፍሳት ልዩ ውበት አላቸው፡፡

በአጠቃላይ በምድር ላይ የሚገኘው ተፈጥሮና ሰው ስራሽ ነገሮች በሙሉ በልዩ ልዩቀለም ያሸበረቁ ናቸው፡፡የቀለማትን ባህሪና ምንነት ለማወቅ እነዚህን የቀለም ውህደት ማወቅ ተገቢ ነው፡፡





ሀ/ መሠራች ቀለማት / አንደኛ ደረጃ ቀለማት / primary colours /




ቀይ ቀለም፣ቢጫ ቀለም እና ሰማያዊ ቀለም አንደኛ ደረጃ ቀለማት ይባላሉ።

ለ/ ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት /secondarycolours/ቀይ ቀለም+ ቢጫ ቀለም= ብርትኳናማ ፣ ቢጫ ቀለም + ሰማያዊ ቀለም = አረንጓዴ ቀለም

ቀይ ቀለም+ ሰማያዊ ቀለም = ወይን ጠጅ ቀለም



ሐ/ ሦስተኛ ደረጃ ቀለማት / Tertiary colours /

ቢጫማ ብርትኳን ቀለም ፣ ቀይማ ብርትኳን ቀለም ፣ ቀይማ ወይን ጠጅ ቀለም ፣ ሰማያዊማ ወይንጠጅቀለም፣ ሰማያዊ አረንጓዴ ቀለም ፣ ቢጫማ አረንጓዴ ቀለም።



ዓላማ :- ቀለማትን ማብራራት

የመወያያ ጥያቄ

የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማት ስንት ናቸው ? ስማቸውስ?

መልመጃ

የሚከተሉትን ቁሳቁሶች በመጠቀም ተግባራዊ ልምምድ አድርጉ

ርዕስ፦ ቀለማት

ዓላማ፦ ከቀለማት ዉስጥ የተለያዩ የቀለም ዘሮችን መለየት
የሚያስፈልጉቁ ሳቁሶች፦

- የውሃቀለም
- የውሃ ቀለም ብሩሽ
- የውሃ ቀለም ወረቀት / ቻርት peper /
- የወረቀት ፕላስተር
- ሌሎች አማራጮች
- ከለር፣ፓስቴል . . . ወዘተ መጠቀም ይቻላል፡፡










የዉሃ ቀለም ብሩሽ እና የውሃ ቀለም የአሰራር ቅደም ተከተል

ያዘጋጃችሁትን የውሃ ቀለምና ብሩሽ ከንፁህ ውሃ ጋር ማቅረብ

- የምንስራበትን ወረቀት ለስራ ዝግጁ ማድረግ
- በብሩሻችን ቀለሞችን በውሃ ቀላቅለን የምንፈልገውን ሕብረ ቀለም ማቅለም
- ባዘጋጀነው ወረቀት ላይ መቀባት
- የፈለግነውን የቀለም ውህድ ማግኘታችንን ማረጋገጥ

መልመጃ ፦ ሁለት ለሚቀጥሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ::

1. የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማት ስንት ናቸው ?
2. ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ከመጀመሪያ ደረጃ ቀለማት በምን ይለያሉ ?
3. ቀለማትን ለመቀላቀል የሚያስፈልጉን ቁሳ ቁሶች/ማቴሪያል ምንድ ናቸው ?
4. ተፈጥሮና ቀለማት ያላቸውን ዝምድና ዘርዝሩ ?
5. ተማሪዎች በሕብረተሰቡ አካባቢ እየተዘዋወራችሁ የተሰቀሉ አመልካች ምልክቶችን፣ አርማዎችን፣ የተለጠፉ ማስታወቂያዎችን ቀለማትና ዲዛይን በትኩረት ጥናት አድርጉና ከክፍል ተማሪዎች ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ፍሬ ሀሳብ ለመምህራችሁ አቅርቡ::

መልመጃ ፦ ቀጥለው የቀረቡትን ትዕዛዛት በተግባር በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ::

1. የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማትን ቀቡ
2. ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ቀቡ

### 1.4.9.ሻካልሴ / ሻካራና ልስላሴ/

የአንድ ተፈጥራዊ ባህሪ መልክ ቅርፅ የምንለይበት መሰረታዊ የክወናና ዕይታ ጥበባት አላባዊያን መካከል አንዱ በሻካራና ልስላሴ በዓይን መለየት የሚያስችል ዘዴ ነዉ::

ምሳሌ፦ 1

ሀ/ የእውነተኛ ተፈጥሯዊ ባህሪያቸው ሻካራና ልስላሴን በአይን መለየት የሚያስችለን ዘዴ ነው።

ለሁለቱንም ያቀናጀ ሻካራነትንና ልስላሴን የያዙ ነገሮችን አይናችንን ብንዳስሳቸው

ሻካራውን ሻካራ ለስላሰውን ለስላስ እንደምንለው ሁሉ በአይናችንም መለየት የሚያስችለን ዘዴ ነው።






ሥዕል፦የሻካልሴ / ሻካራና ልስላሴ / Texture/

### 1.4.10.፦የንጣትና ጥቁረት ሂደት / value /

የቀለማትን ብርሃናማነትና ጥቁረት ሂደት የምንገልፅበት ዘዴ ነው። ይህም ማለት

በክውናና ዕይታ ጥበባት ሀሳብንና ስሜትን ለመግለፅ ትክክለኛ መልዕክትን ለማስተላለፍ የንጣትና ጥቁረት ሂደት / value / በጣም አስፋላጊ ነው።

ምሳሌ:- 2

ሀ/የምንስራውን ዕይታ ጥበብ ሰዓቱን ለመግለፅ በንጣትና በጥቁረት በሂደት /value /አይነተኛ ገላጭ ነው።

ለ/መልክን ለማስመስል ብርሃንና ጥላን ለመፍጠር የንጣትና ጥቁረት ሂደት /value / ሚናው የላቀ ነው።




ሥዕል፦ የንጣትና የጥቁረት መጠን / valve /

### 1.4.11ማጠን / proportion /

የንድፍ ሥራችን በሚያርፈባቸው ወረቀቶች ላይ የነገሮች መጠን በአይናችን እንደተመለከትናቸው በትክክል ተመጣጥኖ መቀመጥ አለበት። ይህም ዘዴ ማመጣጠን / proportion / በመባል ይታወቃል።



ሥዕል፦ማመጣጠን/ Proportion /

ከላይ በሥስዕሉ እንደሚታየው ጎን ለጎን የተቀመጡ ቁሶች መጠናቸው ተጠብቆ ትልቁ ከትንሹ ያለው ልዩነት በተመዛዘነ መልኩ የተቀመጠ ነው።የመጠን አሰራር ዘዴ የሰውና የእንስሳት፣የነገሮች

የሰውና የእንስሳትና በአካባቢያችን ያሉ ነገሮች የተለያየ መጠን አላቸው። እነዚህን ነገሮች በተናጠልም ሆነ በቅንብር በሥዕል ስራችን ስናስቀምጥ ሁሉም መጠናቸው ተጠብቆ ከተሰራ ሥራው እውነተኛ ገፅታን ከማንፀባረቁም ሌላ ውበትም ይኖረዋል።

የአሰራር ቅደም ተከተል

- ሰዎች፣እንስሳትና የተለያዩ ነገሮች በአንድነት ከሚታዩበት ቦታ በመሔድ የመጠን መለያየትና መቀራረብን ተመለከቱ።
- በምን ዘዴ ተጠቅማችሁ መጠናቸውን እንደምትለኩና በንድፍ ወረቃታችሁ ላይ እንደምታስፍሩት የተቀመጠላችሁን ምሳሌ በትኩረት ተመልከቱት፡-





ሥዕል፦ የሰውና እንስሳት ምጣኔ ዘዴ / proportion /

ተግባር፦ የቡድን ወይይት

ዓላማ - የመጠን / Proportion / ፍቺ መግለጽ

የመወያያ ጥያቄ = በንድፍ የምትስሩዋቸው ነገሮች የተለያዩ መጠን አላቸው የእነዚህን ነገሮች መጠን ጠብቆ በትክክል ለማስቀመጥ ምን ማድረግ እንደሚገባችሁ በቡድን በመወያየት የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

የክለሳ ጥያቄዎች

መልመጃ፡-3

ሀ ፡-ለሚቀጥሉት ጥያቄዎች አጭር ምልስ ስጡ።

1 ሻካ ልሴ / ሻካራና ልስላሴ የሚያሳይ አንድ ከሻካራ አንድ ከለስላሳ ጥቀሱ።

2 ሁለቱንም ያቀናጃ ሻካራነትንና ልስላሴን የያዘ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ቁሶችን ዘርዝሩ።

3 በዕይታ ጥበባት ዉስጥ መጠንን እንዴት ተረዳችሁት?

4 እውነተኛ ገፅታንና ውበት ያለው የሥዕል ስራ ለመስራት የሚያግዙን ዘዴዎች የትኞቹ ናቸው?

ለ የሚሰሩ ተግባራት

1 ሻካልሴ/ ሻካራና ልስላሴን በእርሳስና ወረቀት አንስቶ በተለያዩ ቁሳቁሶች ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

2 ትክክለኛ ምጣኔ ያለዉ ቁስ ከወረቀቱ ጋር አመጣጥናችሁ በእርሳስሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

### 1.1.12 ሐረግ

የሐርግና የሥዕል ሥራዎች ከድንጋይና ከእንጨት ቅርፃ ቅርጽ ጋር ተመሳሳይነት ስላላቸው ። ለታሪክ ማስረጃ ከከርሰ ምድር እየተቆፈሩ የሚወጡት በሥነ ስብእ ምሥሎች የጥንት ሰዎች የቤት መስሪያ መገልገያ ዕቃዎችና የድንጋይ ሐውልቶች ላይ ተቀርጸው ይገኛሉ ።







1ኛ



2ኛ



3ኛ



4ኛ



ስዕል፡-2

5ኛ



ስዕል፡-3

## ሥዕል፡-የሐርግ ሥራ

በመሆኑም ከግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ግኙት የበለጠ ዕድሜ ያላቸው ይመስላል ። የሐርግ ሥራን ዕድሜ የምንገመግመው በሀገራችን ልዩ ልዩ ሐውልቶች ዕድሜ ጋር በማገናዘብ ነው ። ከክርስቶስ ልደት በፊት እራቅ ባሉት ዘመናት የተቀረጹት ምሥሎችሐውልቶች ሐረግ የታየባቸው ሲሆኑ አንዳንዶቹም የሳባ ሥነ ጽሑፍ ሰፍሮባቸዋል።የሐረግ ሥራን ዕድሜ የምንገመግመው ከሀገራችን ልዩ ልዩ ሐውልቶች ጋር በማነፃፀር ነው ።



ስዕል፡-4



ሥዕል፡-የሐርግ ሥራ

የሐርግና የሥዕል ሥራ ከቁም ጽህፈት ሙያ አንዱ ክፍል ሲሆን ብዙ ተማሪዎች ለሐረግ ሥራና ለሥዕል ትምህርት አይጨነቁም ። መምህራኑም እነዚህን ሙያዎችለተማሪዎቻቸው ለማስተማር ያላቸው ፈቃደኝነት ቀዝቃዛ ነው። ተማሪዎችም የሐረግአጣጣል ከመምህሩ የሚማረው ጠንካራና ስልቱ ካልሆነ ብቻ ነው ። የሐረግ ሥራየዕለት ከዕለት ልምምድ ስለሚጠይቅም መምህሩም ቢሆን ሐረግ በሚሥልበት መጽሐፍ ላይ በቀጥታ መሳል አይጀምርም ። በአንድአነስተኛ ብራና ላይ ከነደፈ በኃላ ንድፍ ከተዋጣለት በአዲሱ መጽሐፍ ላይ ያስፍረዋል ።

## የምዕራፍ 1 ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ሙዚቃ አላባዊያን ምንነት ያየን ሲሆን የሙዚቃ አላባዊያን የምንላቸው ፡- ስልተ ምት፣ ኃይለ ድምፅ፣ ቴምፖ፣ የክረት መጠን፣ ዜማ፣ ህብረ ድምፅ፣ የድምፅ ቀለም፣ የጊዜ ቆይታ እንደሆኑ አይተናል፡፡ እንዲሁም የውዝዋዜ አላባዊያን የምንላቸው የሰውነት ቅርፅን መሰረት ያደረገ አቋቋም፣ የቦታ አያያዝና አጠቃቀምና ከአጣማሪ ጋር እንቅስቃሴ ማቀናጀት የሚሉ ይገኙበታል፡፡ መሰረታዊ የትያትር አላባዊያንም ስለምንላቸው ያየን ሲሆን እነዚህም ከዋኞች /ተዋኒያን/፣ ተደራሲያን /ታዳሚያን/፣ አዘጋጅ፣ የመከወኛ ቦታ /መድረክ/፣ ጥበባዊ ግብአቶች፣ ጽሁፈ ተውኔት፣ እንደሆኑ በግልፅ ያየን ሲሆን የመዋቢያ ግብዓቶችን ተጠቅመን ቲያትር ለመስራት ሞክረናል፡፡

የዕይታ ጥበባት አላባዊያን የምንላቸው ደግሞ መስመር፣ ቅርጽ፣አካባቢያዊ ቦታ፣ ህብረ ቀለም፣ሻካራና ልስላሴ፣ ንጣትና ጥቁረት፣ መጠንና ሐረግ እንደሚባሉና ስለ ቀላል የቪዲዮአቀራረፅ ዘዴዎች ወይም የቅርብ ዕይታ ቀረፃ፣ የመካከለኛ ዕይታ ቀረጻ የመካከለኛ ዕይታ ቀረፃ የሩቅ ዕይታ ቀረፃ እና አጠቃላይ ዕይታ ቀረፃ እንደሆኑ ተረድተናል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ፈጠራን መግለፅ

### የምዕራፍ ሁለት መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ላይ በዋናነት ክ.ዕ.ጥን በመጠቀም ፈጠራን የምንገልፅበት ምዕራፍ ሲሆን በውስጡ የተካተቱ ይዘቶችም በዋናነት የሙዚቃ ኖታዎችን መፃፍና ስያሜያቸውን መጥራት፣ ስብስብ/staff/፣ የሙዚቃ መስመርና ክፍት ቦታ መሰየሚያዎች፣ ድንገተኛ ምልክቶች የጊዜ ቆይታ፣ በውዝዋዜ እንቅስቃሴ የሙዚቃ ድምፆችን መግለጽ፣ አልባሳትንና የመዋቢያ ግብኣቶችን ተጠቅሞ ትያትር መስራት፣ የገፅ ቅብና የመዋቢያ ግብአቶችን የወረቀት ሞዛይክና ዝግ ህትመት እና ስለ ማጣበቂያ አሰራር በዝርዝር በተግባር የምንሰራበት ምዕራፍ ነው፡፡

## 2.1 የሙዚቃ ኖታዎችን መፃፍና ስያሜያቸውን መጥራት

**ከተማሪዎች የሚጠበቀው  የመማር ውጤት**

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፦

- ሰባቱን የሙዚቃ ሆሄያትና ድምፆች ትለያላችሁ
- ሆሄያቱን በመዝሙር ከድምፃቸው ጭምር ትለያላችሁ
- የሙዚቃ ሰሌዳን መለያ  ቁልፎችን ተረዳላችሁ
- የመስመርና ክፍት ቦታዎችን ስም ትለያላችሁ
- ሆሄያትንና ድምፆችን ትለያላችሁ

ሆሄያትና የሙዚቃ ድምፆች:-ሰባቱ የሙዚቃ ተፈጥሯዊ ድምፆች በሰባቱ የእንግሊዝኛ ሆሄያትና በሰባቱ የላቲን ሆሄያት ይጠራሉ፡፡



| በእንግሊዘኛው | C | D | E | F | G | A | B | C |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በሆሄያት | ዶ | ሬ | ሚ | ፋ | ሶል | ላ | ሲ | ዶ |
| በላቲን | DO | RE | MI | FA | SOL | LA | SI/TI | DO |

ሰባቱን በሆሄያትና በላቲን ክፍለ ቃላትን ድምፆች በመዝሙር በቀላሉ ማሳወቅ

DO -ዶ - ሁሉም ሰው ተዋዶ

RE -ሬ- ሀገሬ ናት ክብሬ

MI - ሚ - አብቢ ለምልሚ

FA -ፋ - እውቀት ይስፋፋ

SO(SOL) - ሶል- ሁሉም ለማገልገል

LA- ላ - እንበል ወደኋላ

SI(TI) - ሲ - በእድገት ገስግሺ

በማለት ሙዚቃን እንማራለን

ከእዚህ በታች በኖት የተፃፉትን የሰባቱን የሙዚቃ ድምፆች ፊደላት ኖታዎችን ዜማ በተራ ለምዘመር በቅድሚያ ኖቱን ማንበብ ስልተምቱን እንዲያውቁና ዜማውን ለመያዝ ቃላቶችን በትክክል መረዳት ያስፍለጋል፡፡




## Music Alphabet Song

ግጥምና ዜማ ፦ መምህር ጥበቡ ወልደዮሐንስ



## 2.2.ስብስብ (Staff)

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የሙዚቃ ስሌዳን ታውቃላችሁ፡፡
- የመስመርና ክፍት ቦታዎችን ትለያላችሁ፡፡

የአምስት ትይዩ መስመርና የአራት ክፍት ቦታዎች ጥርቅ ስብስብ (ስታፍ) ይባላል፡፡ ስብስብ የሙዚቃ ምልክቶች መፃፊያ ቦታ ሲሆን አቆጣጠሩም ከታች ወደ ላይ ነው፡፡




የመስመር የክፍት ቦታ የቁጥር ስያሜ

የድምፅ ኖታ ራስ በስታፍ ላይ ሲፃፉ



**ረዳት መስመሮች** (Ledger Lines) ከስታፍ በታችና በላይ የሚፃፉ አጫጭር መስመሮችናቸው ከላይ የሚፃፉት የድምፁ ክረት ቀጭን መሆኑን ያመለክታሉ:: ከታች የሚፃፉት የድምፁ ክረት ወፍራም መሆኑን ያመለክታሉ:: ረዳት መስመሮቹ ብዛት የተወሰነና የተገደበ አይደለም:: እንደመሳሪያዎች የድምፅ ደረጃ ይወሰናል:: የመስመሮቹ አፃፃፍ ስታፍን መስመር ክፍት ቦታእያልን እንዳስቀመጥን ይሆናል::




**ግሬትስታፍ** (Great staff grand staff) ሁለቱ ስብስቦችን በአንድነት አጣምሮ የያዘ ስብስብ ነው:: የምንጠቀምባቸው በተለይም ለፒያኖ ሙዚቃ መሳሪያና ለህብረ ሙዚቃ ቅንብር (harmony) የሚያገለግል ስብስብ ነው::



### 2.2.1.የሙዚቃመስመርናባዶቦታመሰየሚያዎች (clefs)

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራች ሁካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ሆሄያትንና ድምፃችን ትለያላችሁ
- የሙዚቃ ሰሌዳን ታውቃላችሁ
- የመስመርና ክፍት ቦታዎችን ስያሜትለያላችሁ

በስታፍ በስተግራ በኩል የሚፃፉ ቁልፍ ምልክቶች ድምፃች በስታፍ ላይ የሚኖራቸውን ቦታ አመልካቾች ሲሆን በኖታ ምልክቶች ድምፃችን መለየት የሚያስችለን ምልክቶች ናቸው፡፡

ሀ/ የትሬብል (G) ቁልፍ ከሁለተኛው መስመር ላይ የሚጀምር (ይሚጠቀለል) ለቀጭንና ለመካከለኛ ቀጭን ድምፅ (ሶፕራናአልቶ) የሚፃፍ ምልክት ሲሆን የአፃፃፍ ቅደም ተከተሉ ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ላይ በቀረበው መሰረት ይሆናል፡፡






የስብስብ መስመርና ክፍት ቦታዎች ስም

| መስመር | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 5ኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| በእንግሊዘኛው | E | G | B | D | F |
| በላቲን ሆሄ | ሚ | ሶል | ሲ | ሬ | ፋ |

በቀላሉ በእንግሊዘኛው ዓረፍተ ነገር እንዲለዩ

Every Good Boy Deserves Fudge

Empty Garbage Before Dad Flips

Elephant Go Backwards Down Freeways

| ክፍትቦታ | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
|---|---|---|---|---|
| በእንግሊዘኛው | F | A | C | E |
| በላቲን ሆሄ | ፋ | ላ | ዶ | ሚ |

F A C E

Fating AllWays Causes Enemies

Frequent Asking Can Enlighten

ለ/ ቤዝ (F) ቁልፍ ከአራተኛው መስመር ላይ የሚወሰን ለወፍራምና ለመካከለኛ ወፍራም ድምፅ (ቴኖር ቤዝ) የሚፃፍበት ቁልፍ ነው።






| መስመር | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 5ኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| በእንግሊዘኛ | G | B | D | F | A |
| በላቲን ሆሄ | ሶል | ሲ | ሬ | ፋ | ላ |

Good Bubbles Do Fizz Always

Great Big Dinosaur's Fight Always

Goofy BabiesDoFunny Acts

| ክፍትቦታ | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
|---|---|---|---|---|
| በእንግሊዘኛ | A | C | E | G |
| በላቲን ሆሄ | ላ | ዶ | ሚ | ሶል |

A Cats Eyes Glow

All Cows Eat Grass

All Cars Eat Gas

## መልመጃ አንድ

1.ከዚህ በታች በስብስብ ላይ የተፃፉትን የድምፅ ኖታዎች የክረት ስም ፃፉ::





2. ሙሉ የድምፅ ኖት ምልክትን በስታፉ በትክክለኛው ቦታ ላይ ፃፍ::



A C G F B G D E D B



E F D G C A B G A C

3. ሙሉ የድምፅ ኖትን ከስታፉ በላይ በረዳት መስመር ላይ ፃፍ::



G B A D C B D C E F

4.ሙሉ የድምፅ ኖትን ከስታፉ በታች በረዳት መስመር ላይ ፃፍ




### 2.2.2.የድንገተኛ ምልክቶች (Accidentals sign)፡-

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ምልክቶችን ትለያላችሁ፡፡
- የሚቀይሩትን የድምፅ ደረጃ ትለያላችሁ፡፡

ድንገተኛ ምልክቶች (ድንገተኛ የክረት ለዋጭ ምልከቶች) አጋጣሚ ምልክቶች ሲሆኑ ከኖታው ፊት ለፊት የሚፃፍ ድምፅን በግማሽ ወይም በሙሉ ሊቀጥኑ ወይም ሊውፍሩ የሚችሉ ምልክቶች ናቸው፡፡

| ምልክቶች | እንግሊዘኛ | በአማርኛ | የሚፈጥሩት የድምፅ ለውጥ |
|---|---|---|---|
| ♯ | Sharp | ሻርፕ (ቅጥን) | በግማሽ ደረጃ ማቅጠን |
| ♭ | Flat | ፍላት (ውፍር) | በግማሽ ደረጃ ማወፈር |
| 𝄪 | Double sharp | ድርብ ሻርፕ (እጥፍ ቅጥን) | በሙሉ ደረጃ ማቅጠን |
| 𝄫 | Double flat | ድርብ ፍላት (እጥፍ ውፍር) | በሙሉ ደረጃ ማወፈር |
| ♮ | Natural | ወደ ዋናው መመለሻ (ተፈጥሯዊ) | ወደ ዋናው (ወደተፈጥሯዊው) ክረት መመለስ |

በሻርፕ ናፍላት

በድርብ ሻርፕና ፍላት




ኢንሃርሞኒክ ኢኩቫለንት አንድን ክረት ለመጥራት የሚያገለግሉትን የተለያዩ ስሞችን ያምልክታል፡፡

| | |
|---|---|
| C# = D♭ | C𝄪 = D |
| G# = A♭ | D𝄫 = C |
| D♭ = C# | E𝄪 = F# |

### 2.2.3. የጊዜ አመልካች (Time signature)

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ምልክቶችን በመለየት የምት ዋጋ ታውቃላችሁ፡፡
- በባር/በሙዚቃ ክፍል/ ውስጥ ያለውን የኖት ብዛት መጠን ታውቃላችሁ፡፡

የጊዜ አመልካች፡-በስታፍ ላይ ከክሌፍ ቀጥሎ የሚጻፍ ሲሆን ኖታ ምልክቶችን በእኩል ዋጋ በማከፈል ስሌት ይገለጻል ፡የላይኛው ቁጥር በባር ውስጥ ለሚገኙ የሚገባቸውን የኖታዎችን ብዛት ሲነግረን የታችኛው ቁጥር የኖታዎችን አይነት ይገልፃል፡፡

| ምልክት | ያለው የጊዜ ዋጋ | በባር ሊገኝ የሚገባ ኖታ ዋጋ |
|---|---|---|
|  4 4 C "ኮመንታይም) | በአንድ ባር አራት ምት |  |
|  2 4 | በአንድ ባር ሁለት |  |
|  3 4 | በአንድ ባር አንድ ወይም ሶስት ምት |  |
|  6 8 | በአንድ ባር ሁለት ምት |  |

**የባር መስመር(Barline) :** የሙዚቃ ኖታዎችንና የእረፍት ምልክቶችን በጊዜ አመልካች የዋጋ ስሌት በኩል ዋጋ የምንከፋፍልበት ቅዋሚ መስመር ነው። ባር (Bar or measure) በሁለት ቅዋሚ መስመር መካከል ያለው ክፍት ቦታ ነው። ድርብ የባር መስመር (Double bar line) ሙዚቃው ተፅፎ ሲያበቃ በመዝጊያ የሚፃፍ ነው።




የመድገም ምልክቶች ሙዚቃው ተፅፎ ዜማን ለመድገም የሚያስፈልግ ሆኖ ከተገኘ ከዚህ የሚፃፉ ምልክቶች ናቸው።




## 2.3 በውዝዋዜ እንቅስቃሴ የሙዚቃ ድምፆችን መግለጽ

ሰባቱን የሙዚቃ ድምፆች በኣከልና በእጅ እንቅስቃሴ መዘሙር መቻላችሁ ክፍተኛ እገዛ አለው። አትኩረት እንዲኖራቸው ከፍተኛ እገዛ አለው።

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርትተምራችሁካጠናቀቃችሁበኋላ፡-

- ሰባቱን የሙዚቃ ሆሄያትና ድምፆች በእጅ እንቅስቃሴ ትለያላችሁ

ሰባቱን የሙዚቃ ሆሄያትና ድምፆች በእጅ ምልክት መለየት




## 2.4.አልባሳትንና የመዋቢያ ግብአቶችን ተጠቅሞ ቲያትር መስራት

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ስለአልባሳት ምንነት ትረዳላችሁ።
- የአልባሳት አይነቶችን ትለያላችሁ።
- የገፅ ቅብ ምንነት ታውቃላችሁ።
- የገፅ ቅብ ጠቀሜታዎችና የገፅቅብ ባለሙያዎች በመረዳት አጭር ድራማ ትሰራላችሁ።

ልብስ የሰው ልጆች እርቃነ ስጋቸውን የሚሸፍኑበት፤ ከብርድና ከፀሀይ የሚከለሉበት እንዲሁም ገላቸውን ከጉዳት የሚጠብቁበት ሲሆን እግራቸው ላይ ከሚያደርጓቸው ጫማዎች እራሳቸው ላይ እስከ የሚያደርጓቸው የተለያዩ ኮፍያዎች ጭምር ያካትታል። ስለ ጥበባዊ አልባሳት ስናነሳ ግን ከምናውቃቸው አልባሳት በተጨማሪ በእኛ ዘመን ሲደረጉ አይተናቸው ስለማናውቃቸው አልባሳት ማለትም በድርሰቱ ታሪክ ውስጥ ስለተጠቀሱ ዘመናት የሚገልጹ በድሮ ጊዜ ተደርገው ስለነበሩ ወይንም ተደርገው ስለማያውቁ እና ወደፊት ይደረጋሉ ተብለው ስለሚታሰቡ ወይም በማናውቃቸው ገጸ-ባህርያት በማናውቀው ቦታ ላይ ደራሲው በጠቀሰው ወይም ዳይሬክተሩ በፈጠረው ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የሚለበሱ አልባሳትን የሚያጠቃልል ነው።

እነዚህ አልባሳት ገጸ-ባህርያትን የሚገልጹ ሲሆን፡-

ገጸ-ባህሪው፡ የሚኖርበትን ዘመን

- የሚኖርበትን ቦታ
- የአየር ንብረት ሁኔታ
- እድሜውን
- ጾታውን
- የገቢና የኑሮ ሁኔታውን (ማህበራዊ ደረጃውን)
- ማንነቱን፣ ባህሉን፣ ስሜቱን፣ እምነቱን እና
- የጤና ሁኔታውን በመግለጽ በደንብ እንድንረዳው ያደርገናል፡፡

ምሳሌ፡ ገጸ-ባህሪው የአዕምሮ ችግር ያለበት ቢሆን የተቀዳደደና የቆሸሸ ልብስ እንዲሁም የተቦጫጨቀኮፍያ እና የተለያዩ የማይጠቅሙ ነገሮች ብናስይዘው በቀላሉ የአዕምሮ መቃወስ እንደገጠመው እንገነዘባለን፡፡

የተለያዩ አልባሳት አይነቶች ሲኖሩ በዘመኑ የነበረውን የፈጠራ ጥበብ፣ የቴክኖሎጂ ደረጃ፣ በዘመኑ የነበረውን ፋሽንና ስልጣኔ ለማሳየት የሚያገለግል ሲሆን የማህበረሰቡን ማንነት እና የኑሮ ሁኔታም ይገልጻሉ፡፡

## ባህላዊ አልባሳት

ባህላዊ አልባሳት የአንድን አገር፤ አካባቢ ወይም ማህበረሰብ ባህል፣ ወግ፣ ልምድ፣… የሚያንጸባርቁ አልባሳት ሲሆኑ በተለያዩ ክዋኔዎችና ስርዓቶች የሚለበሱ ሆነው የማህበረሰቡን እሴቶች እና ስሜቶች ለማሳዎቅ ይረዳሉ፡፡

በስራ ወቅት ማለትም፡ በእርሻ፣ ውቂያ፣ አረም፣ ሰብል ስብሰባ ጊዜ ልዩልዩ አልባሳትን ይጠቀማሉ፡፡

በሰርግ ወቅት የተለያዩ ጌጣጌጦች የተለበጡና የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ እሳቤዎች የሚወክሉ አልባሳት ይዘወተራሉ፡፡

በሃዘን ወቅት ስሜታቸውን የሚገልጹ የአለባበስ ዘዴዎች የተለየ ቀለም ያላቸው ልብሶችን ይጠቀማሉ፡፡

የክብረ በዓላት አለባበስ ስንመለከት ደግሞ እንደየበዓሉ አከባበር ሁኔታና አካባቢያዊ ልማድ የተለያዩ አልባሳት በተለያዩ የአለባበስ ስልቶች ጾታ እና እድሜን በሚወክልመልኩ ይለበሳሉ፡፡

### ሀይማኖታዊ አልባሳት፡

እነዚህ አልባሳት በአንድ ሀይማኖት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች እንደየ ስልጣናቸውና ማንነታቸው የተለያዩ መለያዎች ያሏቸው አለባሳት የሚለበሱ ሲሆን የሀይማኖቱ ተከታዮችም ሀይማኖታቸውን የሚገልጹ የአለባበስ ስርዓቶችን ይከተላሉ፡፡

ምሳሌ፦ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ውስጥ ያሉ አገልጋዮችን ብናይ የቄስ፣ የመርጌታና
ድያቆን አለባበስ ይለያያል፤ ራሳቸው ላይ የሚደረገው ጥምጣም መጠንም ይለያያል፡፡

### ሙያዊ አልባሳት

የስራ ላይ ልብሶችን ስናነሳ የተለያዩ ሙያዎች ላይ ያሉ ሰዎች የሚለብሷቸው ና ማንነታቸውን የሚገልጹ የደንብ ልብሶች ሲሆኑ እነዚህ አልባሳት የራሳቸው የሆነ ሙያዊ ደረጃን የሚገልጹ መለዮዎች ያሏቸው ናቸው፡፡

ምሳሌ፦ የፖሊስ

የወታደር

የህክምና ባለሙያዎች

የመምህራን

የስፖርተኛ … ወዘተ. አልባሳትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

### ዘመናዊ አልባሳት

እነዚህ አልባሳት ዘመን አመጣሽ አልባሳት ሲሆኑ በሆነ ወቅት እንደ ስልጣኔ ደረጃቸውና የቴክኖሎጂ ግብዓቶች የተለያዩ አልባሳት በተለያዩ ዘመናት የሚፈጠሩ ሲሆን በቋሚነት የማይዘለቁና በየጊዜው የሚለዋወጡ አልባሳት ናቸው፡፡ እነዚህ አልባሳት የተለያዩ የአሰራር ጥበባትን እና የአለባበስ እስታይሎችን የሚያካትቱ ሲሆኑ በእድሜ፣ በጾታ፣ እና በስልጣን ደረጃ ሊከፋፈሉ ይችላሉ፡፡ ወቅትን መሰረት አድርገው የሚለበሱ አልባሳትንም የሚያጠቃልል ሲሆን በጸሀይ ወቅት የሚለበሱ፤ በብርድና ዝናብ ወቅት የሚለበሱ፤ የእራት ልብስ፣ የምኝታ ልብስ፣ የምርቃት ልብስ፣ የልደት ልብስ… እያልን ልንከፋፍላቸው እንችላለን፡፡

## 2.5. የገጽ ቅብና መዋቢያ ግብዓቶች

የገጽ ቅብና መዋቢያ ማለት አካላዊ ገጽታን የሚቀይርና ከተለመደው ማንነት ልላ ገጽታ የሚያላብስ ሲሆን የተክለሰውነት ለውጥ ለማምጣት ተብሎ የሚደረግና ትልቅ ጥበባዊ ፋይዳ ያለው ነው፡፡ የገጽ ቅብና መዋቢያ ተዋንያን የተለያዩ ገጸ-ባህርያትን ለመወከል (ተክቶ ለመስራት) ልዩልዩ የእድሜ፣ የኑሮ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እንዲሁም የስራ ሁኔታዎችን ለማምጣትና ለመግለጽ ያገለግላሉ፡፡ የሰውነት ቀለም፣ መጠንና ድሎት ወይም የጉዳት ሁኔታ ከማሳየት በተጨማሪም ሌሎች ግብዓቶችን በመጠቀም ከስብዕና አውጥቶ ሌላ ፍጡር የማስመሰል አቅም አላቸው፡፡

ምሳ. ሽማግሌን ወጣት፤ መላጣን ጎፈሬ፤ ጥቁር ነጭ፤ ሰውን አውሬ ወይም ሌላ የማይታወቅ ፈጡር፤ ጤነኛን የአካል ጉዳት እንደደረሰበት ማስመሰል ይችላሉ፡፡

ለመዋቢያ የምንጠቀምባቸው ቁሳቁሶችም ሆነ ቀለማት በሰው ላይ ጉዳት የማያደርሱ እና በቀላሉ የሚለቁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ይህንን ተግባር ለመከወን የተለያዩ ባለሙያዎች የሚሳተፉ ሲሆን የገጽ ቅብን የሚሰራ ባለሙያ፤ የጸጉር ስራ ባለሙያዎች፤ በእጃቸው የሚጠቀሙበት ወይንም በሰውነታቸው ላይ የሚደረግን ቁሳቁስ የሚያዘጋጅ ባለሙያ፤ እንዲሁም ስለሚቀቡና ስለሚደረጉ ነገሮች የኬሚካል ይዘት እና የጉዳት ደረጃ የሚያውቅ የህክምና ባለሙያዎች አሉት፡፡

የገጽቅብ ባለሙያ የስዕል ችሎታ ያለው፤ የቀለማትን ቅንብር በደንብ የሚረዳ፤ የፊት ገጽታን፣ የቆዳ አይነትን፣ እና የተክለ ሰውነት ሁኔታን በቂ በሆነ መልኩ የሚያውቅ ሰው መሆን ይኖርበታል፡፡

የገጽ ቅብና የመዋቢያ ቁሳቁሶች ለጥበብ ስራ የተለያዩ ጠቀሜታወዎችን የሚሰጡ ሲሆን ስለ ድርሰቱ ገጸ- ባህርያት፡-

-ማንነት ይገልጻሉ

-ባህርያቸውንና ስሜታቸውን ለማሳየት ይረዳሉ

-የኢኮኖሚ ደረጃቸውን ያሳያሉ

-ታሪኩ የተፈጠረበትን ጊዜ ያመላክታሉ

-የቴክኖሎጂ እድገት ደረጃን ያሳውቃሉ

-የፈጠራ ችሎታቸውን

-የአውቀት ደረጃቸውን

-ስራቸውን

-ስልጣኔያቸውን

-የአምልኮ ስርዓታቸውን

-ባህላቸውን

- እምነታቸውን…ወዘተ. በመግለጽ ምንነታቸውን፣ ከሰው ጋር ያላቸውን ግንኙነት፣ እንዲሁም የሚኖሩበትን ቦታና ሁኔታ ለማሳየት የሚጠቅሙ ዋነኛ ግብዓቶች ናቸው፡፡

## የመልመጃ 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሃሰት በማለት መልሱ

1. አለባበስ የአየር ንብረትን መግለጽ ይችላል፡፡
2. በአለባበስ የአንድን ማህበረሰብ ባህል መግለጽ አይቻልም፡፡
3. የገጽ ቅብ የሰውን መልክ መቀየር አይችልም፡፡
4. የገጽ ቅብ ስራ ላይ የህክምና ባለሙያ ይሳተፋል፡፡

የሚከተለው ከቤቶች የቴልቪዥን ድራማ ላይ የተወሰደን ጽህፈተ ተውኔት ተማሪወች አልባሳት እና የገጽ ቅብን ተጠቅማችሁ ስሩ፡፡

Scene 1

ውስጥ-ዋናው ቤት ውስጥ

ቀን-የዕረፍት ቀን ቀትር ላይ

አዛሉ እና ዘሩ ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው ይመካከራሉ፣ሌላኛው ክፍል ውስጥ ማፊ፣በዜ

እና እርስቴ በር ላይ  ተለጥፈው ለመስማት ይታገላሉ፡፡

አዛሉ፦

በጣም አጠፋህ! በጣም አጥፍተሃል

ዘሩ፦

ምን ላድርግ አዛልዬ?

አዛሉ፦

እንዴት ምን ላድርግ? ከገዛህ ለሁሉም ነው       አለበለዚያ ደግሞ

አለመግዛት ይሻላል!

ዘሩ፦

አዛልዬ ዋጋው እኮ ........

በመሃል ይበቃል ሲገባ ሁሉም ወሬ ይቀይራሉ

ዘሩ፦

አዎ አዛልዬ እውነትሽን ነው፣አሜሪካ በጣም ታምራለች፣አዛሉ

አንድ ቀን እና ያታለን፣

ደቤ፦

እንዴ! ማሚ አሜሪካ እዚህ ልትመጣ ነው?ዘሩ

ቀልደህ  ሞተሃል!ይበቃል እየሳቀ ወደ ሌላኛው ክፍል ይገባል፣

ዘሩ፦

ሆሆ አሜሪካ ልትመጣ ነው ይላል? እና አዛሉ ዋጋው ውድ ስለሆነ አንድ የእጅሰዓትብቻ ነው የገዛሁት፣

አዛሉ፦

እሺ ለማን ልትሰጠው ነው?ለአንደኛው ብሰጠው አንደኛው ይከፋዋል፣ዘሩ ልጆቹን ማመለየት ተገቢ አይደለም፣አዛሉ እኮ ምን ልታደርግ አሰብክ?...(ትስቃለች)ዘሩምን .... ምነው? ምንያስቅሻል?

አዛሉ፦

አ...ይ (በራሱ ድምፅ) አዛልዬ ይኸውልሽ ለልጆቼ ምርጥ የእጅ ሰዓት አመጣሁኝ (በራሷ ድምፅ) ስትለኝ እኮ የመሰለኝ 4 የእጅ ሰዓቶችያመጣህ እንጂ....

ዘሩ፦

(ቆጣብሎ) አዛልዬደሞ! ያውታዲያ አመጣሁ አይደል?

አዛሉ፦

አንድ ብቻ? እንዳንባሻ እየቆረሱ እንዲካፈሉ ነው? ወይስ... ሆሆ... ሜትር ከሃምሳ አልጋ አረከው እንዴ 1 የእጅ ሰዓት ለ4 ?

ዘሩ፦

እኔ እኮ አዛልዬ ይህንንም የገዛሁት ገና ሳየው ስለወደድኩት ነው፣እሱም አንድ ብቻውን ነበር በዚያ ላይ ዋጋው!

አዛሉ፦

ይልቅ አሁን ለማናቸው እንስጥ? እንዴት?

ዘሩ፦

ዘዴ አይጠፋም፣

አዛሉ፦

እኮ ተናገሩ፣

ዘሩ፦

እ...... እ....... እ

አዛሉ፦

በቃ ዘርዬ እንዲህ እናድርግ ልጆቹ ይጠሩና ራሳቸው ይወስኑ፣

ዘሩ፦

አይሆንም አዛሉ።

አዛሉ ፦

ይሆናል፣

ዘሩ፦

ተይ!

አዛሉ፦

ግድ የለህም .... ልጆች .... ደቤ ..... ማፊ ...... ኧረ ልጆች፣

የሌላኛው ክፍል በር ድንገት ይከፈትና ይቤ ይወድቃል ይቤላይ በዜ፣በዜ ላይማፊ፣ማፊ ላይ እርስቴ ተደራርበው ይወድቃሉ አዛሉና ዘሩ በሁኔታቸው ተገርመው ዝም

ይላሉ።ሁሉም ተነስተው ልብሳቸውን ያራግፋሉ።

ዘሩ፦

ምንድን ነው እንደዚህ እንደበግግርርር ማለት?

ይቤ፦

አባቢ ሁላችንም ስንጠራ እኮ ምን መጣብለን።

ዘሩ፦

አይደል? ምን መጣብላችሁ ደንግጥአላችሁ አይደል?

አዛሉ፦

አሁን ወደ ዋናውጉ ዳይ፣

ይቤ፡-

ወደ ገደለው….አዛሉ

እንግዲህ ምን መሰላችሁ? አባታችሁ ከአሜሪካ ሲመጣ ምርጥ በጣም ምርጥ የእጅ ሰአት ይዞ ነው የመጣው፣

በዜ፡-

ወንዳታ! የታለ?

ዘሩ፡-

(ኪሱእየገባ) አትንቀዥቀዥ

ዘሩ ሰአቱን ከኪሱ እያወጣው ልጆቹ በአድናቆት አፋቸውን ይከፍታሉ፣

ዘሩ፡-

ይኸውላችሁ …….

በዜ፡-

አንድ ብቻ!?ዘሩአዎ አንድ ብቻ

በዜ፡-

ታዲያ አንድ ብቻ ይዘህ ከመጣህ አይቀርለምን የግርግዳሰአት …

ዘሩ፡-

ግድግድያርግህ አንተ!

አዛሉ፡-

እንግዲህ እንደም ታዩት አባታችሁ አንድ የእጅ ሰአት ለ4 ልጆች ይዞ መጥቶአል…

በዜ፦

ቆይ ግን ከዚህ በህኃላ የዚህ ሰአት ባለቤት ማነው?

ማፊ፦

(ለመቀበልጠጋብላ) እስቲ እስቲ ልየው፣

ዘሩ፦

ማየት አይቻልም

(ማፊ አኩርፋ መለስትላለች)፣

አዛሉ፦

ማፊዬ አትከፊ የኔማር እንደልብታይዋለሽ፣

እርስቴ፦

እማሚ..... አካቢ..... አሁን ይህን ሰአት ለማን ለመስጠት ነው ያሰባችሁት?

ይቤ፦

እርስቴ፦

የቤቱ ትልቅ ልጅ ማነውና?

ሁሉም ይንጫጫሉ ይጨቃጨቃሉ ዘሩና አዛሉ በጭብጨባ ዝምያ ሰኙዋቸዋል፡፡

በዜ፦

በቃእጣይ ውጣና የደረሰው ይውሰደው (ጫጫታ)

አዛሉ፦

እሽሽሽሽሽ... የምን እጣ?

ዘሩ፦

እጣማ አይሆንም

እርስቴ፦

በቃ ሁላችንም አንድ አንድ ጥያቄተ ጠይቀን የመለሰሰው....

በዜ፦

እንዲህማ አይሆንም! እንዴ! እኔ የማላውቀውን እሱ ያውቃል እሱ የማያውቀውን ደሞ እኔ....

ማፊ፦

እኔምን? እኔ አውቃለሁ እንዳትል ብቻ

አዛሉ፦

አሁን አትጨቃጨቁ

በዜ፦

እና አትናገረኛ! ምንም አታውቅም ትለኛለች? (ለማፊ) ባይገርምሽ ብዙ ነገር አውቃለሁ፣

ማፊ፦

ወሬ አታብዛ!

በዝ፦

ሂጂ ወደዛ!

ይቤ፦

እንዴ! እንዴ! Idea ከችአለ!

ሂጅ ወደዛ፣ወሬ አታብዛ።ሂጂ ወደዛወሬ አታብዛ።ዋው/

ሁሉም ሰው ምንድን ነው እሱ?

ይቤ፦

ቤት መታ እኮ

አዛሉ፦

ታዲያ ምን ይሁን ይቤ?

ይቤ፦

ሁላችንም ለምን ግጥም አንፅፍም?

ሁሉም ፀ… ጥይሉና እርስ በርስ ይተያያሉ።

አዎ አጭር አጭር ግጥም ፅፈን

አባቢና ማሚ አወዳድረው አሪፍ ግጥም

ለፃፈ ሰው ሰአቱን ………………

ዘሩ፦

አ…ዎ ይሄ ጥሩ ሃሳብ ነው እንደውም

ልጆቼ የስነ-ፅሁፍ ተሰጥቶዋቸውን ለመፈተን

ይረዳል (ትርፌትገባለች)

ትርፌ፦

(ሁሉንም እያየች) ምነው? ምንሆናችሁ? የምንጫጫታ ነው?

ዘሩ፦

ትርፌ፦

የጠራሽየለም! ስለዚህ……ትርፌእንዴ ጋሼ ባልጠራስ? ቤቴ አይደል?ይቤ

ትርፌ፦

እስቲ ዝምበይ! ቀጥል አባቢ

ዘሩ፦

አዎ የስነ ፅሑፍ ችሎታቸው ይፈተሽና የበለጠው ይሸለማል፣

አዛሉ፦

ጥሩ ሃሳብ ነው ግን ግጥሙን በምን ጉዳይ ላይ ያተኮረይሁን?

ማፊ፦

በፍቅር (ሁሉምያዩታል) ምነው? ወይም በፊልም....

እርስቴበቤተሰብ ዙሪያ ይሁን፣

በዜ፦

በእንትን ላይ አይሆንም?

ሁሉም፦

በምን?

በዜ፦

በ... እ.... እ.... እ..... እ

ይቤ፦

ለምን ሁላችንም ደስ ባለን ነገር ላይ ግጥማችንን አንፅፍም?

አዛሉ፦

አ...ይ አይሆንም ሁሉም ሰው በአንድ ጉዳይ ላይ መፃፍ ነው ያለበት!

ዘሩ፦

ልክ ነሽ ለማወዳደር የሚመቸው እሱ ነው ሁላችሁም በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ከገጠማችሁ ውድድሩ አጓጊዳኝነቱ ደግሞ ቀላል ይሆናል፡፡

አዛሉ፦

ስለዚህ አንድ ጠቃሚ ጉዳይ ላይ ግጥማችሁን አዘጋጁ፣

በዜ፦

በቃ በእንትን ላይ ይሁን በእ.እ.እ

ትርፌ፦

(በማሾፍ) እኔ ግን ጋሼ ለግጥም የሚሆን ርዕስ ስትፈልጉ አባይ ተገድቦ ያልቃል .እ.

ይቤ፦

(በጩኸት) ሁሁሁ. ትርፌ! ግጪ (ይጋጫሉ) ነፍስ የሆነ Idea! ለምን በአባይ ዙሪያ አይሆንም (ሁሉምፀ…ጥይላሉ)

ዘሩ፦

ይቤ

ይቤ፦

!ወይ

ዘሩ፦

ምርጥ ሃሳብ ነው (ለአዛሉ) የሁላችንም ተስፋ የሃገራችን ታላቅ ቅርስ ከመሆኑ አኳያ በጣም በጣም አሪፍ Ideal! (ሁሉምያጨበጭባሉ)

ዘሩ፦

በሉለሁላችሁም 10-10 ደቂቃ ይሰጣችኋል፡፡

አዛሉ፦

እጥር ምጥን ያለ ቆንጆ ግጥም! ታዲያ ለመሸለም ብቻ ሳይሆን ታላቅ! ሃገራዊ ጉዳይ ላይ ልጆቼም ያላቸውን ቀና አመለካከት ለማሳየት እንዲረዳ ጭምር ስለሆነ በርቱ እሽ!

ሁሉም፦

በቃ ይጀመር ይጀመር

ዘሩ፦

(ሰአቱን እያየ) አሁን ሰአቱ…

ትርፌ፦

(እየተልጎመጎመች) አቡቡቡእምምም
ዘሩ፦
ትርፌ ምነው? ደሞ ምን ሆንሽ?

ትርፌ፦

እኔ ልጃችሁ ስላልሆኩ ነው አይደል? ልጃችሁ ብሆን ኖሮ ይሄኔ...

አዛሉ፦

ልጃችን ማነሽ! ታዲያ ምን ጎደለብሽ?

ትርፌ፦

አባይ የሚለውን ሃሳብ ያመጣሁት እኔ ነኝ እንዴ! ማን ባመጣው ሃሳብ ማን...

ዘሩ፦

ትርፌ መነፋረቁን ትተሽ ምን ፈለግሽ?

ትርፌ፦
እኔም ልወዳደር

ልጆቹ፦

ምን?

ትርፌ፦

ግጥም!

ሁሉም አንዴ እርስ በርስ ይተያያሉ አንዴ በአግራሞ ትርፌን እያዩ ይሳሳቃሉ አዛሉና ዘሩ በማይሰማ መልኩ በቀስታ ይነጋገራሉ አዛሉ ወደ ልጆቿ ዞርብላ

አዛሉ፦

ትወዳደር በቃ

ልጆች፦

ምን!?

ዘሩ፦

ትወዳደር

ይቤ፦

ግጥም?

ትርፌ፦

አዎ! ምነው?

ማሪ፦

ትርፌ ግጥም እኮ…

ይቤ፦

ትርፌ ሠአት ለመሸለም ነው?

ትርፌ፦

አ? ሠአት?... አዎ ይሁን ትርፌ ሰአት አይወድላትም ያለው ማነው?

ይቤ፦

አሃ… በሰአት ምን ያህል እንደምትበይ ለማወቅ ይጠቅምሻል

ትርፌ፦

እወዳደራለሁ! በቃ ከበላ ይተፈቅዶአል!

ዘሩ፦

አሁን ሰአት እንይዛለን ሁላችሁም በ10 ደቂቃ ውስጥ ጨርሳችሁ እድትከሰቱ! በቃ!

ሁሉም በየተራ ግጥም አቅርበው ከጨረሱ በኂላ

ዘሩ፦

በርግጥ ግጥሞቻችሁ ያምራሉ በጣም

ትርፌ፦

ጠፋኝ እንጂ የኔ ይበልጣል

ዘሩ፦

ዝምበይ! ቀልቃላ! ስለዚህ (ሰአቱን አይቶ ንግግሩን ቆሞያረግና) ስለዚህ ዛሬ ተሸላሚ የሚሆነው ሰው ሁሉም በጉጉት ያዩታል ዘሩ ግን ሰአቱን አይቶ ዝም ይልና

ይቀጥላል።

ተሸላሚ የሆነውን ሰው ለመለየት

(ሠአቱን አይቶ ዝም) አዎ ለመለየት

አስቸ ጋሪ ነበር (አዛሉን ያያታል)

አዛሉ፦

እውነቱን ነው…

ዘሩ፦

(ሰአቱን እያየቆሞ) አዎ አዛሉ እውነቷን ነው (ሰአቱን አይቶ ዝም) አዛልዬ

አዛሉ፦

ወዬ ዘርሽ

ዘሩ፦

ሰአቱን በደንብ አየሽው?

አዛሉ፦

አዎ ቆንጆ ሰአትነው

ዘሩ፦

ይሄ ሰአት እጄ ላይ በጣም አምሮበታል።

ተወዳዳሪዎች፦

(በጋራ) እና!?

ተፈፀመ።

## የመልመጃ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተክክል የሆነው እውነት ወይም ተክክል ያልሆንው ደግሞ ሃሰት በማለት መልሱ።

1. ዘሩ ገንዘብ ይወዳል።
2. በውድድሩ አሸናፊው ሰዓት ተሰጥቶታል።
3. አዛሉ መልካም እናት ናት።
4. የተወዳደሩት ሁሉ በጉጉት የሚጠብቁት ሽልማት ብር ነበር።

ከሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ(ጭ)።

1. ከሚከተሉት ውስጥ የሰውን መልክ ወደ ሌላ ፍጡር የመቀየር አቅም ያለው ጥበብ የቱ ነው?
   ሀ. አልባሳት ለ. የገጽ ቅብ ሐ. ፎቶ መ. ሁሉም
2. ከሚከተሉት አልባሳት ውስጥ የስራ መደብን የሚገልጽ የትኛው ነው?
   ሀ. ነጠላ ለ. የሰርግ ቬሎ ሐ. ማልያ መ. መልስ የለም
3. ከተጠቀሱት ውስጥ የገተሰፅ ቅብ ባለሙያን የማይገልጸው የቱ ነው?

   ሀ. የቀለማት ቅንብርን ማዎቅ አለበት።

   ለ. የሰውን ቆዳ ሁኔታ ማዎቅ አለበት።

   ሐ. የስዕል ችሎታ ሊኖረው ይገባል.።

   መ. ሙዚቀኛ መሆን አለበት።

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በክፍቱ ቦታ ሙሉ

1. እንደየ ጊዜው እና የስልጣኔ ደረጃ አልባሳት-----ይባላሉ?
2. የአንድን ማህበረሰብ ወግ፣ ልማድና ማንነት የሚገልጹ አልባሳት----በመባል ይታወቃሉ?
3. የገጽ ቅብ ስለገጸ- ባህርያት ለማሳወቅ ከሚሰጣቸው ጠቀሜታዎች ውስጥ ቢያንስ አራቱን ጥቀስ(ሺ)

## 2.6.የወረቀት ኮላዥ እና ዝግ ህትመት /በድንች ማተም/

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- መሰረታዊ የወረቀት ኮላዥ አሰራር ዘዴን ታወቃላችሁ፡፡
- ኮላዥ የተሰሩ የጥበብ ውጤቶችን ታደንቃላችሁ ፡፡
- ኮላዥ በምን መስራት እንደምትችሉ በዝርዝር ትገነዘባላችሁ ፡፡
- የወረቀት ኮላዥ ተጠቅማቹ የማስዋቢያ ስራዎችንና እንዲሁም የራሳችሁን የፈጠራ ሥራ ትስራላችሁ፡፡
- የወረቀት ኮላዥና ሕትመትን ተጠቅመው የማስዋብያ ስራዎችንና እንዲሁም የራሳቸውን ነፃ የፈጠራ ሥራ ትስራላችሁ
- ለሚሰሩት የሕትመት ስራ በድንች ላይ ንድፋን ትቀርፃላችሁ፡፡
- ወረቀቶችን በተለያዩ መጠን ይቆራርጣሉ
- የወረቀት ኮላዥ እና ዝግ ህትመት/በድንች ህትመት/ ትስራላችሁ፡፡

ሞዛይክን ለመስራት የመስታወትና የእምነ በረድ ስብርባሪዎች ፣የወንዝ ዳር ጠጠሮችና ፣ባልጭት ድንጋይ ፣ዶቃ የመሳሰሉት ሲሆኑ እነዚህን ነገሮች በምትሰበስቡበት ጊዜበቅርጻቸው ፣በቀለማቸው እንዲሁም የሻከርና ለመለስለስ ባህሪያቸው ለምትፈልጉት ሥራ ውበትን የሚሰጡ እንዲሆን በጥንቃቄ መምረጥ ይኖርባችኃል፡፡ የወረቀት ኮላዥ አስራር ዘዴ በመለጠፍ በመቆራረጥ የሚሰራው ነው፡፡

ጠንከር ያለ ወፍራም ሰሌዳ ላይ ለወረቀት ኮላዥ ሥራ የተመረጠውን ምስል መንደፍ::እንደየ ምርጫችሁ በኮላዥ ሥራ ልትገልጹት የምትፈልጉትን ንድፍ መንደፍ ተገቢ ነው::




በአካባቢያችን በቀላሉ ሊገኙ የሚችለውን የወረቀት ኮላዥ መስሪያ ወፍራም

ካርቶኖችን የተለያዩ ቀለሞችን መቀባት::

ቀለም ተቀብተው የተዘጋጁ ካርቶኖቹን በተለያየ መጠንና ቅርፅ መቆራረጥ::

የተቆራረጡትነነን ከለር ካርቶኖች በየቀለማቸው መለየት እና በቀላሉ የምንፈልገውን ከለር በቀላሉ እንድናገኝ አድርገን ማዘጋጀት::

ተፈላጊውን ቀለም የያዘውን በመምረጥ በተዘጋጀው ንድፍ ላይ መለጠፍ /ማጣበቅ/ ::

በሚስራበት ጊዜ ብርሃናማውና ጥላማውን አካል ለማሳየት

በጥንቃቄ በማስተዋ ልትክክለኛውን ቦታ እስከ ሚንፀባረቅ ድረስ መስተካከል ያለበትን ጉድለት መስራት::



ሥዕል፡-ቀለም የተቀቡ የተዘጋጁ  ካርቶን በተለያየ መጠንና ቅርፅ መቆራረጥ

### 2.6.1.ማጠበቂያ አሠራር

የሞዛይክ ሥራን ለመስራት ማጣበቂያ በጣም አስፈላጊ ነው።በመሆኑም ለማጣበቅ በፋብሪካ የሚመረቱ ማጠበቂያዎችን መጠቀም ቢቻል በምግብ እህል ዱቄት ሙቅ በማዘጋጀት፤የዛፍሙጫና በተለምዶ የተክል ደም በመባል  የሚታወቀውን ፈሳሽ ለተፈላጊው ስራ ማዋል ይቻላል።



ሥዕል፡ከዛፍ ማጣበቂያ አሠራር



ሥዕል፡የፋብሪካ ሙጫ

- መምህራቹ አስራር ዘዴ በተግባር ያስተምሯቹኃል።





ሥዕል፦ ወረቀት የተሰራ ኮላዥ

## የቡድን ውይይት

1- በኮላዥ ጥበብ የተሰሩ የፈጠራ ውጤቶችን ማሳየትና በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ ፡፡





ሥዕል ፦ ለውይይት የቀረበ በወረቀት የተሰራ ኮላዥ

## መልመጃ አንድ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሳቸውን ምረጡላቸው፡፡

1. የወረቀት ኮላዥ ለመስራት የሚያስፈልጉንን ቁሶች በቅደም ተከተልዘርዝሩ?

ሀ/ወፍራምካርቶን   ለ/ ከተር፣መቀስ   ሐ/የወሃቀለም፣ሙጫ   መ/ሁሉም

2. የወረቀት ኮላዥ ለመስራት ማጣበቂያ ከምን እንሰራለን?

ሀ/ ከዛፍ ለ/ ከተለያዩ ዱቄት ሐ/ ሀእናለ መ/ ምልሱ የለም

3. በአካባቢያችን በቀላሉ ሊገኙ የሚችለው የወረቀት ሞዛይክ መስሪያ የቱ ነው?

ሀ/ የመስታወት ስብርባሪ ለ/ የካርቶን ቁርጥራጭ ሐ/የእምነበረድ መ/ሁሉም

### 2.4.2 ህትመት/በድንች ማተም/

ህትመት ማለት የአንድ ነገር ምስል / ቅርፅ / ደግሞ ደጋግሞ በተፈለገው ብዛት ማራባትወይም ማባዛት ማለት ነው።የህትመት ስራ የሚከናወነው ከፍተኛ መስሪያዎች ተጠቅመን እና በእጅ ሲሆን በእዚህ ትምህርት ክፍል ቀላል ዘዴዎች በመጠቀም የህትመት ስራዎች ትስራላችሁ። የህትመት ስራ በአካባቢያችሁ የሚገኙ በርካ ታየተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ነገሮችን እንዳስተዋላች ሁይታመናል።አጠቃላ ይገፅታ በሚገባ አስተውሎ መገንዘብ ለህትመት ሥራ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።የህትመት ስራ ውጤቶች በብዙነ ገሮች ላይይታያል። እነዚህን የህትመት ውጤቶች በት/ቤት ሆነ በቤታችሁ ትጠቀሙባቸዋላችሁ።

በድንች ላይ የተለያዩም ስዕሎችን አርማዎችነን ቆርጣችሁ በማውጣት የድንች ብሎክ ህትመት ሥራን ትስራላችሁ።





ሥዕል5 ፦ በድንች ላይ ለሕትመት የሚሆን የንድፍ የተቀረፀ




ሥዕል ፦ የድንች ህትመት ውጤቶችን ተመልከቱ

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሙዚቃ ኖታዎችን እንዴት መፃፍ እንደምንችልና ስያሜያቸው ምን እንደሆነ፣ ስለ ስብስብ/staff/ እና ስብስብ/staff/ ፣መስመርና ክፍት ቦታዎች እንዳሉት፣ ስለ ድንገተና ምልክቶችና የጊዜ ቆይታ፣ የሙዚቃ ድምፆችን በውዝዋዜ እንቅስቃሴ እንዴት መግለጽ እንደሚቻል፣ አልባሳትንና የመዋቢያ ግብኣቶችን ተጠቅሞ ትያትር መስራት፣ የገፅ ቅብና የመዋቢያ ግብአቶች ምንነት ስለ ወረቀት ሞዛይክና በድንች ዝግ ህትመት እንዴት ማተም እንደምንችል በተግባር የተደገፈ ትምህርት ተምረናል፡፡

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ለሚከሉት ጥያቄዎችን ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

1-የድንች ህትመት አሠራር ቅደም ተከተል በዝርዝር አስረዱ ?

ሀ ድንቹን እኩል በኩል መሀል መቁረጥ

ለ ተፈላጊው ምስል ወጣብሎ እንዲታይ ማድረግ

ሐ ወረቀት ወይም ጨርቅ ላይ እየለተሙ ማተም

መ ሁሉም

2 የህትመት መስሪያ ግብአቶች ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ ቀለም ለ ድንች ሐ ስለታማ ነገር መ ማሽን

3 የድንች ህትመት ስትስሩ ድንቹ ላይ ከነደፋቹ በኃላ ተቆርጦ የሚውጣው ክፍል የትኛው ነው

ሀ ንድፉን ለ ወጣማለት ያለበትን ሐ ከንድፉ ውጪ ያለውን መ ሁሉንም

# ምዕራፍ ሦስት

## ታሪካዊና ባህላዊ አውዶች

### የምዕራፍ ሦስት መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ትኩረት የተደረገው በዋናነት በሀገራችን ባህላዊና ታሪካዊ አውዶች ላይ ሲሆን በዚህ ስር ያሉ ይዘቶች ደግሞ ማህበረሰብ የሚጠቀምባቸው የሀገረሰብ ውዝዋዜዎች አይነቶች የሀገረሰብ ተረትና ታሪኮች እና የዕይታ ጥበባት ታሪክ ወይም የዋሻ ጥበብና ቀለም ቅብ ላይ በዝርዝር የምናይበት ምዕራፍ ነው፡፡

### 3.1. ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸው ሃገረሰባዊ መዝሙራት

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- በስታፍ ላይ የተፃፉ ኖቶችን ከነዜማው ትዘምራላችሁ
- ቃላቶችን በቅደም ተከተል ትረዳላችሁ
- የተለያዩ ስልተምቶችን ታውቃላችሁ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ መዝሙር

የዜግነት ክብር - በኢትዮጵያችን ፀንቶ

ታየ ህዝባዊነት - ዳር እስከዳር በርቶ

ለሠላም ለፍትህ - ለሕዝቦች ነፃነት

በዕኩልነት በፍቅር - ቆመናል ባንድነት

መሠረተ ፅኑ - ሰብዕና ያልሻርን

ሕዝቦች ነን ለሥራ- በስራ የቆምን

ድንቅ የባህል መድረክ - የአኩሪ ቅርስ ባለቤት

የተፈጥሮ ፀጋ - የጀግና ሕዝብ እናት

እንጠብቅሻለን - አለብን አደራ

ኢትዮጵያችን ኑሪ - እኛም ባንቺ እንኩራ

ግጥም ደረጀ መላኩ
ዜማ ሰለሞን ሉሉ
1984ዓም






**መዝሙር ኢትዮጵያ ሀገሬ**

ኢትዮጵያ ሀገሬ መከታ ጋሻዩ/2/፣፣

ለኔ መመኪያ ነሽ ለልቤ መኩሪያዩ/2/፣

ኢትዮጵያ ሀገሬ መከታ ጋሻዩ፣

ለኔ መመኪያ ነሽ ለልቤ መኩሪያዩ/2/፣

የሃገሬ ውበት እጅግ ደስ ያሰኛል፣

ኢትዮጵያዊነቴ በጣም ያኮራኛል፣

ኢትዮጵያዊነቴ እጅግ ያኮራኛል፡፡

ግጥምና ዜማ ፍሬው ሐይሉ



<u>መዝሙር መማር ያስከብራል</u>

መማር ያስከብራል

መማር ለሀገር

መማር ለዕድገት

መማር ለኩራት

መማር ያስከብራል

ሀገርን ያኮራል (2 ጊዜ)

ጥበብን ዕውቀትን

እንሂድ እንማር እንቅሰም ማሩን

እንሂድ እንገስግስ እንቅሰም ማሩን

መማር ያስከብራል

ሀገርን ያኮራል (2 ጊዜ)

ግጥምና ዜማ የክቡር ደ/ር ተስፋዬ አበበ



**መዝሙር ሰላም**

ለሰው ልጆች ፍቅር

ለሰውልጆች ሰላም x 2

ለሰውልጆች በአለም ዙሪያ ሁሉ

ሰላም ይሁን ምድሩ ሁሉ

ሠላም ሠላም ሠላም

በአለም ዙሪያ ሁሉ x 2

ለሠው ዘር በሙሉ

ከባህር ከየብሱ ከሰፊው ውቂያኖስ

በሚመጣው አየር በሚነፍሰው ነፋስ

ያለን መልካም ምኞት ያለን ቀና መንፈስ

የሰላም ጥሪያችን መልክታችን ይድረስ

የተበከለ አየር ጠፍቶ ከላያቸው

የዱር አራዊቶች አዋፍ በጎጇቸው

ሁሉም በየአሉበት በየበኩላቸው

የሰላሙ ፋና ይድመቅ ይብራላቸው

ባለም ባለም ይስፈንልን ሰላም/2/

ሰላም ሰላም ሰላም

በአለም ዙሪያ ሁሉ

ለሠው ዘር በሙሉx 2

ህፃናት እንዲያድጉ በንፁህ አይምሮ

ነፃ ህሊናቸው ጎልብቶና ዳብሮ

ወጣት ሽማግሌ የሰው ዘሮች ሁሉ

ሰላም ባለማችን ይላሉ በሙሉ

ዘንባባ ዘንጥፈን እርግቦችን ለቀን

ዘር ቀለም ሳንለይጥላቻን አርቀን

ለሰው ልጆች ደስታ ለሰውልጆች ፍቅር

ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ ለሰላም እንዘምር

ባለም ባለም ይስፈንልን ሰላም

ሠላም ሠላም ሠላም

በአለም ዙሪያ ሁሉ x 2

ግጥም ይልማ ገብረአብ

ዜማ አበበ መለሰ






## 3.2 ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸው ሀገረሰብ የውዝዋዜ አይነቶች

**ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት**

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የብሄረሰቦችን አንድነት ለሀገር እድገት በሚገባ ትረዳላችሁ

ሀገራችን የህዝቦቿ አንድነት እና ውበት የብሄር ብሄረሰቦች ሙዚቃና ለሙዚቃው ድምቀት ማጀቢያ ሚጠቀሙበት ውዝዋዜ አንዱ መሆኑ እሙን ነው።



የአንድነትና ህብር ሀገር እናት



ውበታችን

## 3.3. የሃገረሰብ ተረትና ታሪኮች

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ስለ ታሪክ ምንነት ትረዳላችሁ፡፡
- የታሪክ ማቅረቢያ መንገዶች ታውቃላችሁ፡፡
- ስለ ስነቃል ታስረዳላችሁ፡፡
- አጭር ልቦለድ ታሪክ ትተርካላችሁ፡፡

ታሪክ በአለማችን፣ በአገራችን፣ ወይም በአካባቢያችን በአንድ ወቅት የተከሰተን ነገር ወይም የፈጠራ ሠዎች ሰው ማወቅ አለበት ብለው የሚፈጥሩትን የፈጠራ ስራ (ልበወለድ)የሚገለጽበት ጥበብ ነው፡፡

የስነጽሁፍ መሰረታዊያን በተሰኘው የዘሪሁን አስፋው መጽሀፍ ላይ ታሪክን በሚከተለው መልኩ ተገልጾ እናገኘዋለን ታሪክ በተወሰነ የጊዜ ቅደም ተከተል የተቀናጁ ሁነቶች ትረካ ነው፡፡ በሁነቶቹም ሰንሰለታዊ ጉዞ ታሪኩ ከአንዱ ደረጃ ወደ ሌላው ሲተላለፍ ባለታሪኮቹ የተለያዩ ድርጊቶችን በመፈጸም ማንነታቸውንና የሚደርስባቸውን ክፉም ሆነ ደግ ነግር ይታያል፡፡

ይህ ክስተት ወይም የፈጠራ ስራ በተለያዩ የማስተላለፊያ መንገዶች የተርካል፡፡ ታሪክ በተለያዩ የጥበብ ዘርፎች ሊቀርብ ይችላል፡፡ እነሱም፦ ስነ-ፅሁፍ፣ ሙዚቃ፣ ስነ-ስዕል፣ቅርፃ ቅርፅ እና ስነ-ህንፃ ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸው የኪነ-ጥበብ ዘርፎች በራሳቸውሰፋፊ የትምህርት መስኮች ሲሆኑ ለትምህርት ዘርፎችን አቀራረብ ዘዴ የሚቀርበንንስነ-ፅሁፍ ስናነሳ በስሩ ተለያዩ ዘውጎችን እናገኛለን፡፡ እነሱም፡- ግጥም፣ ልብ ወለድ፣ተውኔት፣ እንዲሁም ቪዲዮ (ፊልም)ን መጥቀስ እንችላለን፡፡ ስለዚህ የምናውቀውን፣የሰማነውን፣ ያየነውን ወይም የፈጠርነውን ታሪክ በግጥም፣ ልብ ወለድ፣ በተውኔትወይም በቪዲዮ አዘጋጅቶ ማቅረብ ይቻላል፡፡
ከእዚህ በተጨማሪም ቃላዊ በሆነው ታሪክ የመንገሪያ ክዋኔያዊ ሃብታችን ስነ-ቃልማቅረብ ይቻላል፡፡

ስነ-ቃል፡- የህብረተሰቡን ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ የአኗኗር ስርዓትና ልዩ ልዩ የህይወት ገጽታዎች እንዲሁም ተፈጥሯዊ ክስተቶችን (ማንነትንና ታሪክን) ከትውልድ ወደትውልድ በመንገር፤ በመተረትና በማዜም የሚያስተላልፍ ኪነ-ጥበባዊ ሀብት ነው፡፡የራሱ የሆነ የአጀማመርና የአጨራረስ ክዋኔ እንዲሁም እንደየ ቦታውና እንደየዘመኑ እየተሻሻለና እየተቀያየረ ይቀርብበታል፡፡ የተለያዩ ተግባራት ሲኖሩት ጣሪክ ለማሳወቅ(ለአስተምሮት) በቀላልና ሳቢ በሆነ መልኩ መጥፎ ነገሮችን በመንቀፍና ጥሩ ነገሮችን በማግዘፍ የማይረሳ አድርጎ በቀላል መንገድ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ስለሚያድርግ ትልቅ ጥቅም አለው፡፡

### መልመጃ 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሃሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ስነ-ቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ይተላለፋል፡፡
2. ተረት የስነ-ቃል አይነት አይደለም፡፡
3. ኪነ-ህንፃ በጥበብ ዘርፍ ውስጥ አይካተትም፡፡
4. ታሪክ ከእውነተኛ ክስተት ወይም በፈጠራ ሰው (ደራሲ) ሊፈጠር ይችላል፡፡

ከእዚህ በመቀጠል ስብራት እና ሌሎች ከተሰኘው የታቦር ገብረመድህን ድርሰት ላይሽንቁር የሚለው አጭር ልብ ወለድ ታሪክ ቀርቦላችኃል አንብባችሁ የቀረቡላችሁንጥያቄዎች መልሱ፡፡

ስፍራው ደሴ፣ ሙገድ የገብያ አዳራሽ አጠገብ ነው፡፡ የማለዳው ቅዝቃዜ በለስላሳዋ የፀሀይ ሙቀት ገና መተካት አልጀመረም፡፡ በህፃኑ ወይታና እሪታ ሲታመስ ያደረው የነድያኑ ሰፈር እንደ ሙታን አምባ ፀጥ እረጭ ብሏል፡፡ በሰፈሩ ህይወት መኖሩ የሚታወቀው ቀረብ ብለው ሲያስተውሉት ብቻ ነው፤ እዚህና እዚያ በወዳደቀው በእንቅልፍ ዓለም ሰምጦ በሚያንኮራፋው፣ በሚቃዠውና በሚገላበጠው ነዳይ፡፡

ሁሉም ነዳይ እንቅልፍ አጥቶ ያደረው ጮቄም፣ የህፃኑ እናት፣ ከእሱጋር እንቅልፍ አጥታ በማደሯ ክንዷ ላይ እንዳስተኛችው ተዘርግታለች፡፡ ግንበቅዠት የተሞላው እንቅልፏ ለእሷ እረፍት አልሰጣትም፡፡ አልፎ አልፎ ትወራጫለች፤ ታነበንባለች… በእንቅልፍ ልቧ፡፡ ኮማ (ሰመመን) ውስጥ እንደ ገባ በሽተኛ ራሱን የሳተ የሚመስለው ህፃን ልቡ በድካም ደም መርጨቷን ቀጥላለች፡፡

ጮቄ ትወራጫለች፡፡ አንዳች አቋሙ የሰው፣ ፊቱ የገመሬ ዝንጀሮ፣ ጆሮው የአህያ፣ ጅራቱ የበሬ፣ እግሮቹና መዳፎቹ የአንበሳ የመሰለ አስፈሪ ፍጡር በክንዷ የታቀፈችውን ህፃን ለነጥቃት፤ ያቀፈችበትን ክንዷን በሀይል ለመፈልቀቅ ሲታገላት ላለመልቀቅ፣ ላለመሸነፍ ስትተናነቅ ነፍሷ ተጨንቃለች፡፡

በዙሪያዋ የተኮለኮሉ ነደያን እንዲደርሱላት ለመጮህ አፏን ለመክፈት ብትሞክር ያቅታታል፡፡ በእግራ ልትራገጥ በእጇ ልትመነጭቅ ትፈልግና አካላቷ ሁሉ እንደ በረዶ ተጋግሮ አይላወስላትም፡፡ እንደገና ለመጮህ ትሞክራለች፤ ላንቃዋ ተላትሞ አይላቀቅላትም፡፡ አስቀያሚው ፍጡር ጨረ፣ ነፍሷን እያስጨነቀ ትንቅንቁን ይቀጥላል፡፡

እንደምንም አንዱን እጇን ማንቀሳቀስ ችላ ጉሮሮውን ልታንቀው ስትሞክር በስጋ ደዌ በሽታ ተመድምዶ መዳፍ ብቻ የቀረው እጇ አልጨብጥ ይላታል፡፡ እንደገና ለመጮህ ስትሞክር የተላተመው አፏ ይከፈትና ይቀራል… ድምፅ ግን አይወጣትም፡፡ ትጮህለች … ጩኸቷ ግን ለራሷም አይሰማትም፡፡

ድንገት የሚተናነቃት አስቀያሚ ፍጡር ጆሮ በተከፈተው አፏ ሲገባ አፏ ይላተምና ያ አስቀያሚ ፍጡር በገጠመው ድንገተኛና ሀይለኛ ንክሻ ሲበረግግ ሁሉም ነገር ቀጥ ይላል፡፡ አስቀያሚው ፍጡር እንደ ጤዛ ትንን፣ እልም…

ከእዚያ እንደ ግግር በረዶ ረግቶና አንዳች ነገር ተጭኖት አልንቀሳቀስ ብሎ  የነበረው ሰውነቷ ተፍታታ። ደርቆ የተላተመው መንጋጋዋ ተላወሰ። ነቃች ዙሪያዋን ብትማትር ሁሉም ነድያን እንደተኙ ናቸው። የሚያንኮራፋው የሚገላበጠው፣ የሚቃዠው…ሁሉም እንደተለመደውና እንደነበረ ነው። ለስላሳዋ የጠዋት ፀሀይ በዙሪያው ያሉትን ሕንፃዎች ጥላ ቁመት እያሳጠረች ቢሆንም ገና ለነድያኑ ሰፈር አልደረሰችም እሩቅ ናት።ስለዚህ ነድያኑ አሁንም በቅዝቃዜው እንደተጨበጡ፣  በብርዱ እንደተኮራመቱ ናቸው።

ግራ ክንዷ ላይ የተጋደመውን ጨቅላ ቀና ብላ አየችው። ፀጥ ብሏል። ስጋ ደዌ የመደመዳቸው ጣቶቿ ስሜት አልባ ስለሆኑ በመዳፏ ጀርባ ዳበሰችው። ሙቀቱ እንዳለ ነው። በወፍራም ድሪቶ የተጠቀለለ በመሆኑ ከቅዝቃዜው ጥሩ መደበቂያ  ሆኖታል.። ተመስገን አለች በልቧ ከሌሊት ዋይታው  ከእዚያ ጭንቀትና ጥበት አንፃር ያሁኑ ፀጥታ ከህመሙ ለመታገሱ ምልክት ነው በማለት።

ቆይ ይመጣታል አጉረመረመች ለራሷ። የባለቤቷ የህፃኑ አባት ጥሏት ሌላ ቦታ ማደር አብግኗት። ህፃኑ መታመሙን በተለይ ሌሊት ማስቸገሩን እያወቀ እንዳሻት ትሁን ብሎ በግዴለሽነት ትቷት የትም ማደሩ አብግኗታል። በነተበውና አቧራ በቃመ ቡትቶ የተጠቀለለውን ህፃን ፊቱን ገልጣ አየችው። መልሳ ሸፈነችውና ክንዷን ቀስብላ ካንገቱስር በመምዘዝ ቀና ብላ ቁጭ እያለች ሁለተኛ በማለት አጉረመረመች፤ አጠገቧ ትንሽ ፈንጠር ብላ የተጋደመችው የእሷው ቢጤ ነዳይ ጓደኛዋ ማታ ሹክ ያለቻትን አስታውሳ። እስቲ የት ሄደ ይባላል የጮቄ ጥያቄ ነበር፣ ማታ ባሏ ከወትሮው ሰዓት በማሳለፍ ተስፋ ከቆረጠች በኋላ በጭውውታቸው መሃል የሰነዘረችው። ቧንቧ ውሀ ነው ብዋ እገምታለሁ! የጓደኛዋ አስተያየት ቧንቧ ውሀ ሌላ የነዳይ ማደሪያ ሰፈር አለ፤ ካስፓልቱ አደባባይ ትንሽ አለፍ ብሎ። ቧንቧ ውሃ

እዚያ ምን ይሰራል ከንፈሯን አሸራማ መልሳ ጠየቀቻት። የሚሰራውንማ እሱ ያውቃል! አሽሙር አከለችበት። ጮቄ የጓደኛዋ የነገር አካሄድ ገብቷታል። ምን ማለትሽ ነው ቢሆንም ጠየቀቻት፤ በስቃይ የሚያቃስተውን ህፃን ዝም እንዲል እየወዘወዘች። አላውቅም ልትይ ነው ሴትየዋ የተገረመች መሰለች፤ በደረበችው ድሪቶ ስር በስጋ ደዌ የተጎዳ እጇን መዳፍ ሰዳ ብብቷን በሀይል እየፈተገች። ጣቶቿን በሙሉ በደዌው  አጥታለች። ምኑን ነው የማውቀው ከቧንቧ ውሃዋ አይነ ስውር ጋር ፍቅር  መጀመሩን…ጮቄ መጀመሪያ ሳቀች፤ ከዚያ ተገረመች፤ ከዚያ የቅናት ሾተል ሸነቆጣት፤ ቀጥሎ ተናደደች፤ በመጨረሻም አንጀቷ አረረ፣ ቀሽቷ ደበነ። ቆይ ይነጋል ብቻ ብላ አሰበች፤ነገር በልቧ ጠነሰሰች፤ ቂም ቋጠረች… እንዳሰበችውም መንጋቱ አልቀረም ነጋ።

ከድሮው በተለየ፣ እጅግ ረጅም ሌሊት የነበረ ቢሆንም ነጋ… ወተቱ በቅጡ ያልተጠባለት ጡቷ እንደኛው ከምን አይነት ጨርቅ እንደተሰፋ ከማይታወቀው ቀሚሷ አንገትጌ አፈትልኮ ይታያል፡፡ የጡቷ ሞላ ማለት በድህነት ጀርባ የተደበቀ ወጣትነቷን ያሳብቃል፡፡ መዳፍ ብቻ በሆነው እጇ ገፋ አድርጋ ወደ ጨርቋ አስገባችውና ጉልበቶቿን አቅፋ የተጎሳቆለ ፊቷን ደፋችበት፡፡

ከጥቂት ደቂቃዎች በኃላ ጉልበቶቹ የሚነካኩ ብቻም ሳይሆኑ ሲራመድ የሚፋተጉ ሰውነቱ ነትቦ እንደሳሳ ዲሪቶ ድቅቅ ብሎ የቀለለ፤ የደቀቀ ነዳይ አስፓልቱን ይዞ ከወደ ቴሌ ብቅ አለ፡፡ የጮቄ ባል ነው፡፡
እግሮቹ እንደልቡ ስለማያራምዱት አከሄዱ አዝጋሚ ነው፡፡ የሌሊት ልብሱን አጣጥፎ ተክሻው ላይ ተሸክሟል፡፡ እንደ ካፖርት ከረዘመበት፤ ግጥም ብሎ በብዙ ቁልፎች አንገቱ ድረስ ከተቆለፈውና ብዙ ቦታ ከተጣጣፈው ኮቱ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ደቃቃ ሰውነቱ ከአፋራም አይኖቹና ራሱን መሸከም እንዳቃተው ሁሉ ወደ አንድ ወገን ቀለስካለው አንገቱ ጋር ባአንድነት ሲታይ ሀዘን በልብ ያችራል፡፡

ከነደያኑ ሰፈር ሲደርስ እያቅማማ ጉልበቶቿ ላይ ወደተደፋችው ጮቄ ተጠጋ፡፡ አንገቱን እያቅለሰለሰ አፋራም አይኖቹን አንዴ ሚስቱ አንዴ ህፃኑ ላይ አንከራተተ፡፡ ጮቄን ለማናገርም ሆነ ህፃኑን ገልጦ ለማየት መፍራቱ በግልፅ ያስታውቃል፡፡

ሌሊት ሌሊት የህፃኑን የስቃይ ዋይታና እሪታ ሊቋቋም ባለመቻሉ ነበር ለጮቄ ሳያመክር ሌላ ቦታ ሄዶ ያደረው፡፡ ቢሆንም ሳይናገር በመሄዱ ጮቄ በነበልባላዊ ምላሷ እንደ ምትወርድበት ገምቷል፡፡ ስድብና እርግማኗ ማብቂያ የለውም፡፡ ከባሰባት ደግሞ ለዱላም አትመለስም፡፡ ብቻ እሷ ተናዳ ስትናገር መልስ አለመስጠት ነው፤ ሀሳቡን ቀይሮ መለስ አለና የሙጋድን የገብያ አዳራሽ ካጠረው ግንብ ስር ባለው ትልቅ ድንጋይላይ ጉልበቶቹ እንደ ተጋጠሙ እግሮቹን ግራና ቀኝ ልኮ ሲቀመጥ አሳለው፡፡ ጮቄ ቀና ብላ አይኖቿን ተከለችበት፡፡ ነበልባላዊ አይኖቿን ሊቋቋም ስላልቻለ አፋራምአይኖቹን አሸሸ፡፡ ቅልስልስ አይኖቹን ደፋ፡፡ እንደጓጎለ የፍራሽ ጥጥ እየጠቀለለናወዲያወዲህ የተንጨባረረው ጸጉሯ አስፈሪ ፍጡር አስመስሏታል፡፡ እና የስድብ ናዳዋንወረደችበት… እ! አንተን ብሎ ወንድ!.. በጩኸቷ የነዳያኑን ሰፈር አመሰችው፡፡በእንቅልፍ ዓለም የነበሩ፤ አልያም ነቅተው በየግላቸው የሃሳብ ስንክሳር ተጠምደውየነበሩት ነዳያን ሁሉ ተቀሰቀሱ፡፡ አንተን ብሎ ባለ ሁለት ሚስት! ጥምልምል!
እ… እኔኮ

ዝም በል ደሞ እኮ አፍ አለኝ ብለህ ትናገራለህ፡፡ እነዚህን እግሮችህን ነው የምሰባብርልህ፡፡ የተቀሰቀሱት ነዳያን ጣልቃ ሊገቡ የሚዳፈሩ አይደሉም፡፡ ጮቄ ያለገላጋይ ወረደችበት ባለቤቷን፡፡ ሁለቱ ሲጨቃጨቁና ጮቄ ከሌላ ሰው ጋር ስትጣላ ጣልቃ ለመግባት የሚሞክር ሶስተኛ ወገን ካለ እሱ የምሱ ተቋዳሽ ነው የሚሆነው፡፡ ራሷው ተናግራ ሲወጣላት ራሷ ዝም ትላለች፡፡ አለያ እሷን ሀይ ማለት እሳቱን የባሰ ማራገብ ብቻም ሳይሆን ወደ ጎረቤቱ እንዲዛመት መቆስቆስ ነው፡፡

እኔ እዚህ ባንተ ዲቃላ መከራየን ሳይ አድራለሁ አንተ ባለሁለት ሚስት፣ ወግ ደረሰህና ትዝናናለህ፡፡

የ- የምን ሁለተኛ ሚስት ነው የምትይው!

ቆይ ቧንቧ ውሃ አይደለም ያደርሽው

ኸረ አይደለም፡፡

ታዲያ የት ነው

መናኸሪያ ነው አውቶቡስ ተራ፡፡ ውሸቱን ስለመሰላት ይብስ ተበሳጨች፡፡

እዚያሥ ቢሆን ምን አባክ ልትፈጥር ነው ሄደህ ያደርሽው- እ የኛ ባለሁለተኛ ቤት! የማንን ጎፈሬ ስታበጥር ነው ያደርሽው እዚያ ደሞ አንተም ወንድ ሁነህ! ተራህን ታቅፈሀት ትውላለህ፡፡

እባክሽ ጮቅዬ እኔ እኮ…

ችግር ይጨቅጭቅህ! ስሜን አተጥራ፣ ሞት ወደግዛቱ ይጥራህ! ያዝ ልጅህን፤ ድንገት ብድግ ብላ ህጻኑን ከነድሪቶው አፋፍሳ አነሳችውና ወስዳ አስታቀፈችው፡፡ ባል ደንግጦ እንዴ ጮቄ እንዴ በእቅፍ ባለው ህጻን ላይ አይኖቹን አንከራተተ፡፡ ህጻኑ ድንገት በእሪታ፣ ስቃይ በተሞላው ወይታ ሰፈሩን ይባስ አመሰው፡፡ ባል በድንጋጤ ተጨማደደ በእቅፍ ያለውን ህጻን ወደ እራሱ አጥብቆ እያቀፈ፡፡ ጮቄ ስሜት አልሰጣትም፡፡…

ሽንጧን ይዛ እየተውረገረገችበት፤ ቻለው፣ እኔ ስችለው ያደርኩትን፡፡ ወገኛ፡፡ ትታው መንገድ ቀጠለች እሱ በመጣበት አቅጣጫ፡፡

ጮቂ! ሳግ እየተናነቀው ተማፀናት፡፡ የህፃኑን ዋይታ እየሰለለች ሃይሏን እያጣችና እየቀነሰች ብትመጣም አንዳች አይሰቀጥጣት፣መንፈሱን የሚቧጥጥ ስሜት አስጨንቆታል አባትየውን፡፡

እኔኮ የህጻኑን ለቅሶ ስለሚያሳቅቀኝ ነው እዚህ ያላደርሁት፡፡ እባክሽ ነይ ውሰጅልኝ፡፡ እኔ እንዴት አባቴ አድርገዋለሁ አላውቅበትመኮ! እባከሽ ሁለተኛ አይለመደኝም…የሰማችው ቢሆንም ምላሽ ነፍጋው መንገዷን ቀጠለች ጮቂ፡፡ እሱም ተስፋ ቆረጦአፉን እንደከፈተ ቀረ፡፡

አንዳንድ ነዳያን በትዝብት ይሁን በሀዘኔታ፣ በግርምት ይሁን በማሽሟጠጥ… ባይገባውም ራሳቸውን ግራ ቀኝ አወዛወዙለት፡፡ በጮቂ ልብ ውስጥ ጥርጣሮውን የጠነሰሰችውም ጭምር ገና ድሮ ከእንቅልፏ ነቅታ ሁኔታውን በጥሞና ትከታተለው ነበር ለሱ እንዳዘነች ሁሉ በማስመሰል ከንፈሯን መጠጠችለት፡፡ እናም ምስኪኑና ደካማው አባዋራ ሆድ ብሶት በጸጥታ አነባ፡፡

የህፃኑ የሲቃይ ዋይታና የልብ ምት እየቀነሰ ሄዶ ፀጥ ቢልም አባት አለተረጋጋም፡፡ እንደገና በሚሰቀጥጥ ጩኸቱ መንፈሱን እንዳያወከው ካደረበት ስጋት የተነሳ አጥብቆ አቅፎታል፡፡ ጮቂ እውነትም ጥላው የምትሄድ፣ የማትመለስ ከሆነ ምን እንደሚያደርግ ግራ ገብቶታል፡፡ ጡት አያጠባው፣ ጡጦ የለ፤ ጥሬ አይቆረጥምም…

ምን አባቱ ይሞክረው!… ጮቂ ትብከነከናለች በበኩሏ- ፈጥና እየተራመደች፡፡ ገስግሳ ቴሌ አጠገብ እንደደረሰች ወደ ቀኝ ታጥፋ ወደ መድሀኒያለም ቤተ- ክርስቲያን የሚወስደውን ዳገት ተያያዘችው፤ ብቻዋን እያነበነበች፡፡

ምናባቱንስ ታቅፎ ይዋል፡፡እኔም መከራየን ሳይ ነው ያደርሁት፡፡ ደሞ እሱን ብሎ ባለ ሁለተኛ ሚስት! ወይ ጉድ ቆይ ብቻ- የአችን የቧንቧ ውሃ አይነ ስውር ላግኛት!

የመድኒያለም ዳገት የዋዛ አይደለም፡፡ ቢደክማትም ወደ ቤ/ክ መግቢያ ተቃረበች፡፡

እለቱ ሰንበት ስላልሆነ ምዕዋት ፈልጋ አልነበረም ያቀናችው፡፡ ስለተበሳጨች ከነበረችበት አካባቢ ለመራቅ እንጅ፡፡ ጮቂ ቤ/ክኑ መግቢያ ስትደርስ መግቢያው ግራናቀኝ ግንቡን ተገን አድርገው ማደሪያቸውን ካበጁች ነዳን ብዙዎቹ ነቅተው ከፊሉ ልብሳቸውን ሲሰፉ ከፊሉም ተባይ ይገድላሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የለመኑትን ምግብ ለቁርስ ሲያዘጋጁ ይታያሉ፡፡ በእዚህ ሁሉ ነገር መሃል የጮቄን አትኩሮት የሳበ ነገር አለ፡፡ በግራ በኩል ባለው ቦታ አንድ ነዳይ እግሩን ዘርግቶ ግንቡን ተደግፎ የአንዷን ነዳይ ራስ ደረቱ ላይ አስደግፎ ጸጉሯን ይዳስስላታል፡፡ ጮቄ አተኩራ ተመለከተቻቸው፡፡ ጮቄም በንዴት የጋለው ሰውነቷ እየቀዘቀዘ ሲሄድ ተሰማት፡፡ አልተሳሳተችም ሴትዬዋ የቧንቧ ውሃዋ አይነስውር ሰውየው ደግሞ ሰሞኑን ከቧንቧ ውሃ ሚስት እንዳጨ የነገራትና ደሴ ላይ ከረጅም ጊዜ በፊት የምታውቀው ነዳይ ነው፡፡…

ሰውየው ጮቄ እንዳያት ፈገግ አለና ሰላምታ አቅርቦ እንዳላስተዋውቃችሁ ትተዋወቃላችሁ አላት፡፡

ሴትዮዋም የጮቄ ስም ሲጠራ ቀና ብላ ፊቷን በፈገግታ ሞልታ ሰላምታ አቀረበችላት፡፡

ጮቄም በፍጥነት የመልስ ጉዞዋን ጀመረች፤ ቁልቁለቱን እየተንደረደረች በልቧ እየተጸጸተች በጓደኛዋ ከንቱና የድፍረት ወሬ እየተገረመች…

የጮቄን ተመልሳ መምጣት ሲያይ ባሏ ባለማመን አፈጠጠባት፡፡ ህፃኑ ግን ገና እሪታውን አቁሞ ፀጥ ቢልም እሱ ግን ግራ እንደገባው እንደተረበሸና ተስፋ እንደቆረጠ ተጨብጦ ከተቀመጠበት አልተንቀሳቀሰም- ህፃኑን ደረቱ ላይ አጥብቆ እንደታቀፈ፡፡

በቀጥታ ወደእሱ እየገሰገሰች አምጣ ልጅን ለራስህ ሳትሆን ለህፃኑ ትሆናለህ አለችው፡፡ ስሜቷ ተረጋግቶ ለስለስ ባለ አንደበቷ ፀፀቷንና እፍረቷን በሚያንፀባርቅ ቅላፄ፡፡

አጠገቡ እንደደረሰች የት እንዳደርክ ኃላ ታስረዳለህ፡፡ አሁን ልጁን አምጣ መጀመሪያ ለራስህ ስትሆን እሱን ታቅፋለህ፡፡

ትንፋሽ ሳያሰማ እንደ ፈዘዘ ህፃኑን ከእቅፉ ፈልቅቃ ወሰደችው፡፡ ከዚያም ወደ ደረቷ አስደግፋ አቀፈችው፡፡ ነገር ግን ህፃኑን ገና ደረቷ ላይ እንዳሳረፈችው ፍዝዝ ድንዝዝ ብላ ቀረች፤ ባሏ ላይም እንዳፈጠጠች፡፡ የታቀፈችው ህፃን ገላ ሙቀት የሚለግሳት የአካሏ ክፋይ ሳይሆን በጨርቅ የተጠቀለለ በረዶ እንደሆነ ሁሉ ከባድ ቀዝቃዜ አለበሳት፡፡ እንደደነዘች፣ እንደ ፈዘዘች የታቀፈችውን ነገር ወደፊት ዘርግታ አየችውና እሪታዋን አቀለጠችው፡፡… በማለዳው ቅዝቃዜ ፈዝዝያለው የነደያኑ ሰፈር እንደገና በዋይታ ታመሰ፡፡

መልመጃ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ወይም ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ጮቄ ከባሏ ጋር የተጣላችው በውሸት ወሬ ነው።
2. ጮቄ የአካል ጉዳት የለባትም።
3. የጮቄ ልጅ በምቾት ተይዟል።
4. ነዳይ ማለት በልመና የሚተዳደር ሰው ማለት ነው።

ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ተስማሚውን መልስ በባዶው ቦታ ሙሉ።

1. ከታሪኩ ምን ምን ቁምነገሮች አገኛችሁ----
2. በታሪኩ ውስጥ ስንት ባለታሪኮች አሉ----
3. ታሪኩ የተሰራበት አገር የት ነው-------
4. ታሪኩ የቀረበው በምን መልኩ ነው------

## 3.4 የዕይታ ጥበባት ታሪክ / የዋሻ ጥበብና ቀለም ቅብ መለየት

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፦

- የዕይታ ጥበብ ታሪክን በመረዳት የዘርፉን እንቅስቃሴና ውጤት በማህበረሰብ ዉስጥ ባለው የአስተሳሰብ ለውጥና አጠቃላይ የዕድገት እንቅስቃሴ ላይ ያለዉ አዎንታዊ አስተዋፅዖ ከፍተኛ መሆኑን በመረዳት ተሳታፊነትን ያዳብራሉ ።
- በአገራችን ዉስጥ ያሉ ማህበረሰቦችና በዓለም ላይ ያሉ የተለያዩ ነገራትን በዕይታ ጥበብና የዕደ ጥበብን ታሪክና ውጤቶችን ይገነዘባሉ።
- የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ በማዳበርና የባህሪ ለውጥ በማዳበርና በማምጣት በራሱ የሚተማመን ብቁ ዜጋ ይሆናሉ ።
- ታሪካዊ የሆኑ ቅርሶችን አስፈላጊነት በማስገንዘብ ሙዚቃዎችን ይጎበኛሉ
- የዕይታ ጥበብና የዕደ ጥበብ ውጤቶች ከታሪካዊ ፋይዳቸው አንፃር በሙዚየሞች ውስጥ ተቀምጠው የሚታዮትን ግልፅ የሆነ ገለፃ ያደርጋሉ ።

መምህር/ት ተማሪዎች የሀገራችንን የሥነ ጥበብ ሥራዎች በማን፣ መቼ እዴት ተሰሩ ለሚለው በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ይገኛሉ:: እነዚህ ሥራዎች የዓለም የጥበብ ሥራዎች አካል እንደመሆናቸው አጀማመሩም ተመሳሳይነት አለዉ:: ለእዚህ መርጃ የሚሆነው በቅድመ ታሪክ እይታ ጥበብ ሥራነት ከተመዘገቡት ሥራ መካከል በአዋሽ መልካ ቆንጠሮ ፣ በድሬድዋ አካባቢና በሲዳሞ ወናጎ በመባል በሚታወቀው ስፋራ በዋሻዎች ግድግዳ ላይ ተሰርተው የሚገኙት ሥዕሎች ይጠቀሳሉ :: እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች በየዘመናቱ በጥንታዊ ሰዓሊያን የዘመናዊው የዕይታጥበብ ዕውቀት በቀስሙ ሠዓሊያንና ቀራፂያን የተሰሩ ሥራዎች በየሙዚየሙ በየገዳማቱና ቤተ ክርስቲያናት በቅርስ አስባሳቢነት በሚታወቁ ታዋቂ ግለስቦች ቤት ይገኛሉ::

መምህር/ት ተማሪዎ በየዘመኑ የታሰሩ የሥነ- ጥበብና የዕዳ ጥበብ ውጤቶችን በስዕል በፎቶ ግራፍ እንዲሁም እንዳለው ተጨባጭ ሁኔታ ለሥዕላዊ መግለጫ ወይም በገለፃ የተደገፈ ቪዲዮ ማሳየት ይገባል ::

ሙዚየሞች የሥነ ጥበብ ማሳያ ጋለሪዎች የስነ ጥበባዊ ይዘት ያላቸው ታሪካዊ ቦታዎች የዕደ ጥበብ ውጤቶችና የስነ ጥበብ ዓውደ- ርዕዮች ታዋቂ የሆኑ የስነ ጥበብና የዕደ ጥበብ ባለሙያዎችና ስራዎችቸውን ለተማሪዎች ማስታዋወቅና ማሳወቅ::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ብዙ ሠዓሊያንንም ማፍራት ብቻ ሳይሆን በዓለማዊው ሥነ ሥዕልም ከፍተኛ ደረጀ ላይ ለደረሡ ሠዓሊያን መፍራት የበኩሏን አስተዋጽዖ አበርክታለች:: ኢትዮጵያ ሀገራችን የምትኮራባቸው ስመጥር

ሠዓሊያን በተለያዩ ጊዜያት ሲጠየቁ ለእነርሱ የሥዕል መሠረት ቤተክርስቲያን መሆኑን በኩራት ይገልጻሉ::





ሥዕል፡- ቤተ-ክርስቲያን ሥዕላት




ሥዕል፡-የዋሻ ቤተ ክርስቲያን

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።

1. በቅድመ ታሪክ በቅርስነት ከተመዘገቡት የዕይታ ጥበብ ሥራዎች

መካከል የትኞቹ ናቸው

ሀ/ በላሊበላ አከባቢ ለ/ በጎንደርና በአካባቢዎቹ ሐ/ በአዋሽ መልካ ቆንጠሮ፣ በድሬድዋ አካባቢ መ/ በሲዳሞ ወናጎ በመባል በሚታወቀው ስፍራ ሠ/ ሐ ና መ

2. በአካባቢ የሚገኙ ቅርሶች ፣ ሥዕሎች ፣ የዕደ ጥበብ ውጤቶች የትኞቹ ናቸውሀ/

በብራናና በጨርቅ ላይ የተሰሩ የቀለም ቅብ ሥዕሎች

ለ/ የድንጋይና የእንጨት ቅርፃ ቅርጾች ሐ/ የጦር ሜዳ መሳሪያዎች ጦርና ጋሻ

መ/ ጥንታዊ ሱሪና ቀሚሶች ከእንጨት ከብረታ ብረትና ሸክላ ሠ-ሁሉም

3. ቅርስ ያልሆነው የቱ ነው

ሀ/ ጎራዴና ሾተል ለ/ ካባ፣ በርኖስ፣ ለምድ ሐ/ ሀእናለ መ/ ሁሉም

ለምሳሌ በ20ኛው ክ/ዘ ከተነሡ ስዓሊያን መካከል አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ፣ አገኘሁ ወርቅ እንግዳ፣ እምአእላፍ ህሩይ ፣ አለፈለገ ስላም፣ አፈወርቅ ተክሌ እንዲሁም ገብረ ክርስቶስ ደስታ/አባቱ የቤተክርስቲያን ቄስ ሆነው ብራና በመደጎስ እውቀት የነበራቸው/ የነበሩት ሠዓሊያን ለእዚህ ተጠቃሽ ናቸው።



ስዕል1.1 ሰዓሊ አለ ፈለገ ስላም



ስዕል1.2 ሰዓሊ ገ/ክርስቶስ ደስታ



ስዕል1.3 ሰዓሊ እሸቱ ጥሩነህ




ስዕል1.4 እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሰዓሊ አፈወርቅ ተክሌ





ሰዓሊ እስክንድር በጎሲያን

የሰዓሊ እስክንድር በጎሲያን አካባቢ የሚገኙ ቅርሶች ፣ ሥዕሎች ፣ የዕደ ጥበብ ውጤቶች በተለያዩ ጊዜያት የተሰሩ የሀገር ቅርሶች ሥዕሎችና በቤታችሁ በሃይማኖት ቦታዎችና ሙዚየሞች ስለ ሚገኙ ቦታው ድረስ ሄዶ መመልከትና ማጥናት የሃገራችሁንና የአካባቢያችሁን የጥበብ ታሪክና የዕድገት ደረጃ ለመረዳት ያስችላችኋል።

በጉብኝታችሁ ወቅት ጥንታዊ የጦር ሜዳ መሳሪያዎች ጦርና ጋሻ ፣ ጎራዴና ሾተል ከአልባሳት ደግሞ ካባ፣ በርኖስ ፣ ላምድ ፣ እጀ ጠባብ ልዩ ልዩ የአሠፋፍ ዘዴ የሚታይባቸው ጥንታዊ ሱሪና ቀሚሶች ከእንጨት ከብረታ ብረትና ከሸክላ የተሰሩ ቁሳቁሶች በብራናና በጨርቅ ላይ የተሰሩ የቀለም ቅብ ሥዕሎች የድንጋይና የእንጨት ቅርፃ ቅርጾች ልትመለከቱ ትችላላችሁ እነዚህን ነገሮች በትኩረት በምታስተውሉበት ጊዜ በአብዛኛዎቹ ላይ የሥነ ጥበብ ሥራዎች ማለትም ዲዛይኖችና ሐረጎች ልዩ ልዩ ቅርፃ ቅርጾች አርፈውባቸው ለእይታ ውብና ማራኪ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል ።









ሥዕል፡- በጉብኝታችሁ ወቅት ጥንታዊ የጦር ሜዳ መሳሪያዎች ጦርና ጋሻ

## የምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ማህበረሰብ የሚጠቀምባቸውን መዝሙራት በመዘመር፣ ማህበረሰብ የሚጠቀምባቸውን የውዝዋዜዎች አይነቶች እስመስሎ በመወዛወዝ/በመከወን/፣ ስለ የሀገረሰብ ተረትና ታሪኮች በትረካ መልክ በመተረክ መማርና ማስተማር እንደሚቻል እና የዕይታ ጥበባት በዋሻ ውስጥ እንደተጀመረና ስለዋሻ ውስጥ የቀለም ቅብ ስራዎች የትና በየት እንደሚገኙ ስለአንዳንድ የዕይታ ጥበብ ባለሙያዎች ከሞላ ጎደል ማወቅ የቻልንበት ምዕራፍ ነው፡፡

## የምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ትክክል የሆነውን ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በቃል መልሱ፡፡

1. በ20 ኛዉ ክ.ዘ ከተነሡ ሥዐሊያን መካከል አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ፣ አገኘሁ ወርቅ እንግዳ፣ እምአእላፍ ህሩይ ፣ አለፈለገ ስላም፣ አፈወርቅ ተክሌ እንዲሁም ገብረ ክርስቶስ ደስታ ናቸው፡፡
2. የሀገራችንን የሥነ ጥበብ ሥራዎች የዓለም የጥበብ ሥራዎች አካል

እንደመሆናቸው አጀማመሩም ተመሳሳይነት አለዉ፡፡

3. በጉብኝታችሁ ወቅት ጥንታዊ የጦር ሜዳ መሳሪያዎች ጦርና

ጋሻ ፣የቀለም ቅብ ሥዕሎችና የድንጋይ፣ የእንጨት ቅርፃ ቅርጾች

# ምዕራፍ አራት

## ሥነ ውበታዊ ዕሴት (ዋጋ)

ማስተዋወቅ

### የምዕራፍ አራት መግቢያ

በዚህ በምዕራፍ አራት ላይ ትኩረት የተደረገው የአንድን ነገር በተለይ የውዝዋዝ የትያትርና የሙዚቃ ጥበባት መጠቀም ያለው ስነ-ውበታዊ ዋጋ /እሴት ምን እንደሆነ እና የሙዚቃ፣ የትያትር፣ የውዝዋዜ አንድነትና ልዩነት ላይ ትኩረት በማድረግ ለማስቀመጥ የተሞከረበት እና የዕይታ ጥበብና የዕደ ትበባት አስፈላጊነት፣ አካላዊ ጥቅሞችና የዕይታ ጥበባት ትምህርት የማስታወስ ችሎታ ያሻሽላል የሚሉት ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡

### 4.1 የሙዚቃ ጥበብ ሃሳብን ከውዝዋዜና ከቲያትር ጥበባት ሐሳብ ጋር ያለውን ልዩነትና አንድነት

ከተማሪዎች የሚጠበቀው  የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የክወና ጥበባት እንድነትና ልዩነት በውይይት ትረዳላችሁ፡፡

### 4.1.1.የውዝዋዜ ሃሳብን ከሙዚቃና ከቲያትር ጥበባት ሐሳብ ጋር ያለውን ልዩነትና አንድነት

ከተማሪዎች የሚጠበቀው  የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ስለውዝዋዜ በሚገባ ትረዳላችሁ

ውዝዋዜ  በማህበረሰቡ በጋራ በአንድ ስልተ ምት የሚደረግ የአካል እንቅስቃሴ ላይ ያተኮረ  የሚገለገሉበት የጥበብ ሙያ ነው፡፡

#### ልማዳዊ የሃገረሰብ ውዝዋዜ

በአካባቢ ውስጥ የሚከናወኑ ማህበረሰቡን በጋራ የሚያስማሙ፤ በጋራ የሚከወኑ የድርጊት (ክዋኔ) ናቸው፡፡

መልመጃ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ ስጡ።

1.ወዝዋዜ ልማዳዊ ክዋኔ ነው።

2.ውዝዋዜ ለክብረ በዓላትና ፌስቲቫሎች አድማቂና ስሜት መግለጫ ነው።

### 4.1.2.የቲያትር ሃሳብን ከሙዚቃና ከውዝዋዜ ጥበባት ሐሳብ ጋር ያለውን ልዩነትና አንድነት መወያየት

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ስለክውን ጥበባት ተውቃላችሁ
- እደጥበባዊ ባህላችን ትረዳላችሁ
- ባህላዊ ምግቦቻችን ታውቃላችሁ።

በአንድ አገር ወይም አካባቢ ውስጥ የሚከናወኑ እና በውስጣቸው ባለው ይዘት እንዲሁም ማህበረሰቡን በጋራ የሚያስማሙ፣ በጋራ የሚከወኑ ከትውልድ ወደ ትውልድ በድርጊት (በክዋኔ) ወይም በመተወን የሚተላለፉ ናቸው። ሃገረሰባዊ ትወና ጥበባት ብለን በጥቅል ስም የምንጠራቸው ሃገረሰባዊ ሙዚቃዎችን፣ ሃገረሰባዊ ዳንሶችንና ሃገረሰባዊ ድራማዎችን የሚያጠናውን ሙያና የሚጠኑትን ነገሮች ነው።

ዳንስ፣ ሙዚቃና ድራማ በክዋኔ ውስጥ ለየብቻቸው የቆሙ ሳይሆኑ አንዱ በአንዱ ውስጥ የሚገኙና እርስበርስ የተሳሰሩ ናቸው።

ለምሳሌ፡- ሃገረሰባዊውን ዘፈን ብናነሳ ዜማ፣ ግጥም፣ ምልልስ፣ ገፀ- ባህርያትን፣ የቁጥር መመጣጠንን እና እስክስታን በአንድነት ሲከወኑ ታያላችሁ።

## የመልመጃ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ ከሃገረሰባዊ ክውን ጥበባት ውስጥ የማናገኘው የቱን ነው?ሀ. ሽለላ ለ. ስዕል ሐ. እስክስታ መ. መልስ የለም
2. ከሚከተሉት አንዱ ሃገረሰባዊ ጥበብን አይገልፅም፡፡
   ሀ. ታሪክን አይነግርም ለ. ሀዘንን ይገልፃል ሐ. ፈጠራን ያሳያል መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡
3. ሀገረሰባዊ ክውን ጥበባት የምንላቸው---
   ሀ. ሙዚቃ ዳንስ እና ድራማን ይይዛሉ ለ. ባህላዊ ተግባራት ናቸው ሐ. ከተውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋሉ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

## ሀገረ ሰባዊ ልማዶች

በማህበረሰቡ ውስጥ ልማዳዊ በሆነ መንገድ በተደጋጋሚ የሚተገበሩ ክዋኔዎች ሲሆኑ ለማህበረሰቡ አካላዊ ስነ-ልቦናዊና መንፈሳዊ (እምነታዊ) ጠቀሜታን ያስገኛሉ፡፡ በእነዚህ ልማዶች ውስጥ የተለያዩ ክብረበዓላትና ፌስቲቫሎች፣ መዝናኛዎችና ጨዋታዎች፣ ሃገረሰባዊ መድሃኒቶች፣ እንዲሁም ሀገረሰባዊ እምነቶች ተካተው ይገኛሉ፡፡

ለምሳሌ፡- ከሀገረሰባዊ ጨዋታዎች ብናይ፡ የትግል (መጣጣል) ጨዋታን፣ የዱላምከታን፣ ብይ ጨዋታን፣ ገበጣ ጨዋታን፣ የዝላይ ጨዋታን፣ ገና ጨዋታን… ወዘተ. መጥቀስ ይቻላል፡፡

ሃገረሰባዊ እምነትን ስንመለከት፡ የተለያዩ ህልም አፈታቶችን፣ ከእድል ጋር የሚገናኙ እንደ የእጅ መዳፍ ማሳከክ፣ እግርን እንቅፋት ሲመታ፣ እና ምላስ ሲነክስ ሰው እያነሳኝ ነው ብሎ ማሰብን… ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡

ሃገረሰባዊ መድሃኒትን ብናይ ደግሞ፡ ከተለያዩ የእፅዋት ስራስሮችና ቅጠላቅጠሎች የሚቀመሙና ለተለያዩ በሽታዎች እንደ ትኩሳት፣ ራስ ምታት፣ ምች፣ ጉንፋን ለመሳሰሉ በሽታዎችን … ወዘተ. ለማዳን ይጠቅማሉ፡፡

ተማሪዎች እናንተም ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ የተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎችን፣ እምነቶችንና ባህላዊ መድሃኒቶችን ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

በአካባቢ ውስጥ የሚከናወኑ ማህበረሰቡን በጋራ የሚያስማሙ፤ በጋራ የሚከወኑ የድርጊት (ክዋኔ) ናቸው፡፡ ከእነዚህ በጥቂቱ ዜማዎች (ሙዚቃዎች) ፣ ባህላዊውዝዋዜዎች የአነጋገር ልሳኖች፤ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፤የኑሮ ዘይቤዎች ፤ፀጉር አሰራር ያመለክታል፡፡

### ልማዳዊ ክዋኔዎች

ልማዳዊ በሆነ መንገድ በማህበረሰቡ በየጊዜው የሚተገበሩ ክዋኔዎች የአንድነት ተግባቦትን የሚፈጥሩ የጋራ እንቅስቃሴዎች ናቸው ፡፡ በእነዚህ ልማዶች ውስጥ አለማዊ መዝናኛዎች ስነ ስርአት መንፈሳዊ ክዋኔዎች የክብረ በዓላትና ፌስቲቫሎች፣ጨዋታዎች (ገና፣ ነፃ፣ ትግል፣ ገበጣ) ፣ባህላዊ የህመም ፈውስ መድሀኒቶች፣እምነቶች፤የስም አወጣጦች፤ከብዙ በጥቂቱ ናቸው፡፡

### የመልመጃ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ደግሞ ሃሰት በማለት መልሱ፡፡

1. የዶሮ ወጥ የኢትዮጵያ ባህላዊ ምግብ አይደለም፡፡
2. ባህላዊ መድሀኒቶች አብዛኛውን ጊዜ ከእፅዋቶች ይዘጋጃሉ፡፡
3. ጥቁር መልበስ በአብዛኛው የአገራችን አካባቢ ደስታን የምንገልፅበት ልማዳችን ነው፡፡
4. ጢያ ትክል ዲንጋይ በጉራጌ አካባቢ ይገኛል፡፡

## 4.2.የዕይታና እደ ጥበባት አስፈሊጊነት በማህበረሰብ ውስጥ

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁብ ኂላ፡-

- የዕይታና እደ-ጥበባት ልዩ ነትና አንድነት ትለያላችሁ፡፡

የእይታ-ጥበባት እንቅስቃሴዎች ልምዶችን ሀሳቦችን ስሜቶችን በሚታይና በተጨባጭ መንግድ በማደረጀት የሚከወን ክንዋኔ በመሆኑ ለፈጠራና ለስነውበት አድናቆትን ከመስጠት ባሻገር የአስተሳሰብ አድማስን ያጎለብታል የማስተዋል ግንዛቤን ይጨምራልበሁሉም የስርአተ ትምህርት ዘርፎች የትምህርቱ ሂደት በቀላሉ ሊረዱበት በሚያስችል መልኩ ዕንዲሆን ያደርጋል ፤ የቋንቋ እድገትና ለግል ማንነት ክብር የሚሰጠው ይሆናል የስሜት ህዋሳትን ፍላጎትና ደስታ ይሰጣል ማህበራዊ ክህሎቶችን ያስፋፋል፡፡

ለምሳሌ፡- በዚህ ጥበብ ሀገራችን ውስጥ ከተላለፉልን ድንቅ ቅርሶች መካከል የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን፣ አልነጃሽ መስጊድ፣ ፋሲለደስ ቤተመንግስት፣ አክሱም ሀውልትና የጢያ ትክል ድንጋይ ከብዙ በትቂቱ ይጠቀሳሉ፡፡

ቅድመ ዕይታእና ጥበባት ስዕላዊ መግለጫ





ተማሪዎች የሚከተሉትን የዕይታና እደ ጥበባት አስፈላጊነት በማህበረሰብ ውስጥያልውን ፋይዳ መምህራችሁ የሚያደርጉላችሁን ገለጻ በንቃት ተከታተሉ።

በአዕምሯዊ የፈጠራ ጥበብን በመጠቀሞ ስሜትን ከሃሳብ ጋር በማጣመር በልሳንወይም በቃላት ሊገለፁ የሚችሉ ሃሳቦችን በእጅ ጥበብ ቁሶችን በመጠቀም ቅርፆችላይ የማስፈር ማንነት መግለጫ ነው።

በእደ ጥበብ ባህል ከሚጠቀሱት ባላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ስራዎች ለምሳሌ ክ

በቁሳዊ ባህል ውስጥ ከሚጠቃለሉት ውስጥ ሃገረሰባዊ የእጅ ስራ፣ ሃገረሰባዊ ብረታብረትስራ፣ የሸክላ ስራ፣ ሽመና፣ የቆዳ ስራ፣ ሃገረሰባዊ ቤት አሰራር፣ ድንጋይ ጠረባ፣እንዲሁም የሃገረሰባዊ ምግብ አሰራር ዋና ዋናዎቹ ናቸው።





ሥዕል ፡-ተማሪዎች የዕይታጥበባት ሲሰሩ

### 4.2.1 አካላዊ ጥቅሞች

ጥሩ የዕይታ ጥበብ እና የእጅ ሥራዎች ክህሎቶችን ማዳበር አብዛኛዎቹ የዕይታ ጥበብእና የእጅሥራዎች አእምሮ እና እጃችን ያካተቱ እንቅስቃሴዎች በመሆናቸው ጥሩክህሎቶችን ለማዳበር ይረዳሉ። በእርሳስ መንደፍ ብሩሽ ቀለም መቀባት ያሉ ቀላልእንቅስቃሴዎች ጡንቻዎችን ለማጠንከር እና አእምሮ እድግትን ለማሻሻል ጉልህ ሚና አለው።

### 4.2.2 የእይታ ጥበባት ትምህርት የማስታወስ ችሎታ ያሻሽላል

አንዳንድ ለጆች በአዳዲስ ቀለሞች እና ቅርጾች በኪነ ጥበብ እና እደ ጥበባት ይማራሉ።እንዲሁም ከተለያዩ ችሎታቸውን እና ዘይቤዎች ጋር ይተዋወቃል። እንደ ሽመና መማር፣የሸክላ ሥራ፣ወዘተ ያሉ እንቅስቃሴዎች ውስብስብንድፎችን በአዕምሯዊ እይታጥበብ በማስታወስ ይሰራሉ ቅርፆች ላይ የማስፈርማንነት መግለጫ ነው።





ሥዕል፡- የዕይታ ጥበብ እና የእጅ ሥራዎች ክህሎቶችን ማዳበር

መልመጃ 1፡

ቀጥሎ የተቀረቡትን ጥያቄዎች፣በአዳመጣችሁት ገለፃ መሰረት፣ትክክል የሆነውን‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በቃል መልሱ፡፡

1 የእደ ጥበብ ውጤቶች ለማህበረሰብ አገልግሎት አይውልም ፡፡

2 የእደ ጥበብ ውጤቶች ሀገር በቀል ናቸው ፡፡

3. የዕይታናእደጥበባት መማር አሰፈላጊነት አለው፡፡

4. በትምህርት ቤት ውስጥ የዕይታ ጥበብ እና የእደ ጥበብ ሥራዎች አንዱ አካላዊ ጥቅሞች ነው፡፡

5 የዕይታ ጥበብ እና የእደ ጥበብ ሥራዎች አእምሮን ያነቃቃሉ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ገልጻ

•የዕይታ-ጥበብ እውቀቶችንና እደጥበብ አሰራርና  ቅርሶችን ማድነቅ ትማራላችሁ፡፡







ሥዕል፡- እደጥበብ እውቀቶችና ቅርሶች

### መልምጃ 2

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

ሀ. እደጥበብ እውቀቶች የምንላቸው ጥቀሱ?

ለ. ስለቅርስ ጥቅሞች ወይም ዓይነቶች የምታውቁትን አብራሩ?

መልመጃ 3፡-

ቀጥሎ በ‹‹ሀ›› ረድፍ በምንባቡ ላይ ያሉ አንቀጾች ቅደም ተከተል የቀረቡ ሲሆን በ‹‹ለ›› ረድፍ ከቀረቡት የየአንቀጾቹ ዋና ዋና ሀሳቦች ጋር በማዛመድ መልሱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የዕይታ -ጥበብ | ሀ. ሐውልቶች ባህላዊና ሃይማኖታዊ ትሪዒት ዋሻዎች፣ ሃይማኖታዊ ተቋማት....ወዘተ |
| 2. በእደ-ጥበብ | ለ. ሥዕል፣ ቅርጻቅርጽ፣ ህትመት....ወዘተ |
| 3. ባህልንና ቅርሶች | ሐ. ሸክላ ስራ፣ ሽመና፣ ስፌት |

መልመጃ 4፡-

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄበ መምረጥ መልሱ፡፡

1 ቅርስ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ላሊበላ ለ. ሶፉመርዋሻ ሐ. አክሱም መ. ሁሉም

2 በዕይታ -ጥበብ የገለጸው ምን በማድረግ ነው?

ሀ. በሥዕል ለ. በቅርጽ ሐ. በፎቶ መ. ሁሉም

3 እደ-ጥበብ ለምንድን ነው በሀገራችን ትኩርት ያጣው?

ሀ. የግንዛቤ ጉለት ለ. በትምህርት ስላልታገዝ

ሐ. አድካሚነቱ ከገቢው ጋር አለመመጣጠን መ. ሁሉም

ክፍል ሦስት፡-የፈጠራ ችሎታችሁን የምታዳብሩብትን ዘዴ ታሳያላችሁ።






ሥዕል ፡-ተማሪዎች የእደ-ጥበብ ፈጠራ ሲሰሩ

## ማጠቃሊያ

በዚህ ምዕራፍ የሙዚቃ ጥበብ ሃሳብን ከውዝዋዜ እና ከትያትር ጥበባት ጋር ያለውን ዝምድና /አነድነት/እና ልዩነት ምን እንደሆነ በውይይት ያየንበትና ሦስቱንም የጥበብ ዘርፎች /ሙዚቃ፣ትያትርነ ውዝዋዜ/የማይነጣጠሉና የአንዱ መኖር ለአንደኛው ውበት እንደሚሆን የዕይታ ጥበብ በማህበረሰቡ ውስጥ አስፈላጊና አካላዊ ጥቅም የማስታወስ ችሎታን እንደሚያሻሽል በግልፅ ተቀምጧል።

# ምዕራፍ አምስት

## ጥምርታ ዝምድናና ትግበራ

### ምዕራፍ አምስት መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ በትኩረት የተገለጸውና በተግባር የተደገፈ አቀራረብ የሚታይበት ሲሆን በዋናነት ክ.ዕ.ጥ./የክወናና የዕይታ ትበባት/ከሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ጋር ያለውን ጥመርታ፣ ዝምድናና ትግበራ ላይ የሚያተኩር ሲሆን ዝርዝር ይዘቶቹ የትራፊክ፣ የኤች አይቪ. የአደንዛዥ ዕፅ ወዘተ… የሚገልፁ /ድንበር ተሻጋሪ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን ከመዝሙር /ከሙዚቃ/ ከውዝዋዜ፣ ከትያትር፣/ተውኔት/ እና የአካባቢው አቅጣጫ ማሳያ ምልክቶች/አርማ እና የተለጠፉ ማስታወቂያ ወይም ፖስተር፣ ቅድመ ዕይታ የንግድና ተዛማጅ ተዛማጅ ዘርፍ ያላቸው ድርጅቶች አርማዎች ስለ መንገድ ዳር የትራፊክ ጠቋሚ ምልክቶች በዝርዝር የተቀመጡበት ምዕራፍ ነው፡፡

## 5.1.የትራፊክ፣የኤች አይቪ ኤድስ፣የአደንዛዥ ዕፅ፣ወዘተ. የሚገልፁ/ድንበር ተሻጋሪ ዘርፍብዙ ጉዳዮችን/፣መዝሙራትን ማጣመር

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት ይህን

ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ከምንም በላይ ለጤንነታቸው ቅድሚያ መስጠትን ትራዳላችሁ፡፡
- ራሳችሁን ካላስፈላጊ አደጋ ትጠብቃላችሁ፡፡
- ወደአፍ የሚገቡና የማይገቡ ጎጂ ነገሮችን በሚገባ በማወቅ ትለያላችሁ፡፡

የታፊክ አደጋ በአጋጣሚ በተወሰነ ቅፅበት ውስጥ ሊከሰት የሚችል ስለሆነ እራሳችሁንከአደጋው ለመከላከል የትራፊክ ደህንነት መርሆችን በሚገባ ማክበር ይጠበቅብናል ከነዚህም ውስጥ፦

- መንገድ ስናቋርጥ ግራና ቀኝ መመልከት፣
- ተደርቦ በቆመ መኪና ተከልሎ ለመሻገር አለመሞከር፣
- በእግረኛ ማቋረጫ መሻገር፣
- መኪና ላይ ከኃላ አለመንጠልጠል የመሳሰሉት ናቸው፡፡

መዝሙር

<u>አሽከርክር ረጋ ብለህ</u>

ሁሌም ረጋ ብለን በትዕግስት እንንዳ
ሕይወት እንዳንቀጥፍ አካል እንዳንጎዳ x2
ከባድ ሃላፊነት እንዳለብን አውቀን
ሁልጊዜም ስንንዝ ይሁን ተጠንቅቀን
መፍጠንና መቅደም አይደለም ችሎታ
ትግስት እንላመድ ሲኖረን እርጋታ
ሁሌም ረጋ ብለን በትግስት እንንዳ
ሕይወት እንዳንቀጥፍ አካል እንዳንጎዳ x2
ለእግረኛ ቅድሚያ እንስጥ በየመታጠፊያው
አደጋው ይቀንስ የሰው ህይወት መጥፊያው
ሴቶችና ህፃናት አረጋውይኑ
በመኪና አደጋ ከማለቅ ይዳኑ
አትቸኩል ረጋብለህ ረጋብለህ
አትቸኩል ትደርሳለህ ዘና ብለህ x2
ልጆችህን አስብ ትዳርህን አስብ
ልጆችሽን አስቢ ትዳርሽን አስቢ x2
ሁሌም ረጋ ብለን በትግስት እንንዳ
ሕይወት እንዳንቀጥፍ አካል እንዳንጎዳ x2
እያሽከረከርን እንዳንዘናጋ
በቸልተኝነት ይደርሳል አደጋ

አይገኝምና ህይወት እንደዋዛ

መቼም ይሁን የትም ለህግ እንገዛ

ሁሌም ረጋ ብለን በትግስት እንንዳ

ሕይወት እንዳንቀጥፍ አካል እንዳንጎዳ x2

ከአልኮል ከአደንዛዥ ዕፅ ከሱስ ሁሉ ፀድተን

ድካም እናስወግድ በቂ እንቅልፍ አግኝተን

ፋታ ያጣ ሹፌር ሁሌም ይዘናጋል

ሰላማዊ ኑሮን በድንገት ይናጋል

አሽከርክር ረጋብለህ ረጋብለህ

አትቸኩል ትደርሳለህ ዘና ብለህ x2

ልጆችህን አስብ ትዳርህን አስብ

ልጆችሽን አስቢ ትዳርሽን አስቢ x2

ግጥም ሞገስ ተካና ይልማ ገብረአብ
ዜማ ሞገስ ተካ






## ኤች አይቪ ኤድስ

የሰውነትን በሽታ መከላከያ በተለይ የነጭ ደም ሴሎችን (ህዋሳትን) በማጥቃት በቀላሉ ሰውነት ለበሽታ እንዲጋለጥ የሚያደርግ ቫይረስ ነው። ኤች አይ ቪ የሚያጠቃው የሰውነት የነጭ የደም ሴሎችን የሰውነት የበሽታ የመከላከያ ተቋማትን ነው።ኤች አይ ቪ ቫይረሱ ከሰውንት ከወጣ በኂላ በጣም ደካማ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ አይቆይም ወዲያውኑ ይሞታል። በዚያ የተነሳ ነው ኤች አይቪ ከማንም ሰው ጋር በምናደርጋቸው የዕለትተዕለት እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ፣ እንደ እጅ መጨባበጥ፣ መተቃቀፍ እና መሳሳም ሊያስተላልፉ እንደማይችሉና በተጨማሪም ኤች አይቪ በመጸዳጃ ቤት መቀመጫ፣በበር መኽፈቻ፣ በብርጭቆ መጠጫ፣ በምግብ ወይም በማንኛውም አይነት እንስሳእንደ ቢንቢ ንክሻ በመሳሰሉት ሊተላለፍ አይችልም።

ጤንነትን ከሚያዛቡት ዋናው በአላስፈላጊ ሱስ መጠመድ ነው። ሱስ በሁለት መንገድ ልንጠቃ እንችላለን።

በአፍ ወደ አካላችን የሚገቡ ዕፆች በከፍተኛ ደረጃ አዕምሮን በመቀየር ጭንቀት፤ጊዜያዊ ደስታ፤የስሜት መታወክ ፤የአዕምሮን መረጃ በማዛባት የመሳሰሉትን ከመፍጠራቸው ባሻገር የተክለ ሰውነት ቁመናን ያበላሻሉ:: ይህን ተጠቃሚ ሰውበነርቭ፤በጭንቀት፤ሃይለኛ ራስ ምታት፤በአጠቃላይ ራስን ለመግዛትም ሆነ ለመቆጣጠር አያስችልም ከሰውነት ጉዳት አልፎ በህይወት ላይ የሞት አደጋ ያስከትላል፤ ቤተሰብ ይበትናል ፤ከስራላይና ከትምህርት ላይ መገለልን ያስከትላል ፤በርካታ ማህበራዊ ቀውሶችን ያስከትላል::

የዕፁ ተጠቃሚ የሚያሳያቸው ባህሪያት ድካም፣እንቅልፍ ማጣት፣ ግልፍተኝነት፣ ከቤተስብመራቅ፣ የአመጋገብ መዛባት፣ ገለልተኝነት፣ ገንዘብ ማባከን፣ ትኩረት ማነስ፣ የማስተዋልችግር፣ ተስፋመቁረጥ፣ ጎልተው ይታይባቸዋል::

በዚህ በሽታ የተጠቁ ሰዎች አስፈላጊው ህክምና ከተደረገላቸው ወደቀድሞው ጤንነታቸው ይመለሳሉ::

ባአፍ የማይገቡ ሱሶች፦

- ቁማር፣አላስፈላጊ የገንዘብ፣የሃብት ብክነትን ከሚያስከትሉት ዋናዎቹ ናቸው::
- ማህበራዊ ድህረ ገፅ በዚህ ሱስ ከሚያስከትሉት የጤና ችግርመጨነቅ፤ድባቴ፤የትምህርት መከታተል መቀነስ፤ጠቃሚ የሆኑ ዕወቀቶችንለማግኘት ምንባብን ማቋረጥ ናቸው::

ቅድመ ጥንቃቄ

እረጋ ብሎ ማሽከርከር ፤ከኤች-አይቪ መከላከል ፤ጠንቅና እያለሳለሰ ስውን ከሰው በታችከሚያደርገው ሱስ ፤ መጠበቅ ቤተሰብን ከችግር ንብረትን ከውድመት የሀገር ኤኮኖሚንከክስረት ማዳን ነው::

## መልመጃ

I.ከዚህ በታች ለተሰጡት ጥያቄዎች ትክክለኛው መልስ የያዘውን ሆሄ ምረጡ::

1. የትራፊክ አደጋን ከማያስከትሉት አንዱ ያልሆነው

ሀ.መረጋጋት ለ.ፍጥነት ሐ.ግራናቀኝ አለመመልከት መ.መንገድ መጣስ

2. አፍ የማይገባ ሱስ ከሚያስከትላቸው ጉዳቶች

ሀ.የጊዜ ብክነት ለ.አንድ ቦታ መጠመድ ሐ.ጭንቀት መ ሁሉም

3. ሱስ የአእምሮ መዛባትን ያስከትለል ስንል

ሀ. አለማሰብን ለ. መቆጣጠርን ሐ. መተውን መ. መ/የ

4. ኤች አይቪ በሽታ ይበልጥ የሚያጠቃው የሰውነት ክፍል የሆነው ይቱ ነው

ሀ. አጥንት ለ. ነጭ የደምሴል ሐ. ልብ መ. አይን

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ሐሰት በማለት መልስ ስጡ

1. ረጋ ማለት የአዋቂነትና የብስለት ውጤት ነው፡፡

2. ወደ አፍ የሚገባ ሱስ የፊት ገፅታን ከሚያበላሹት አንዱና ዋነኛው ነው፡፡

3. በእግረኛ ዜብራ መንገድ ማቋረጥ ህግን ማክበር ነው፡፡

### 5.1.1 የትራፊክ፣የኤችአይቪ፣የአደንዛዥ ዕፅ፣ወዘተ… የሚገልፁ/ድንበር ተሻጋሪ ዘርፍ ብዘጉዳዮችን/ውዝዋዜ ማጣመር

ውዝዋዜ መድረክ ላይ ለሚከወኑ አስተማሪ በሆኑ መድረኮች ከሙዚቃው ጎን ለጎን መልእክቶች በከካል እንቅስቃሴ የሚገለፅበት ነው፡፡

አላማ

በውዝዋዜ ጤንነትን ሊጎዱ ከሚችሉ ነገሮችን በቅድሚያ መጠንቀቅ እንዳለብን ገላጭ መሆኑን ማሳወቅ፡፡

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ለጤንነታችሁ ቅድሚያ መስጠትን ትረዳላችሁ
- ስለትራፊክ አደጋ መከላከል የተዘጋጀ መዝሙር ላይ ያለውን ውዝዋዜ ትሰራላችሁ።
- ሰለሱስ ጎጂነት ገላጭ የሆኑ አስተማሪ ውዝዋዜዎችን በጋራ ትሰራላችሁ።

የውዝዋዜ መልእክት ገላጭነት

ውዝዋዜ የሀገር መልካም ገፅታን ገላጭ ከሆኑት ከባህል ክፍሎች መካከል አነዱ ነው ከዚህም አልፎ ለምሳሌ ስለ አንድነት ፣ትምህርት ፣ማንበብና መፃፍ ፣ብሄርብሄረሰቦች ስለግብርና ወዘተ በመሳሰሉት መልእክት ገላጭ ነው።

### 5.1.2 የትራፊክ፣የኤች አይቪ፣የአደንዛዥዕፅ፣ወዘተ... የሚገልፁ/ድንበር ተሻጋሪ ዘርፍ ብዙ ጉዳዮችን/ተውኔት ማጣመር

ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመማር ውጤት

ይህን ትምህርት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ታሪኩን ታነባላችሁ።
- የተረዳችሁትን ታብራራላችሁ።
- የገፀ- ባህርያትን ማንነት ትገልፃላችሁ።
- ታሪኩን አስፋፍታችሁ ትፅፋላችሁ።
- ቃለ- ተውኔቱን በአእምሯችሁ በመያዝመድረክ ላይ ታቀርባላችሁ።

እሳትና ውሃ

በዚህ አጭር ተውኔት ውስጥ በተለያየ አይነት አስተሳሰብና አመለካከት የሚጓዙ አገር አፍራሽ፣ ክፍተት ጠጋኝና አገርን አራማጅ ገፀ- ባህርያት በሀገራቸውና በህዝባቸው ላይ ሲነሱና ለችግሩም ሆነ ለመፍትሄው የራሳቸውን አሻራና የታሪክ ጠባሳ ሲያኖሩ ይታያል፡፡

ገፀ- ባህርያቱም፡-

አሸብር፡ ውሸት ነጋሪ

አብላላው፡ ወሬን ከወዲያወዲህ የሚረጭበለው፡ የዘረኝነት መንፈስ የተጠናወተው

መርምር፡ ታገስ ተመለስ የሚል ውሸትና እውነቱን የሚያስረዳ

ምንግዴ፡ ምንም ቢፈጠር የማይገዳት አስመሳይና በነፈሰው አብራ የምትነፍስ እና

ደኛው፡ አቅጣጫ አመላካች መሪ ሆነው ቀርበዋል፡፡ ዘመኑ አሁን ያለንበት ሲሆን ቦታው ኢትዮጵያ ነው፡፡

አሸብር ወሬ አነፍነፎ ስላጣ የውሸት ወሬ በመፍጠር መራገብ ጀምሯል፡፡

አሸበር፡ አንዷን አህያ የዳብን አካባቢ ነዋሪዎች ከሲገት አካባቢ ነው የመጣች በማለት ለአምስት ቀናት ያለማቋረጥ ሶስት መቶ ኩንታል ስለጫኗት አረፋ ደፍቃ ሞተች፡፡

አብላላው፡ ይህማ ፖስት መደረግ አለበት፡፡

በለው፡ የእነሱ አህያ እየፈነጠዘች የኛን አህያ በግፍ ገደሏት፤ ወይኔ ሰውየው እውነታቸውን ነው ወንድ አጡብና በቁም ሞተናል!

ምን ግዴ፡ ይኸው የፈራሁት አልቀረም ነገ ደግሞ እኛን ያሸክሙናል ተው ያገሬ ወጣት ተነስ፡፡

መርምር፡ አገራችን እኮ መሪ አላት የምን ግንፍል ግንፍል ነው ተረጋጉ ሳታጣሩ እሳት አትጫሩ፡፡

አሽብር፡ እሱም ተላላኪ ከሀዲ ነው እንዳትሰሙት፡፡ ከፈለጋችሁ ከአሁን በፊት ከዳብን መሪ ጋር ተቃቅፎ የተነሳው ፎቶ ይሄውላችሁ፡፡

አብላላው፡ አያችሁት ይሄን ጉድ እስቲ ፎቶውን ተመልከቱት ተቃቅፈው እየዶለቱ፡፡

በለው፡ ይህ ጉዳይ ዘርን መሰረት ያደረገ ጥቃት ነው፡፡

ምንግዴ፡ አያችሁት ሲዝት!

መርምር፡ ተው ይህ ጉዳይ ይጣራ?

አሽብር፡ አያችሁት ሲከላከልላቸው፡፡

በለው፡ በቃ! ይበቃል ከዚህ በላይ ከመደፈር መሞት ይሻላል፡፡

ምንግዴ፡ እና! ሞክረና! ባለጌ ደሞ ይዝታል እንዴ፡፡

በለው፡ ይኸው አንዷን አህያ ሶስት አርገን ብድር መልሰናል፡፡

ምንግዴ፡ እንዲያ ነው ነገሩ እንመጣልሃለን በተወለድንበት ትገነዛለህ፡፡

አሽብር፡ እዩት ምንግዴን መጣን እያለች ነው፡፡

በለው፡ እና ማን ይፈራል ታዲያ ኑና ይለይልና፡፡

አሽብር፡ የነምንግዴ ማህበረሰብ ሰላሳ የበለውን ዘሮች ገደለ፡፡ (የውሸት ፎቶ ይለጥፋል፡፡

በለው፡ ዝመት ህዝቤ ሆይ! ሚስትህ እየተደፈረች፣ ወንድሞችህ እየታረዱ፣ልጆችህ እየሞቱ ነው፡፡

አሽብር፡ የእነ በለው ብሄረሰብ የእነ ምንግዴን ዘር መቶ መቶ ገድለው ተበቅለዋል፡፡ (ፎቶይለጥፋል)

መርምር፡ ይህ ፎቶ የአሁን አይደለም፡፡ በድሮ ጊዜ ሌላ አገር የተፈጠረ ነው፡፡

አሽብር፡ ውሸት አያችሁት ዘር ለማጥፋት አብሮ ሲደራጅ፡፡

ምንግዴ፡ ጀግና ከሆናችሁ ይሄ ሬሳችሁ ኑና ቅበሩ፡፡

አሸብር፡ እግዞ ተጨራረሱ ተመልከቱ አካባቢው ሁሉ በሬሳ ተሞልቷል፡፡

ዳኘው፡ ተው የአገሬ ህዝቦች ለውጣችን የከነከናቸው የሚሰጡንን የእልቂት ሃሰብ ተው ለጥፋት አትመቻቹ፡፡

አሸብር፡ እሱ የእነምንግዴ ዘር ስለሆነ አዘናግቶ የነበለው ዘር ለማስጨረስ ነው፡፡

በለው፡ አዎ ነቅተንበታል ጎበዝ እንዳታመነቱ አናት አናቱን ምቱ፡፡

ምንግዴ፡ ተው ባክህ ወንበዴ የኔን ብሄር መቸም አታውቀውም እሽ፡፡

መርምር፡ ካሁን በፊት የተፈጠረውን አስቡ ሌላ የጋራ ጠላት እየመጣብን ነው፡፡

አብላላው፡ ሰበር ዜና የእነ በለውን ማህበረሰብ የሚረዱ የውጭ ሃይሎች መኖራቸው ተረጋገጠ፡፡

ዳኘው፡ ይች የፀጋ ምደር ይሽ ለምለም አፈር፤

ሳላስከፋን ብሎ ባይፀናብን ችግር፡፡

አገር እንዳንመራ፤

ሰርተን እንዳንኮራ፡፡

ተንኮል ጋርደውብን፤

እውነቱ ጠፍቶብን፡፡

እሾሁን አንስተን፤

በራችንን ከፍተን፤

ለባዕዳን ሰጥተን፤

ባፈር ስንጫወት አቧራው በኖብን መች እኛ እናያለን፤

ጉድፍ እንደሚያወጣ እፍእፍ ስንባባል ጠፍተን እናልቃለን፡፡

አለ ገጣሚው! ሰዎች በአህያ የጀመርነው የጎጠኝነት ችግር ከእንስሳት በታች እንድናስብ አድርጎናል፡፡ በራችንን አጥረን አእምሯችንን አጥረን በሰፈር እንድንደራጅ አርጎናል፡፡

መርምር፡ ልክ ነው ይህ ችግር ከሰፈር አልፎ የአገር ችግር ሆኗል፡፡ የተፈጠረውንችግር ለሆዳቸው ያደረጉ አወቅንልህ ባዮች ያልበላነውን እያስከፈሉን ነው፡፡

ዳኘው፡ ከዛሬ ጀምሮ የእነ አሸብር አይነት ተደብቀው የሚያጋድሉ ሆድ አምላኪዎችአገራችንን ሲበድሉ እያየን መታገስ የለብንም፡፡

በለው፡ ታሪክ ዳቦ ሆኖ አያውቅም እርምጃ ያስፈልጋል፡፡ ባለፈ ታሪክ ስንመራአንኖርም፡፡

መርምር፡ ታሪክማ ሊመራን ይገባል! ያለፈ ማንነታችን የነገ መንገዳችንን ያሳየናል፡፡ካልሆነ ውሃ በሌለበት እሳት አውራ ነኝ ሊል ይችላል፡፡

አሸብር፡ አጎንብሱ ለጫናችሁ እየተባልን መሆኑ ነው?

መርምር፡ ማንም ማንም ላይ አይጫንም ሁሉም በአገሩ እኩል መብት አለው ያ ማለትግን አጥፊ በዘር ተሸፍኖ ይኑር ማለት አይደለም፡፡

ምንግዴ፡ እኔ ምን አገባኝ ታዲያ ማንም ጫነ ተጫነ ዋናው ይመቸኝ፡፡ዳኘው፡ ካሁን በኋላ አገርን አስቀድመን በህግ ጥላ ስር የመኖር ግዴታ አለብን፡፡በለው፡ የቱ ህግ? ድንቄም ህግ አሉ! ህግ ቢኖርማ…

መርምር፡ አዎ የህግ ክፍተት ሊኖር ይችላል፤ ካሁን በኋላ ግን ክፍተቱን የሚሞላየሚዲያም ሆነ ሌሎች ጉዳዮች የያዘ አዲስ ህግ መውጣቱን ሰምቻለሁ ከአሁን በፊትለነበረው ጥፋታችሁ ካሳ ይሆን ዘንድ ግን ሁላችሁም ተንበርክካችሁ ይቅርታ ጠይቁናሰላም አውርዱ፡፡

(ሁሉም በመፀፀት ይቅርታ ይጠይቃሉ)

ዳኘው፡ (በደስታ እየሳቀ) አሁን ሉላችሁም የሚሆን ዜና አለኝ የመጣብንን ችግርበ ጥበብና በትዕግስታ አልፈነዋል፤ ጠላቶቻችንም አፍረዋል፡፡ መስማማታችን ያመጣውን ለውጥ ተከተሉኝና ላሳያችሁ፡፡ (ይከተሉታል፤ሰላማችንና አንድነታችን ለእድገታችን፤ አገር ከምንም ነገር በላይ ነው የሚል ፅሁፍ ያለበትና በአረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ የተለበጠአዲስ ነገር ያሳያቸዋል፡፡ ሁሉም በደስታ ይተቃቀፋሉ)፡፡

የኢትዮጵያ ብሄራዊ መዝሙር ይዘመራል፡፡

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ደግሞ ከሆነ ሃሰት በማለት መልሱ፡፡

1. አብላላው ጥሩ ስነምግባር አለው፡፡
2. መርምር ከአገር ዘርን ያስቀድማል፡፡
3. አገር ከምንም ነገር በላይ ነው፡፡
4. አሸብር ለሆዱ ያደረ በጥባጭ ነው፡፡
5. ምንግዴ መወላወል አይታይባትም፡፡
6. ዳኘው ጥበባዊ መሪ ነው፡፡

### 5.1.3 አካባቢው አቅጣጫ ማሳያ ምልክቶች /አርማ እና የተለጠፉ እና የተለጠፉ ማስታወቂያ / ፖስተር

ከተማሪዎች የሚጠበቀው  የመማር ውጤት

ይህን ትምህርትተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የክወናና ዕይታጥበብ የትራፊክና የመንገድ ዳር አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች ትለያላችሁ፡፡
- የክወናና ዕይታጥበብ ታዋቂ የሆኑ የሀገር ውስጥ የንግድና የአገልግሎት ሰጪ ምልክት አርማዎች ይተዋወቃሉ፡፡
- የክወናና ዕይታጥበብ የተለመዱ ምልክቶችና አርማዎች ታውቃላችው፡፡
- የክወናና ዕይታጥበብ የተለያዩየ ፋሽን ልብሶች ማስታወቂያ ፖስተር የምግብና የመጠጥ  መለያ አርማና ፖስተሮች ይለያሉ፡፡

ቅድመ ዕይታ ስዕላዊ መግለጫ




ሥዕል፡-መረጃ ጠቋሚ ምልክቶች

አንዳንድ የተለመዱ ምልክቶችና አርማዎች የሚከተሉት ናቸው

- የልብ ምልክት- ፍቅርን፣ርህራሄን ይወክላል::
- የእርግብ ምልክት - ሰላምን ፍቅርን እና መረጋጋትን ይወክላል ::
- የሪቫን ምልክት- ሞትን እና ጥፋትን ይወክላል ::
- የዛፍ ምልክት - እድገትን፣ ተፈጥሮን ፣ መረጋጋትን ዘላለማዊ ሕይወትን ይወክላል ::
- የጉጉት ምልክት - ጥበብንና ብልህነትን ይወክላል::
- የቢራ ቢሮ ምልክት- መውደድን ፣ ውበትን እና ለውጥን ይወክላል ::
- የውሻ ምልክት - ታማኝነትን ፣ ጥበቃን ፣ ዳኝነትን ይወክላል ::
- የአንበሳ ምልክት - ድፍረትን፣ መሪነትን ፣ ንጉሳዊነትን ይወክላል ::
- የቀበሮ ምልክት - ተንኮልና ብልህነትን ይወክላል ::

መልመጃ 1

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

ሀ/የጉጉት ምልክት መገለጫ ጥቀሱ?

ለ/የሪቫን ምልክት ውክልና ግለጹ?

ሐ/የዛፍ ምልክት ውክልና ግለጹ?

መ/ የልብ ምልክት ውክልና ግለጹ?

በግራፊክ ዲዛይን እና በእውነተኛው ዓለም ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የተለመዱ ምልክቶች፦

የቀስት ምልክቶች - አቅጣጫዎችን ለመወከል ያገለግላል

ደመና ፣ ዝናብ፣ በረዶ እና የፀሐይ ምልክቶች - የአየር ሁኔታን ለመወከል ያገለግላሉ

የኃይል፣ የዲስክ፣ የዋይ ፋይ እና የብሉቱዝ ምልክቶች - ቴክኖሎጂን ለመወከል ያገለግላል፡፡

የተሽከርካሪ ወንበር ፣ መረጃ ፣ የመታጠቢያ ቤት እና የማጨስ መከልከልን የሚያመለክቱ ምልክቶች - ለሕዝብ ቦታዎች በተገኙ የተለያዩ ምልክቶች ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

### መልመጃ 2

ቀጥሎብ ‹‹ሀ›› ረድፍ የቀረቡ ምልክቶች ሲሆን በ‹‹ለ›› ረድፍ ከቀረቡት የየመልክቶች ዋና ዋና ሀሳቦች ጋር በማዛመድ መልሱ፡፡

| | « ሀ » | « ለ » |
| --- | --- | --- |
| 1 |  | ሀ/ አቅጣጫዎችን ለመወከል ያገለግላል |
| 2 |  | ለ/ ይህም ሰላምን ፍቅርን እና መረጋጋትን ይወክላል |
| 3 |  | ሐ/ መኪና ማቆም ክልክል ነው |

## 5.2. - የንግድና ተዛማች ዘርፍ ያላቸው ዳርጅቶች እና አርማዎቻቸው

እነዚህን የእንስሳት ባህሪን ተከትለው የሰው ልጆች ለድርጅት አርማዎችን የንግድ ምልክቶች አድርጎ ሲጠቀሙባቸው ቆይቷል ፡፡ የንግድ ዘርፉ ያመረተውን ምርት የሚሰጠውን አገልግሎት ለደንበኞቻ ለማቅረብ ለማስተዋወቅ የንግድ ምልክት አርማ ዎችና መለያ ስሞችን የተጠቀማሉ ፡፡ ይህን ሀሳብ ግልፅ ለማድረግ በሀገራችን ብሎም በከተማችን የተለያዩ ምርትና የምርት መለያ አርማዎች ፣ ምልክቶች ከዚህ ባችታ እንመለከታለን ፡፡

መልመጃ 3:-

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ፡፡

1- ታማኝነትን፣ጥበቃን፣ዳኝነትን የሚወክለው የቱነው?

ሀ ጅብ ለ አንብሳ ሐ ውሻ መ ላም

2 በዕይታ -ጥበብየተገለጸው መውዳድን፣ ውበትን እና ለውጥን የሚወክለው ማን ነው?

ሀ የአንብሳ ለ የበረሮ ሐ የውሻ መ የቢራ ቢሮ

3- ድፍረትን፣ መሪነትን ፣ ንጉሳዊነትን የሚወክለው የቱ ነው?

ሀ- የቀበረሮ ለ- የአንበሳሐ- የቢራ ቢሮ መ- የጉጉት

### 5.2.1. የትራፊክና የመንገድ ዳር አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች

የትራፊክ እና የመንገድ ዳር አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶችን ስንመለከት ሁለትወይም ሦስት ቀለማት ያልበለጡ በመጠቀም ለማህበረሰቡ በቀላሉ መረጃእና ጥቆማ ይስጣሉ :በአብዛኛው ጊዜ የመንገድ ዳር የትራፊክ ምልክቶችን በቀላሉማየትና ማስተዋል ይገባል:: ምልክቶችም አለምአቀፋዊ ናቸው::










ሥዕል ፡-የትራፊክ እና የመንገድ ዳር አቅጣጫ  ጠቋሚ ምልክቶች

መልመጃ 4

ቀጥሎ የተቀረቡትን ጥያቄዎች፣ ባዳመጣችሁት ገለፃመሰረት፣ትክክል የሆነውን ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በቃል መልሱ፡፡

1 ጠቋሚ ምልክቶች ቀላልና ግልፅ መሆን አለበት?

2 መለያ አርማዎች በልዩ ሁኔታ አጉልቶ የሚያሳይ ዲዛይንመምረጥ ያስፈልጋል፡፡

3 ትኩረት ሳቢ ምልክቶችን ቅርፃችንና ቀለሞችን መጠቀም አያስፈልግም፡፡

4 አይን ግቡ የሆኑ የቀለም ምርጫዎችና ምጣኔዎችን መግባት ይኖርበታል፡፡

5 የዕይታ ጥበብእናየእደ ጥበብሥራዎች አእምሮን ያነቃቃሉ፡፡

አቅጣጫ፣ጠቋሚ መረጃ ሰጪ ምልክቶች

በተለያዩ አገልግሎት ስጪ ተቋማት ሰንሄድ የምንመለከታቸው አቅጣጫ፣  ጠቋሚ መረጃ ሰጪ ምልክቶች አሉ ፡፡ እነሱም በት/ቤት ፣ በሆስፒታል፣ በሆቴ ሎች ፣ የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ የምናገኛቸው ምልክቶች ባለ አንድና ባለ 3 ቀለማት ምልክቶች ናቸው ፡፡

ለምሳሌ ፡-የመፀዳጃ ቤት ጠቋሚ ምልክቶች ፤ የአደጋ ጊዜ መውጫ

ምልክቶችና ጠቋሚ ምልክቶችን ቀስቶችን እናገኛለን





ሥዕል፡-የመፀዳጃ ቤት እና የአደጋ ጊዜ መውጫ ምልክት

### 5.2.2 ፖስተር

ፖስተር ማለት የአንድ ፊልም ለማስታወቂያየሚውል ከፊልም ወይም የምርት መለያ ማስታወቂያ ውስጥ ተመርጦ የወጣ ሳቢና አጓጊ የምስልና የፀሑፍ መግለጫ ያለው የንግድ መሳቢያ ጥበባዊ ዘርፍ ነው ። በአለም ላይ የተለያዩ የፊልምና የምርት አገልግሎት አርማዎችን ፖስተሮችን እናገኛለን ። ለምሳሌ የኮስሞቲክስ ማስታወቂያፖስተር የተለያዩየ ፋሽን ልብሶች ማስታወቂያ ፖስተር የምግብና የመጠጥ መለያአርማና ፖስተሮች ዘወትር የምናውቃቸው ናቸው።



ሥዕል፡-ፓስተር

•ተማሪዎች እንዴት ጥሩ ፖስተሮችን መስራት እንደምትችሉ መምህራችሁ በቀድምተከተል ያሳዮአችሁ፡፡

## የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ በዋናነት ጥመርታ ላይ ትኩረት በማድረግ የትራፊክ፣ የኤች አይቪ. የአደንዛዥ ዕፅ ወዘተ… የሚገልፁ /ድንበር ተሻጋሪ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን ከመዝሙር /ከሙዚቃ/ ከውዝዋዜ፣ ከትያትር፣/ተውኔት/ እና ከፖስተር ጋር በማጣመር በእያንዳንዱ የጥበብ ዘርፍ እነዚህ ድንበር ተሸጋሪ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን መከላከልና ማህበረሰቡን እንዴት ማስተማር እንደሚቻልና ስለ መንገድ ዳር የትራፊክ ጠቋሚ ምልክቶች በዝርዝር ለማወቅ የቻልንበት ምዕራፍ ነው፡፡

### የመልመጃ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡ፡፡

1. ልማዳዊ የሆነ ውዝዋዜ ክዋኔ የቱ ነው?

   ሀ. ቀረርቶ ለ. ንድፍ ሐ. እስክስታ መ. ዳንስ

2 አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን ያዢ፡፡

ሀ. ዘይቤ ለ. ምሳሌያዊ አነጋገር ሐ. ቅርፅ መ. ገላጭ ቃል

3 የክብረ በዓላትና ፌስቲቫሎች ገላጭ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. በጋራ መሰባሰብ ለ. አብሮ መብላት ሐ. ግለኝነት መ. የማህበር ስራ

ከዚህ በታች ለተጠየቁት ጥያቄዎች አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡

1. የጥልፍ ስራ በልብስ ላይ ብቻ ያተኮረነው፡፡
2. የዶሮወጥ በበዓላት እንደዚሁም አስፈላጊ በሆነ የክብር በአል ላይ የሚቀርብ የምግብ አይነት ነው ፡፡
3. የብረታ ብረት ስራ  ሞፈር፣ ማረሻ፣  ቀምበርን ያጠቃልላል፡፡

## ዋቢ መፃህፍት

-Basic Music Theory: How to read write and understand written music/ Jonathan harnum

-The complet idiotis guide to Music theory / Michael miller

-The College Board: Music Theory course

-Music Theory Fundamentals High-Yield Music Theory, vol. 1

Mark Feezell LearnMusicTheory.net

- ሰለሞን ኃይለማርያም / በስብስብ ላይ የተጻፉ ክረቶችን መለየት (ያልታተመ)

- SOLOMON HAILEMARIAM / Staff,Ledger Lines and Clefs / Augest 2020

-መሰረታዊ የውዝዋዜ ፅንሰ ሃሳብ በውቀቱ ስዩም፡፡ ወንዞች እስኪሞሉ እና ሌሎች አጫጭር ላብ ወለዶች፡፡ አዲስ አበባ ፖፕሌሽን ሚዲያ ሴንተር፤ 1998 ዓ.ም፡፡

-ቤቶች ድራማ 2011 ዓ.ም፡፡

-ዘሪሁን አስፋው፡፡ የስነ-ጽሁፍ መሰረታዊያን፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣1992 ዓ.ም፡፡

-ጳውሎስ አእምሮ፡፡ የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2010 ዓ.ም፡፡

-ፋንታሁን እንግዳ፡፡ የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1992 ዓ.ም፡፡

-Todd Debreceni. Special make up effects for stage and screen, Making and applying prosthetics. Focal Elsevier press, 2009.

-VISUAL AND PERFORING ARTS JUNIOR (GRADE 3-7) SYLLABUS 2015-2022

- Art to day

- understanding art

- Teaching Art to young children 2002 Rout ledge Falmer

- Foundation of Art and Design 2008

- Art Education 1996

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

2014 ዓም/2021